t.me/BooksandYou

# የዕውቀት ማኔጅመንት አውታሮች

አበበ ቅሩብ

t.me/BooksandYou

# የዕውቀት ማኔጅመንት አውታሮች

አበበ ቅሩብ

የዕውቀት ማኔጅመንት አውታሮች
©አበበ ቅሩብ፣ 2009 ዓ.ም
ISBN 9789994466450

ሕትመት፡ በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

t.me/BooksandYou

# ማስታወሻነቱ

በግብርና ምርምር ዙሪያ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ዕውቀታቸውን ሳይቆጥቡ ለአገራቸው የዜግነት ግዴታቸውን ለተወጡና በመወጣት ላይ ላሉ ተመራማሪዎችና ለምርምሩ ግብ ስኬት የማይተካ ሚናቸውን ለተወጡና በመወጣት ላይ ላሉ ለሁሉም የግብርና ምርምር ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሮች ይሁንልኝ፡፡

t.me/BooksandYou

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መቅድም | 4 |
| መግቢያ | 6 |
| የዕውቀት የትርጉም ወሰን | 12 |
| የዕውቀት ማኔጅመንት | 20 |
| የዕውቀት ማኔጅመንት ዘመናት | 34 |
| የተቋም ዕውቀት ማኔጅመንት | 44 |
| የዕውቀት ማኔጅመንት መሠረቶች | 52 |
| የዕውቀት ሽግግርና መጋራት | 74 |
| ዕውቀትን መተርጐም እና መጠቀም | 93 |
| የሳይንስ ዕውቀት | 111 |
| ዕውቀት የልማት ውል | 123 |
| ፈጠራን በዕውቀት መታደግ | 135 |
| ትረካና ዕውቀት ማኔጅመንት | 143 |
| ዕውቀት ማኔጅመንትና ፖለቲካዊ አንደምታው | 153 |
| የዕውቀት ኃያልነት ሲጠነጠን | 163 |

t.me/BooksandYou

# መቅድም

መቅድም መጻፍ የተለመደ ቢሆንም ትንሽ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ስነሳሳ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ብዬ መጀመር እንዳለብኝ አስቤ ነበር፡፡ ይህን ሳስብ ደግሞ የመጽሐፉ ግዝፈት ምንም ያክል ምን አነስ ያለ ነገር ቢያንስ ለሽክም ይመቻል ከሚል ሐሳብ ለመራቅ አልሞከርኩም፡፡ መጽሐፉን ለማገባደድ ስዳረስ ደግሞ እምነቴ ከፍ ብሎ የመጽሐፉ ይዘት ምክንያታዊ በሆነ እይታዬ መልካም የመረጃ ምንጭ እንደሆነ ሳልጠራጠር ለራሴ መስክሬያለሁ፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ለማቅረብ በሞከርኳቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ ይዘቶችና አቀማመጦች በርካታ የመረጃ ምንጮች እንዳሉ እምነቴ ነው፡፡ ከእነዚህ ምንጮች የቻልኩትን ያህል ለማንበብ ሞክሬያለሁ፡፡ ጥቂቶች የማይባሉትንም በሚመቸኝ መንገድ ሐሳባቸውን አግባብቼ ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡ ዋናው የዋቢ

መረጃ ምንጮቼ ግን የራሴ ተሞክሮዎች፣ የጓደኞቼ ሐሳቦች እንዲሁም ከተለያዩ የዕውቀት ማዳበሪያ መድረኮች፣ ስብሰባዎች፣ ብሎጎች እና ሌሎች የሚዲያ ምንጮች ያጠራቀምኳቸውና እንደአግባብነታቸው አስማምቼ ለዚህ መጽሐፍ የተጠቀምኩባቸው ናቸው፡፡

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ሳስብ በርካታ የሥራ ባልደረቦቼን አማክሬያለሁ፡፡ መልካም ምክራቸውን ወስጃለሁ፡፡ የቤተሰቦቼንሐሳቦች ተቀብዬ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ጽሑፉን መስመር በመስመር በማንበብ እጅግ የላቀ ሃሳብና ምክር ለለገሱኝ ለዶ/ር ፈንታሁን መንግሥቱ በቃላት ያልተገደበ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ጽሑፉን በመጻፍና በማረም ወ/ሮ እታገኝ ተክሉ በሚገባ ደግፈውኛል፡፡ የቃላትና የሆሄያት ግድፈቶችን በማረም አቶ ሃይማኖት ታደገ ልዩ ድጋፍ አድርገውልኛል፡፡ ለሁሉም ልባዊ ምሥጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት መፅሃፉን በማተም ያደረገዉ አስተዋፅኦ እጅግ የላቀ ስለሆነ ለእንስቲቱዩት የከበረ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

t.me/BooksandYou

# መግቢያ

ሰዎች አእምሯዊ ተግባራትን ለማከናወን ትውስታቸውን እንደሚጠቀሙ በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ አካባቢያቸውን በመቃኘት ግንዛቤያቸውን ያዳብራሉ፡፡ ይህም አእምሯቸውን እያነቃቃና እያለሰለሰ ግንዛቤያቸውን እንዲያጐለብቱ ይረዳቸዋል፡፡ ትውስታቸውንም በማረጋጋት ግለሰባዊ እውቀታቸው እንዲዳብርና ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን በቀላሉ ቃኝተው በበለጠ ግንዛቤ አስፈላጊ ውሳኔዎችን እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ መሠረታዊ ታሳቢነት የግለሰብ እውቀት ሁሉንም የትውስታ ማዕቀፎችንና እንቅስቃሴዎችን ያካተተና ግለሰቦችም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲገቡ የሚያደርግ ጸጋ ወይም እምቅ ሃይል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው እውቀትና የሰው ልጅ የማይነጣጠሉ ናቸው የሚባለው፡፡

ተቋማትም የግለሰቦችን እውቀት በማሰባሰብ አደረጃጀታቸውንና ሥራቸውን የተቃና፣ ቀልጣፋ እና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ ትኩረት ሰጥተው ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡ አንድ ተቋም የአደረጃጀትና የአሠራር ውጥረት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ከሰዎች ሕልውና ጋር ያለ ዕውቀት የተቋሙን መለወጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ሲደራጅ ተቋማዊ ዕውቀት የሚያሰኝ ትርጉም ሊይዝ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ይህ ተቋማዊ ዕውቀት ከተቋማዊ የመረጃ ቋቶችና ሥርዓቶች የሚለየው እውቀት የሰዎችን መስተጋብርና ግንኙነት ከምንም በላይ አጥብቆ ስለሚጠቀም መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ስለሆነም እውቀት በሰዎች መካከል ያለውን መስተጋብርና ግንኙነትን ማዕከል በማድረግ ማንኛውንም ተግባር በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ትርጉም ባለው መልኩ ማንቀሳቀስና ተቋማዊ ግብን የተሳካ ማድረግ የሚያስችል እንደሆነ በሰፊው ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን ያልተፍታታ እውቀት ይዞ ውጤታማ ለመሆን አስቸጋሪነቱን ከወዲሁ መረዳት ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ የእውቀትን ይዘትና ቅርፅ በውል መረዳት አስተዋይነት መጨመሩን ያስገነዝባል፡፡

የዕውቀት ምንጮች እምነትን፣ ባህልን፣ ጥበብን፣ ስሜትን፣ የግል ተሞክሮን፣ አእምሮን እና ምርምርን አካተው የያዙ ውስጣዊ

ስሜቶች የታሸጉባቸው ካርቶኖች እንደሆኑ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ እውቀትን ለመገንዘብ ከዚህ የሚከተሉትን ጭብጦች ማጤን አግባብነት ይኖረዋል፡፡

- ዕውቀት የሁሉም ስብና እንቅስቃሴዎች መሠረት ነው፤
- ዕውቀት ከሰው ልጆች ጋር ነባር እና ቀጣይ ግንኙነት አለው፤
- ዕውቀት የማንኛውም አእምሯዊ ሂደት ወይም እንቅስቃሴ ውጤት ነው፤
- ዕውቀት በቀጣይ የለውጥ ተፅዕኖ የሚፈጠር ነው፡፡
- እና ሌሎችም....

በአገራችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት የኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኖሎጂካዊ እና ማኅበራዊ ግስጋሴዎች እና መሸጋሸግ እንደነበረና ለውጡም በቀጣይነት እየተጓዘ መሆኑ ይታያል፡፡ እነዚህ ለውጦች በተቋማት አደረጃጀትና አሠራር ላይ አዳዲስ ሚናዎችና ፈተናዎችን እያሳደሩ መምጣታቸውም ከግምት ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህን ሚናዎችና ተግዳሮቶችንም ወደ መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ተቋማዊ ሽግግሩን ማፋጠን ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ ለዚህም የተቋማትሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሩ በእውቀትና ክህሎት በስለው መገኘታቸው አጠራጣሪ

አይደለም፡፡ ይህም የዕውቀት የእሴት ሰንሰለቱን ፈርጣማና ለስላሳ ያደርገዋል የሚል እምነትን ያሳድራል፡፡ ለዚህ ተግባራዊነት ተቋማዊ የእውቀት ዝግጁነትና ትግበራ ባህልን አዳብሮ መገኘት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የአንድ መጽሐፍ መግቢያን ከማዘጋጀት በፊት የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ ይህም በሁኔታዎች ላይ ሚዛናዊ አስተሳሰብ እንዲሰርፅ ያደርጋል፡፡ ካልሆነም ያልተመጣጠኑ ሐሳቦች እና ያልዳበሩ ምክሮችም መስመራቸውን ስተው ወይም አጥጋቢ ሐሳብ ሳያካትቱ የማቅረብ ዝንባሌን ሊያባብስ ይችላል፡፡ በተቻለ መጠን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ወደ አንድ ወገን ያላደሉ ወይም ልቅሐሳቦችን ለመመጠን ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም አልፎ አልፎ ጥቂት የማይባሉ አስተሳሰቦች ላይ ድጋፍ ለማድረግ መሞከሬን በቅን ልብ ልመሰክር ይገባኛል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዓላማም የዕውቀትን ፈርጆች፣ ዓይነቶች፤ አጠቃቀምና ማኔጅመንትን በሚመለከት ቀለል ባለ መልኩ ለአንባብያን ማቅረብ ነው፡፡ እውቀት የአንድ ሙያ ውጤት ሳይሆን የበርካታ ሙያዎችና ተሞክሮዎች ውጤት በመሆኑ በዚህ

መጽሐፍ የተለያዩ ባለሙያዎችንና የራሴንም ተሞክሮ በማሰባሰብ እና በመተንተን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ሂደት ግልፅነት የጐደላቸው ወይም ያልተቋጩ ወይም ያልበሰሉ ሐሳቦች ከተካተቱ ሙሉ በሙሉ የእኔ እንጂ የሌሎች የመረጃ ምንጮች እንዳልሆኑ አንባብያን እንዲረዱት አሳስባለሁ፡፡

ዕውቀት በሥርዓት ተደራጅቶ ካልተመራ ጠቃሚነቱ ያነሰ ይሆናል፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት አቢይ ጥቅሙም ዕውቀት በተቋማዊ ለውጦች ወይም ሽግግር ላይ የሚኖረውን በጐ ተፅዕኖ ለማጐልበት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር በተቋም እሴቶች ላይ የዕውቀትን ሚና ማጉላት ነው፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት ሰፋፊ ቅኝቶችም ተዳሰውና ተተንትነው እንዲቀርቡ ጥረት ተደርጓል፡፡

t.me/BooksandYou

# የዕውቀት የትርጉም ወሰን

የዕውቀትን ትርጉም ወሰን የሚገዙ በርካታ ጽንሰ ሐሳባዊ እና ተተግባሪ ጉዳዮች ይኖርራሉ፡፡ ዕውቀት በአንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ውስን እይታ የማይገታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይህም የእውቀትን የትርጉም ወሰን ሊያጠበውም ሊያሰፋውም የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ማየት መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም ዕውቀት በእይታ፣ በግንዛቤ እና በመረዳት የሚገኝ ሁለንተናዊ ገፅታ መሆኑ ነው፡፡ በስፋት የሚታወቁት የዕውቀት የትርጉም ወሰኖችን እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጎ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

# መደበኛ ዕውቀት

ተጠቃሽነት ያለውና በሥርዓት የተቀመጠ ሆኖ በቀላሉ ተደራሽ ነው፡፡ለምሳሌ፡- የመረጃ ቋት፣ ማስታወሻዎች እና ዶኩመንቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ እነዚህም በተሟላ ሁኔታ ኃላፊነት የሚወሰድባቸው ናቸው፡፡

# ተሞክራዊ ዕውቀት

በአእምሮ ውስጥ የተከማቸ ዕውቀት ሲሆን የዓመታት ተሞክሮን ያማከለ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ባህላዊ እምነቶች፣ እሴቶች፣ አመለካከቶች፣ ክህሎት፣ አቅምና ሙያን መጥቀሱ ይቻላል፡፡ የዚህ ዓይነት ዕውቀት ባለቤቶችአውቀዋለሁ ከማለት ባሻገር ዕውቀታቸውን በተግባር መግለፅ ያዳግታቸዋል፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደሚገልፁት ሰዎች ከሚናገሩት ወይም ሊገልፁት ከሚችሉት በላይ አዕምሯቸው ያጠራቀመው ዕውቀት እንዳላቸው ነው፡፡ ስለሆነም የታመቀና የተነገረ ዕውቀት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በእነዚህ መካከልም ማወቅ እና አውቆ መተግበር ወይም ክህሎት ብሎ መለየት ይቻላል፡፡

# ተካቶ ዕውቀት

በአብዛኛው በሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ተቋማዊ ባህሎች እና የሥነ-ምግባር መተግበሪያዎች ውስጥ ተካቶ የሚገኝ የዕውቀት ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዓይነት ዕውቀት በቀላሉ ተደራሽ ሆኖ ጥቅም ላይ ለማዋል ውስብስብነት ይታይበታል፡፡ አጠቃቀሙም በኃላፊነት ላይ የተመረኰዘ ነው፡፡

ዕውቀት በተለያዩ መዝገበ-ቃላት፣ ሌሎች ጽሑፎችና አነጋገሮች በተለያዩ መልኮችና ይዘቶች ይወከላል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ችሎታ ወይም ተወዳዳሪ (ከሥልጠናና ከተገኘ ዕውቀት የተነሳ)፤
- ግንዛቤ፤
- ትምህርት (በጥናት፣ በሥልጠና የተገኘ ውጤት)፤
- ሙያዊ ችሎታ፤
- ያዘ፣ ጨበጠ (የመረዳት አቅም)፤
- አርቆ ማስተዋል፣ የውስጡን (የማይታየውን) ማየት፤
- የማሰብ ችሎታ፣ የአዕምሮ ምጡቅነት፣ ሚሥጢራዊ መረጃን የመሰብሰብ ብቃት፤
- ድምዳሜ፤

- የተሟላ ዕውቀት መኖር (አንዱን ከሌላው በዕውቀት መለየት)፤
- ትምህርት መማር፤
- ምልከታ፣ በትኩረት ማየት፣ ማስተዋል፣ በመመልከት ማወቅ፤
- ፍልስፍና፣ እውነትን ፍለጋ፤
- ኃይል (ጉልበት)፣ የማድረግ ወይም የመሥራት አቅም፤
- ብቃት፣ ችሎታ፤
- ዕውቅና፣ አንድን ነገር አለ ብሎ መቀበል (እውነት ነው ማለት)፤
- ሳይንስ (ሥነ-ጥበብ)፤
- ፅንሰ-ሃሳብ፤
- ጥበብ፣ የትክክለኛነትና የእውነት ዕውቀት፤
- ክንውኖች፣ በአግባቡ የተሠራ ሥራ (በዕውቀት)፤
- ጓደኝነት፣ ትውውቅ፣ በጥናት ወይም በልምድ የተገኘ ዕውቀት፤
- መጪ ሁኔታን መፍራት (በነገሮች ላይ የሚኖር ሐሳብ)፤
- ማግኘት፤
- መገንዘብ፣ የማወቅ ሂደት፤
- የንግግር ወይም የጽሑፍ መለማመጃ፤
- ንቃተ ኅሊና፣ ከፍተኛ የማሰብ ሁኔታ፤
- ግላዊ ሚሥጢር ሆኖ የተጋለጠ፤
- መረዳት፣ መለየት፤
- አስተምህሮ፤
- ቀኖና፤

- ተቀባይነት ያለው መረጃ፤
- መጠበብ፤
- ልቅና፤
- እውነታዎች፣ እውነተኛ ወይም ግልፅ ክስተት፤
- ሸቀጣሸቀጥ (በመጠንም በጥራትም የሚመጥን)፣ በዕውቀት የተሠራ፤
- ትዕዛዝ ዕውቀት ወይም መረጃ የሚሰጥ፤
- መልክ/ብርሃን፤
- ልማድ/ወግ (መማር ማወቅ)፤
- ምስል (በአዕምሮ የሚሳል ዕውቀት)፤
- መመሪያ/መርህ፤
- ነፃ የትምህርት ዕድል (በትምህርት የተገኘ ዕውቀት)፤
- ማስተማር፤
- ጠቃሚ ዜና፤
- ቁስ/ይዘት፤
- አንድ ተማሪ ማስተማር፤
- የግል የቋንቋ ትምህርት የሚሰጥ ት/ቤት፤
- ሚሥጢር፤
- ፓተንት፤
- የግልጋሎት ሞዴል፤
- የንግድ ምልክት፤
- ቅጅዎች፤

- የተግባር ልምድ፤
- አዕምሯዊ ንብረት፤
- የትብብር ሥራዎች/ፕሮጀክቶች፤
- የስምምነት ማዕቀፎች፤
- የሥልጠና ሰነዶች፤
- የመግባቢያ ሰነዶች
- የጥናትና ምርምር ሪፖርቶች፤
- የሚዲያ መርሃ-ግብሮች፤
- የጥራትና ደረጃ ሰነዶች፤
- የድረ-ገጽና ማኅበራዊ ሚዲያዎች፤
- የብራንድና ስያሜ ሰነዶች፤
- ቃለ-ጉባኤ፤
- የአፈፃፀም አቅጣጫዎች፤
- የጽሑፍ ስምምነቶች፤
- የኮንትራት ውሎች፤
- የሥልጠና ውሎች፤
- የምርምር መረጃ ልውውጥ ውሎች፤
- መረጃ የመጋራት ውሎች፤
- እና ሌሎችም...

ከላይ በተቀመጠው መሠረት የዕውቀት ምንጮች አድማሳቸው ሲፈተሽ የሚያሳየውን ተመልክተናል፡፡ በተለይ በግለሰቦች ዙሪያ የዕውቀት ምንጭነት በትምህርት ዝግጁነታቸው፣ በባህላቸው፣ በእምነታቸው፣ በልምዳቸው፣ በፍላጐታቸውና በምርጫቸው በተለያዩ የዕውቀት ደረጃዎች ሊተመኑ ይችላሉ፡፡ ከተለያዩ የዕውቀት ደረጃዎች ወደ ሌላው ማደግና መሻሻልን ለማምጣት አሁን ያሉበትን የዕውቀት ደረጃ በሚገባ ተረድቶ፣ አርሞና ገርቶ መዳዝን በውል ይሻል፡፡ በውል ባልተረጋገጠ ዕይታ ሲታይ ዝቅተኛው የዕውቀት ደረጃ ከሰብዓአዊነት ዝቅ ባለ ሁኔታ ላይ መገኘትን ሊጠቁም ይችላል፡፡ ሌሎቹ ደረጃዎች ደግሞ እንደሁኔታው ከላይ በተጠቀሱት ጫፎች መካከል ሊፈረጁ እንደሚችሉ መረዳት ተገቢ መሆን ብቻ ሳይሆን የዕውቀት የትርጉም ውስንን አስፍቶና አጥርቶ ማየትን ይጠቁማል፡፡

# የዕውቀት ማኔጅመንት

የዕውቀት ማኔጅመንት ዙሪያ መለስ ትርጉሙ ዕውቀትን በመፍጠር፣ በመጋራት እና በመጠቀም ላይ የሚያተኩር እንቅስቃሴ መሆኑ በስፋት ይገለፃል፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት ተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራርን የወል መንገድ አድርጎ ይከተላል፡፡ በመሆኑም በአንድ ተቋም ወይም ድርጅት ውስጥ ያሉ ፈርጀ-ብዙ አስተሳሰቦችንና የሙያ ስብጥሮችን ያካትታል፡፡ ይህም በአግባቡ የተደራጀ ዕውቀት የአንድ ተቋምን መሠረታዊ ዓላማና ተቋማዊ ግብ ለማሳካት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ያስችላል፡፡

ዕውቀትን ከማስፋፋትና ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ የዕውቀት ማኔጅመንት አስፈላጊነት በሰፊውና በጥልቀት እየተገለፀ ያለ ጉዳይ ቢሆንም በዋናነት እና ልማዳዊ በሆነ መንገድ ሲገለፅ ግን የሚከተሉትን ጉዳዮች ተንተርሶ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

- ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ዕውቀትን ያለሥጋት በተደጋጋሚ መጠቀም እንዲቻል፤
- ከተለያዩ የሥራ ዘርፎች ወይም ሂደቶች የተለያዩ የዕውቀት ምርጥ ጸጋዎችን ለመሰብሰብ፤
- የማኅበራዊ የዕውቀት ምንጮችን በወሳኝነት ለመደገፍ፤
- ታዳሽና ፈጠራዊ ሥራዎችና ሐሳቦችን ለማዳበር፤
- የዕውቀት ጉጉትን/ፍላጎትን ለማርካት፤
- እና ሌሎችም...

ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች የዕውቀት ማኔጅመንት መሠረቶችን እና ፅንሰ ሐሳቦችን ከማጐልበት አንፃር የሚከተሉትን ዋቢ መርሆዎች አካቶ ማየት ይቻላል፡፡

- ዕውቀት ስኬትን ይወስናል፤
- ዕውቀት በሰዎች አዕምሮ ውስጥና ዙሪያ ይገኛል፤
- የተደራጁና ግላዊ ዕውቀቶች አሉ፤
- ለዕውቀት ሽግግር አመቺ ሁኔታዎች ሊከሡቱ ይገባል፤
- የዕውቀት ሽግግር አመኔታን ይሻል፤
- የዕውቀት ማኔጅመንት ተቋምንና የትምህርት ዘርፎችን ያካትታል፤
- ዕውቀት የራሱ መዋቅር አለው ሲያሻው የተበታተነ፤ በወጉ ሲመራም የተደራጀ ነው፤
- እና ሌሎች…

እ.ኤ.አ. ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዕውቀት ማኔጅመንት በዩኒቨርስቲዎች ደረጃ በተለያዩ የሙያ መስኮች በተለይ በንግድ አስተዳደር፣ በመረጃ ሥርዓት፣ በማኔጅመንት፣ በቤተመጻህፍት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

በመረጃ ሳይንስና በመሳሰሉት እንደ አንድ የሙያ ዘርፍ ትምህርት መስጠት እንደተጀመረ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ የሙያ መስክ በራሱ ቆሞ ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ዶክቶራል ዲግሪ ድረስ የትምህርት መስክ ሆኖ ሥልጠና እየተሰጠበት ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ኩባንያዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባንኮች፣ የምርምር ተቋማት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የመንግሥት ሚኒስትሪዎች፣ አማካሪ ድርጅቶች እና ሌሎች ለዕውቀት ማኔጅመንት ትኩረት በመስጠት በአደረጃጀታቸውና በሥራቸው ላይ በጐ ተፅዕኖ እንዲያመጣ በሥራ ዘርፍነት አካተውት ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የሙያ አማካሪ ድርጅቶች ለተለያዩ ተቋማት የሙያ ማጐልበቻ በዕውቀት ማኔጅመንት ዙሪያ ሥልጠናዎችን ሲሰጡ ይታያል፡፡ ተቋማዊ አደረጃጀቱንም ያማክራሉ፡፡

በተቋም ደረጃ የዕውቀት ማኔጅመንት ተቋማዊ አሠራርን ለማሻሻል፣ ተወዳዳሪነትን ለማጐልበት፣ በፈጠራ እና መልካም ተሞክሮዎችን ከመጋራት አንፃር፣ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር እና ቀጣይ የመሻሻል አዝማሚያዎችና አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ይህን ከሌሎች የሥራ ዘርፎች ለየት የሚያደርገው ዕውቀት አያያዝና አጠቃቀም ልዩ ትኩረት

በመስጠት ቀጣይ ማሻሻያዎችን የሚመለከታቸው የሥራ ዘርፎች በቅርብና በቀላሉ እንዲያገኟቸውና እንዲጠቀሙባቸው ሚናውን የላቀ በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ዕውቀት የሁሉም ስትራቴጂያዊ እሴቶች መሠረትና መደላድል መሆኑን ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ እውን የሚሆነው ሁሉም አስፈላጊ ዕውቀት ተደራጅቶ በቀላሉ ተደራሽ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ዕውቀት የተቋማዊ መማማር አስቻይ ነው፡፡

## የዕውቀት ማኔጅመንትና መሣሪያዎች

ለአንድ ተቋም ለዕውቀት ማኔጅመንት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ መሣሪያዎች ወይም የአሠራርና የአመራር ስልቶች በርካታና ውስብስብ ቢሆኑም ጠቅለል ባለመልኩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካትታል፡፡

- ዕውቀትን መጋራት፤
- ትረካ፤
- ከሥራና ከፕሮጀክት መማማር፤
- የአፈፃፀም ግምገማ፤
- የዕውቀት ዘገባ፤
- የድርጊት ማኅበረሰብ፤

- የባለሙያዎች መዝገብ፤
- የዕውቀት ሥርዓት፤
- መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት፤
- የዕውቀት ኤግዚቪሽን፤
- የውድድር/ፉክክር ማኔጅመንት፤
- የሠራተኞችና ባለሙያዎች ቀረቤታ፤
- ሶፍት ዌሮች፤
- የዕውቀት ቋቶች፤
- ተሞክሯዊ ዕውቀትን መለካት እና ሪፖርት ማድረግ፤
- የዕውቀት ድለላ/ጠቋሚ የዕውቀት ምንጭ አቅርቦት፤
- በፕሮጀክቶች መካከል ያለ የዕውቀት ሽግግር፤
- ሌሎችም.....

ተቋማት የዕውቀት ምንጮቻቸው ተደራሽና ጠቃሚ እንዲሆኑላቸው የተለያዩ የማነቃቂያ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሞላ-ጐደል የሚከተሉት ማነቃቂያዎች ይጠቀሳሉ፡፡

- ተቋማት ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ተደራሽ ለማድረግ የዕውቀት ምንጮችን ከግልጽ ይዘት ጋር አቀናጅተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

- የምርትና አገልግሎት አቅርቦቶቻቸውን በአጭር የጊዜ ዑደት ማድረስ ይኖርባቸዋል፤

- ፈጠራንና ተቋማዊ መማማርን በሚገባ ማሳለጥ አለባቸው፤

- ባለሙያዎችን በሚገባ ማፍራትና መጠቀም አለባቸው፤

- ከተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት ጋር ተገቢውን ትስስር ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

- የተቋሙን ሠራተኞች የዕውቀት ፍላጐትን በመለየት አቅርቦቱን ማሳለጥ አለባቸው፤

- ቀላልና ግልጽ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት ይጠበቅባቸዋል፤

- የሠራተኞቻቸውን ቁልፍ ዕውቀትና ክህሎት በተገቢው መንገድ በመምራት የግብ ስኬትን ማፋጠን ይኖርባቸል፤

- እና ሌሎችም....

ለዕውቀት ማኔጅመንት አመለካከት በርካታ ምክንያቶች በተደጋጋሚ ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- የዕውቀት ማኔጅመንት ዓላማዎችን በትክክል አለመቅረጽ፤
- የተሸመደመደ ስትራቴጂ፤
- የማይመች የዕውቀት ማኔጅመንት ሞዴል፤
- ደካማ የፕሮጀክት ማኔጀመንት፤
- ያልተናበበ ማኔጅመንት፤
- ለዕውቀት ማኔጅመንት አመቺ ሁኔታ አለመኖር፤
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከተቋም ባህል፣ አደረጃጀት፣ የሥራ ፍልሰት፣ ሂደት እና ስትራቴጂ ጋር አለማጣጣም፤
- የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓቱን በአግባቡ ተግባር ላይ አለማዋል፤

- የማይጣጣም ተቋማዊ የለውጥ አመራር፤
- የዕውቀት ማኔጅመንትን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ብቻ ለማማከል መሞከር፤
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ባልተገባ መልኩ መቆጣጠር፤
- የተቋም ባልደረቦች ሥርዓቱን በሚገባ ለመጠቀም ብቃት መጉደል ወይም ማነስ፤
- በሥርዓቱ ላይ አግባብነት የሌላቸውን ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ማባዛት፤
- በስርዓቱ ውስጥ ቁልፍ ጉዳዮችን አቀናጅቶ አለመተግበር፤
- በተቋሙ ያልተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት አለመኖር፤
- ሥርዓቱን ለመገንባት በሚደረግ የእቅድ እንቅስቃሴ የተቋሙን ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሩን አመጣጥኖ አለማሳተፍ፤

- የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓቱ ቁልፍ አካላት አፈጻጸም ደካማ መሆን፤
- የተቋም የበላይ አመራሮች ሥርዓቱን በጸጋ ያለመቀበል የሚሉት ይገኙበታል፤

- እና ሌሎችም…

ተቋማት የዕውቀት ክምችቶቻቸውን በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋልና ከሌሎች ተቋማትም ልዩ ልዩ ዕውቀቶችን ለመቅሰም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቴክኖሎጂዎችና ሥርዓቶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡

- ከሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ ዕውቀትን ለመጠቀምና በኅብረት ለመንቀሳቀስ የሚያግዙ የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂዎች በተለይ የጋራ የቡድን የውይይት መድረኮችን የሚያሳልጡ በቅድሚያ ይጠቀሳሉ፤

- ተቋማዊ ዕውቀትን በተለይ የተለያዩ የሥራ ሂደቶችን የሚያሳዩ ሥርዓቶች ለምሳሌ፡- የሥራ ቅጾችን በጋራ ለመጠቀም የሚያስችሉ ወዘተ…

- ሰነዶችን በአግባቡ በማደራጀት በኮምፒዩተር የታገዘ የዕውቀት አቅርቦትን የሚያሻሽሉ ስርዓቶችን መዘርጋት፤
- ተቋማዊ ድረ-ገጾችን መጠቀም፤
- አን-ላይን የመማማር ሥርዓት መዘርጋት፤
- እና ሌሎችም......

# የዕውቀት ማኔጅመንት መልካም መገለጫዎች

አንድ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት በባሕሪው የተለያዩ መገለጫዎች ሊሰጡት ይችላሉ፡፡ ከሞላ ጐደል የሚከተሉት መገለጫዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያሉ፡፡

- አንድ ጥሩ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት የተቋሙን ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሩን የሚያበረታታ እና የሚያጠናክር መሆን አለበት፡፡ ስርዓቱ የተቋሙን ባለሙያዎች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ተሳትፏቸውን በማጉላት የላቀ ሚና ሊጫወት ይገባል፤

- የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓቱ በተቋሙ ዋና ዋና ዓላማዎች ላይ ማተኮሩ ተገቢ ይሆናል፤

- ሥርዓቱን በፍላጐት እንጂ በቴክኖሎጂ ተደራሽነት ላይ የተመሠረተ ማድረግ ዘላቂና አዋጭ አያደርገውም፤

- ሥርዓቱ ተቋማዊ ተወዳዳሪነትን የሚያጐላ እና የአሠራር ሥርዓቱን ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሚያደርግ ሆኖ የተደራጀ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፤

- የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓቱ የተቋም ተገልጋይን እርካታ የሚጨምር ሆኖ መደራጀቱ የግድ ይላል፤

- የተቋሙን ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሩ በሥራቸው እርካታን እንዲያገኙ የሚያበረታታ መሆን አለበት፤

- የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓትን ከመዘርጋት በፊት አስፈላጊነቱ በጥሞና እና በጥልቀት መፈተሽ ይኖርበታል፤

- ጥሩ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት ሁሉንም የዕውቀት ዓይነቶችና ምንጮቻቸውን በጠንካራ የግንኙነት መስመር ያጣመረ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፤

- ጥሩ የዕውቀት ማኔጅመንት ስርዓት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ይፈለጋል፤
- ሥርዓቱ በቀላሉ የሚተገበርና ለለውጥ ወይም ለመሻሻል እንዲያስችል ሆኖ መደራጀት ይገባዋል፡፡
- ሥርዓቱ በወቅታዊ፣ ትክክለኛ፣ የጠራ፣ እና የተመጠነ የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ሊደራጅ ይገባዋል፤
- እና ሌሎችም.....

t.me/BooksandYou

# የዕውቀት ማኔጅመንት ዘመናት

የዕውቀት ማኔጅመንት ከፍተኛውን የአጠቃቀም ዘይቤን መከተል ከጀመረበት እ.ኤ.አ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ሦስት መሠረታዊ ለውጦች መታየታቸው በስፋት ተዘግቧል፡፡ ይህም የተለያዩ ድርጅቶች የዕውቀት ማኔጅመንትን በየጊዜው እየገመገሙ ክፍታውን እየጨመሩት ለመሆናቸው አንዱ መገለጫ ነው፡፡ እያንዳንዱ የከፍታ ዘመንም ድርጅቶችንና የዕውቀት ሥርዓቱን በፍጥነትና ተወዳዳሪነት በሚታይበት መልኩ እድገትን እንዲሹ አድርጓቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ይህ ሲባል ቀደም ሲል የነበረውን ሥርዓት በሙሉ ገሸሽ በማድረግ ሳይሆን ባለው ላይ ተመርኩዞ በማሳደግ መርህ ላይ መሠረቱን በመጣል እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው የዕውቀት ማኔጅመንት ሳይንሳዊ ቅርፅና ይዘት በመያዝ እ.ኤ.አ. ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እያደገ እንደመጣ በርካታ የመረጃ ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚያ በፊት የዕውቀት ማኔጅመንት ከሥልጠናና ከክህሎት መጐልበት ጋር ተያይዞ በግለሰቦች ብቃት መጐልበት ላይ ብቻ ትኩረት ይሰጥ እንደነበር በርካታ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቆመው ዘመን ወዲህ **"የዕውቀት ሠራተኞች"**፣ **"የዕውቀት ኢኮኖሚ"** እና **"ዕውቀት የአንድ ድርጅት ዋቢ እሴት"** እየተባለ ዕውቀት ከሌሎች ሀብቶች ጋር ሲነፃፀር ተወዳዳሪነቱ ከፍተኛ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን የሚጽፉበትና የሚናገሩበት ሁኔታ ድግግሞሹ እያየለ ለመምጣቱ በርካታ ምስክሮችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መጠቆም ይቻላል፡፡

ከ1990ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ተለይተው የተቀመጡት የዕውቀት ማኔጅመንት ዘመናት እንደሚከለተው ጠቅለል ብለው ተቀምጠዋል፡፡

# በተሞከሮ ላይ የተመረኮዘ ዕውቀት ማኔጅመንት

ይህ የዕውቀት ማኔጀሙንት ሥርዓት ከ1995 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ጀምሮ ጥቅምት ላይ እየዋለ መሆኑ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተሞክሮ ላይ የተመረኮዘ ዕውቀት በሰዎች አእምሮ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መልክ ባልያዙ መልኩ እየተብላላ የቆየ መሆኑ በቀላሉ ጥቅም ላይ ለማዋል አስቸጋሪ እንደሆነ በስፋት ይነገራል፡፡

# የተሞክሮ ዕውቀት ማኔጅመንት

ይህ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት ዘመን እ.ኤ.አ. ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ በስፋት እየተሠራበት ያለ ነው፡፡ በዚህ ዘመን በአመዛኙ ከማኅበረሰብ፣ ቡድኖች እና ከፕሮጀክቶች በሚገኝ ዕውቀት የቡድን ውጤታማነትን የላቀ ለማድረግ ሲባል ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ የዕውቀትና ማኔጅመንት ዘመን የተሞክሮ ወይም የልምድ ዕውቀት ማኔጅመንትን ማዕከል ያደረገ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

የዚህ የዕውቀት ዘመን ወይም ሥርዓት መነሻ ሐሳቡ የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም የዕውቀት ማኅደር በመረጃ ቋት ተቀምጦ

ማንም ሰው ሊጠቀምበት ይገባል የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የተቋሙ ሠራተኞችና ባለሙያዎች የግድ መደበኛ የሥልጠና ጊዜ ተመቻችቶላቸው የተቋማቸውን ሁኔታ እንዲገነዘቡና አውቀው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል የሚል አመለካከት አለ፡፡ በዚህም የተቋሞችን ባህሪ፣ አሠራርና አደረጃጀት በቀላሉ ማስረፅ እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ይህ ዓይነቱ የዕውቀት ማኔጅመንት ቀደም ሲል ከተገለፀው ጋር ሲነፃፀር መነሻ ወጭው ከፍ ያለ እንደሆነ በሰፊው ይወሳል፡፡

የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት የአንድ ተቋም ሠራተኞችና ባለሙያዎች የዕውቀት ምንጮችን ከመጠቀም ባሻገር ሠራተኞችና ባለሙያዎች የዕውቀት አመንጪ በመሆን አዕምሯቸውን አለስልሰው የበኩላቸውን ዕውቀት ማጋራት እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ነፀብራቅ መገለጫው ሠራተኞችም ሆኑ ባለሙያዎች በተቋማቸው የነበረውንና የጐደለውን ለይተው ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን መርጠው እንዲያቀርቡ ያበረታታቸዋል፡፡ ከጽንሰ-ሐሳብ ከፍ ያለ አስተሳሰብ አለ፡፡

ስለሆነም ሠራተኞችና ባለሙያዎች የዕውቀት ግኝታቸው ትርጉም ያለው መሆኑ እየተረጋገጠ በጋራ ወይም በተናጠል ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ ከወዲሁ ግንዛቤ መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ይህን ሥርዓት በሌላ እይታ የሚያዩት ምሁራን እንደሚያስረዱን ደግሞ ሠራተኞች እና ባለሙያዎች በቂ በሆነ መልኩ የዕውቀት አመንጪ በመሆን የድርጅታቸውን እይታ ከፍ እንዲል የሚያደርጉት ጥረት አነስተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩም አንዳንድ ሠራተኞችና ባለሙያዎች ሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው የድርጅታቸውን ገፅታና ይዞታ በትክክል ተገንዝበው የድርጅቱን ልዕልና ለማስቀጠል በሚደረጉ ጥረቶች ተሳትፏቸው የሳሳ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በዚሁ ምክንያት ትምህርት የሚወሰድባቸው ጉዳዮችና መልካም ተሞክሮዎች እንዳይስፋፉ መሰናክል መሆናቸው ይወሳል፡፡ ለዚህ አደናቃፊ ሁኔታ ምላሽ መስጠት የድርጅት ወይም የተቋምን ሕልውና አስጠብቆ ለመጓዝ እንዲቻል ሠራተኞችና ባለሙያዎች ሐሳባቸውን ግልፅና ነፃ በሆነ መንገድ እንዲያቀርቡና እንዲያሸጋግሩት ትኩረት የሚሰጥበት ጉዳይ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም፡፡

# የወል ዕውቀትን መሻት

ይህ ዘመን ከ2010 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የጀመረ ሂደት ሲሆን፣ ድርጅቶች የድርጅታቸውን አጠቃላይ ይዘት በጥልቀት በመገምገም የድርጅታቸውን የወል እውቀት ለመጠቀም ስርዓት መዘርጋት የጀመሩበት ዘመን ሲሆን በተለይ የተለያዩ ምሁራን ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አስተያየታቸውን ጐላ አድርገው የሚያሰሙበትና ሰፋ ያለ ተሰሚነትን ለማግኘት የሚጥሩበት ወቅት ነበር፡፡

በዚህ የዕውቀት ማኔጅመንት ዘመን የተለያዩ ድርጅቶች የወል ዕውቀት ስትራቴጂያዊ እይታ እንዲኖራቸው አበክረው ጥረት እንዲያደርጉ ማስቻሉ ይታወቃል፡፡

የወል ዕውቀት ምንጮች በአመዛኙ አውደ ጥናቶች፣ ስብሰባዎች፣ መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በእነዚህ የዕውቀት ምንጮች የተቋሞችን አሰራርና ድርጅታዊ ወይም ተቋማዊ ጉዳዮች በጋራ ውይይት የጋራ መፍትሔ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው የአንድ ተቋም አመራር ለብቻው ለውስብስብ ጉዳዮችና ችግሮች መፍትሔ ለማምጣት አስቸጋሪ በመሆኑ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የጋራ መፍትሔ ለማምጣት

እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በወል ዕውቀት ላይ ለሚመሠረቱ ውሳኔዎች የአመራሩ ሚና ውይይቱን በመምራት የሚያረካ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ይሆናል፡፡ ይህ የሚጠቁመው ዕውቀት የስብዕና መሠረት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የወል ዕውቀት ጠቃሚነቱ እየጐላ ስለመጣ ማኅበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች ኮምፒዩተር አገዝ መተግበሪያዎችን በመጠቀም ቀልጣፋና ውጤታማ ሥራ እየተተገበረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አዕምሮ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ተደራድረው ለአንድ ተቋም የተሻሉ አማራጮችን በመውሰድ ወሳኝ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ አስተሳሰቦች፣ መልዕክቶች እና ክህሎቶችን ለማግኘት የዕውቀት ምንጮች ወሳኝነታቸው የላቀ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም የዕውቀት ክምችት በየጊዜው እየተሻሻለ ወቅታዊነቱን ጠብቆ መጓዝ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም በሰዎች አእምሮ ውስጥ የተጠራቀመ ተሞክሯዊ ዕውቀት በየጊዜው እየታደሰና እየተሻሻለ መሄድ እንዳለበት መታወቁ እንዳለ ሆኖ በዘፈቀደ የተቀመጠው ዕውቀት ደግሞ እንደሁኔታዎች አስገዳጅነት ወቅታዊነቱ ሊጠበቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በመርህ ደረጃም ሆነ በተግባር ቅኝት ውስጥ

የዕውቀት ማኔጅመንትየሚደረገው በነባሩ ዕውቀት ላይ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ይህም የተቋምን ዓላማና ግቦች እንዲተገበር ብሎም የረጅም ጊዜ ራዕዩ እንዲደረስበት ዋቢ ምሰሶው ዕውቀት መሆኑን ማጤን አግባብነቱን ያጐላል፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ ተቋማዊ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ የሚሆኑት በተሳለጠ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት መሆኑ ትኩረት የሚሰጥበት የአስተሳሰብ ጣሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር የተቀመሩትን ሐሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀጣይ ዘመናት ስኬታማ ኑሮን ማጣጣም የሚችሉት ዕውቀትን ለመቅሰም ማንበብና መጻፍ የሚችሉት ሳይሆኑ ያወቁትንና የተረዱትን ቀምረው እና ችሎታቸውን ተጠቅመው ተግባራዊ የሚያደርጉት ብቻ ናቸው ወደሚል የላቀ አስተሳሰብ በዓለማችን በሚያስደንቅ ሂደት ግንዛቤ እየተሰጠበት መሆኑን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ የዚህ አባባል መሠረተዊ መገለጫው በዘላቂነት ስኬትን ማጣጣም በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሁሉ-አቀፍ ምርታማነት ሲሰፍን ብቻ ነው፡፡ ምርታማነት ሲባል በሚዳሰሱና በማይዳሰሱ እሴቶች ሊገለፅ ይችላል፡፡ ዕውቀትም የእሴቶች ሁሉ ድምር ውጤት ወይም አምድ እንደሆነ እምነት ሊጣልበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በዕውቀት ላይ ያልተመሠረተ ውሳኔ በአመዛኙ አሉታዊ ተጽእኖው ያየለ ይሆናል የሚል እምነትን ያሳድራል፡፡ ለዚህም

ነው ያለ በቂ ግንዛቤ የተወሰነ ጉዳይ ቅጽበታዊ አወንታዊ ውጤት ሊያሳይ ይችላል፡፡ ሆኖም በእጅጉ ሲመነዘር በአሉታዊ ተፅእኖ ሥር መደረጉ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው በቅፅበታዊ ውጤት መዘናጋት በራስ መከራ ሜዳሊያ እንደማጥለቅ ይቆጠራል የሚባለው፡፡

t.me/BooksandYou

# የተቋም ዕውቀት ማኔጅመንት

በመሠረቱ ለዕውቀት ማኔጅመንት በተለይ ለተቋማዊ የዕውቀት ማኔጅመንት ወጥ የሆነ አባባል ወይም ትርጉም መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት ለተለያዩ ሰዎችና ተቋማት የተለየ ስሜትና ትርጉም ይሰጣቸዋል፡፡ ምክንያቱም የዕውቀት ማኔጅመንት እንደአግባቡ ጽንሰ-ሐሳባዊና ተግባራዊ ትርጉም ሊሰጠው ስለሚችል ነው፡፡ አጠቃቀሙ እንደሁኔታው፤ ወይም አጋጣሚዎች አስገዳጅነት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህ ተለያይነትም የግንዛቤ፣ የሚዛናዊ አስተሳሰብና የውሳኔዎችን ደረጃና ዓይነት ለመወሰን ጸጋው የሰፋ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ግለሰቦችም ሆኑ ተቋማት የዕውቀት ማኔጅመንት ድንበር ሊሆኑ አይችሉም የሚል አስተሳሰብን ሊይዝ ይችላል፡፡

ግለሰባዊ ዕውቀትን በተመለከተ ደግሞ ከተቋም እይታ ውጭ ሆኖ የመገኘት ሁኔታው ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ሰዎች ሥራቸውን፣ የኑሮ ዘይቤአቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ባሕላቸውንና እምነታቸውን በተመለከተ ከሌሎች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በራሱ የዕውቀት ማኔጅመንት አካል ነው የሚል አስተሳሰብም በስፋት ይንፀባረቃል፡፡ ይህም ሰዎች ከተቋም ወደ ተቋም ሲዘዋወሩ ልብ ሊሉት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

የተቋም የዕውቀት ማኔጅመንት ከጊዜ ወደ ጊዜ ልዩ ትኩረት እየተሰጠው ያለ ዓለማቀፋዊ ጉዳይ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገራችንም ለዚሁ ጉዳይ እየተሰጠ ያለበት ሂደት ውስጥ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተቋማዊ ግብ ከምንጊዜውም በላይ ለሥራ እና አደረጃጀት ልዩ ዋጋ እየተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ መልኩ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተደራሽነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱና የዕውቀት ጉዳይም በሁሉም የሥራ ወይም የሙያ ዘርፎች ነገረ-ሐሳቡን እንደመልካም ወይም ተመራጭ ቅርስ አድርገው የወሰዱበት አዝማሚያ ተጠቃሽ እየሆነ መጥቷል፡፡ እነዚህ ታሳቢዎችን ዋቢ በማድረግ ተቋማዊ የዕውቀት

ማኔጅመንት ለአንድ ተቋም በስኬት ለመዝለቅ ዋስትና እንደሆነ ግንዛቤን ያስጨብጣል፡፡

ምንም እንኳ የተቋማዊ ዕውቀት ማኔጅመንት አስፈላጊነት አከራካሪ ባይሆንም፤ ስልቶቹ ከቀደምት አስተሳሰቦች ያልተላቀቁ መሆናቸው በዚሁ ሂደት አለፍ-ገደም ያለ አስተዋይ ምስክርነቱን ይሰጣል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችም በአግባቡ ጥቅም መስጠታቸው አጠራጣሪ ነው የሚሉም ጥቂት አይደሉም፡፡

በተነፃፃሪ ሲታይ ከላይ የተቀመጡትን ሐሳቦች እማኝ በማድረግ የተቋም የዕውቀት ማኔጅመንት ራሱን ዕውቀትን በስፋት መመርመር አስፈላጊነቱ ይታያል፡፡ በዚሁ መሠረት የተቋም የዕውቀት ማኔጅመንት ስርዓቱ ተገንብቶ ተቋማዊ ድጋፍ እስኪጠናከር ድረስ በየጊዜው አስፈላጊ ማሻሻያዎች እየተደረጉ ሊቀጥል ይገባል የሚል ሐሳብና ምናብን የሚያቀናጅ አስተሳሰብ አለ፡፡ በሌላ መልኩ ሲፈተሽም የዕውቀት ማኔጅመንት ቁሳዊ ይዘት የሌለው ወይም ቴክኖሎጂካዊ ተፅዕኖው ሁሉ-አቀፍ ያልሆነ ወይም ገዥ-ባሕል አለመሆኑን በተለየ መልኩ ሲገለጽም ይታያል፡፡ ሌሎች ነገረ-ሐሳቦችም የተቋም ዕውቀት ማኔጅመንት ጽንሰ-ሐሳብ ሆኖ ከዕውቀት ማኔጅመንት ዘይቤዎችና

ማስፈፀሚያ መሣሪያዎች ጋር እየተነፃፀረ የሚቀርብ ሆኖ በመግባባትና በፍላጐት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤና ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚያግዝ ሥርዓት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በርካታ መረጃዎች እንደሚጠቀሙት ተቋማዊ ዕውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ብቻ ያልቃል አይባልም፤ ዕውቀት ሲሸጋገር ወይም ከአቀባዩ ወደ ተቀባዩ ሲተላለፍ ሊጠፋ ይችላል የሚል ስጋትም እንደሌለ፤ ዕውቀት በማንኛውም መልክና ይዘት በብዛት ሊኖር ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርስ መንገድም እንዳለ ይተረካል፡፡ ሆኖም አጠቃቀሙ ግን አናሳ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም አንድ ተቋም የዕውቀት ክምችቱ ለተቋሙ ምንም ውጤት ሳያስገኝ ወይም እሴት ሳይጨምር በውል ባልታወቀ ወቅት ወደሌላ አቅጣጫ ተሸጋግሮ ለሌላ ተቋም ወይም ግለሰብ ጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት ጉዳይ ተቋማዊ አሠራርን፣ አስተሳሰቦችን፣ አካሄድን፣ አመራርን፣ ፖሊሲዎችንና መርሆን ለመቁረጥም ሆነ ለዘላቂነት ለማስቀጠል አሳሳቢ ለመሆኑ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

ተቋማት ቀጣዩን ታሪካቸውን አስቀድመው ለማወቅ የዕውቀት ክምችታቸው ዓይንና ጆሮ መሆኑን ተገንዝበው ክምችቱን

መዋቅራዊ አረጃጀት፣ ሰብዓዊ ግብዓትና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አጣምረው የወደፊት ራዕያቸውን በመሳል ተቋማዊ ግቦችን በፍጥነት፣ በጥራትና በብዛት መረከብ እንዲችሉ ሆነው መገኘት እንዳለባቸው ሳይዘገዩ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

ዕውቀት በተቀናበረ መንገድ ተግባራዊ በማይደረግበት ተቋም ውስጥ መቆየት ያቅታል፡፡ የፍትሕ ሚዛን ይዛባል፣ ሠራተኞች ይሰለቻሉ፣ ግራም ይጋባሉ፣ ተስፋን ይዞ መጓዝ ይከብዳቸዋል፡፡ ስለሆነም ሁኔታው የሠራተኛ ፍልሰት ምክንያት ከመሆን አያድንም፡፡

በሌላ መልኩ የዕውቀት ምንጮች የሆኑ ግለሰቦች ወይም የተቋም ሠራተኞች፣ ባለሙያዎች እና አመራሩ ግላዊ ዕውቀቱን እና የሙያ ተሞክሮዎችን ወደ ተቋማዊ ዕውቀት ለማሻገር በተቋም ፍላጐት ላይ ያነጣጠረ የመማማር ሥርዓት መገንባት ቸል የማይባል መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ የተበታተነውንና በዘፈቀደ የሚሸጋገረውን ዕውቀት ምርታማ ከማድረግ አንፃር ፍጹም ተፈላጊነቱ አያጠራጥርም፡፡ ቢቻል አርአያ ወይም ሞዴል ሊሆን የሚችል ተቋማዊ የዕውቀት ሥርዓት መገንባት የተቋምን ተወዳዳሪነት ከማምጠቅ ባሻገር

ተቋሙ ግብ-ተኮር ለመሆኑ ምስክር የማያሻው እንደሆነ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡

ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት በተቋም ደረጃ ሠራተኞችን በሙሉ፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን፣ የሥራ ሂደቶችን፣ እና ተቋማዊ አደረጃጀትን ሆን ተብሎ በሚያሰኝ ሁኔታ አስተሳስሮ ተቋማዊ እሴትን ማዕከል በማድረግ ዕውቀትን ደጋግሞ ጥቅም ላይ በማዋል ፈጠራን ማከናወንን እንደሚያጠቃልል በመገንዘብ መስተጋብሩን ለመተግበር በተለያዩ ደረጃዎችና ሁኔታዎች የሚገለጽ መማማርን፣ ዕውቀት መጋራትን እና አውቆ መተግበርን በተለይ መልካም ተሞክሮን እና ስኬታማ እንቅስቃሴዎችን በተቋም ትውስታ ውስጥ በማካተት የተቋም ወጣ-ገባነትን በውል በማስተዋል ለግብ ስኬት መሮጥ መጀመርንና ሩጫውንም በድል ማጠናቀቅን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ነው በርካታ የተቋም አመራሮች የተቋማቸው ዋነኛ እሴት የሠራተኞቻቸውና የባለሙያዎቹ እንዲሁም የመካከለኛ አመራራቸው ዕውቀት መሆኑን አበክረው የሚገልጹት፡፡ ይህ የሚያሳየን ደግሞ ክቡር የሆነውን የተቋም እሴት ባለቤቶችን በአግባቡና ዕውቀትን ባማከለ አመራር መያዝ አግባብነት ያለው የሥራ አመራር ጥበብ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡

ሆኖም ብዙዎች የተቋም አመራሮች ዕውቀትን ማዕከል በማድረግ የዕውቀት ምንጮችን እንዴት ታስተዳድራላችሁ? ሲባሉ በቀጥታ የሐሳብ አገላለጻቸው ወይም መልሳቸው ወጥነት እንደሌለው ይሰማል፡፡ ይህ የሚያሳየው እጅግ የዳበረ የሆነ የዕውቀት ክምችት በተቋማቸው ውስጥና ዙሪያ እንዳለ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ አመራሩንም ለማሳመን ከቀጥተኛ የሐሳብ አገላለጽ በተጨማሪ ጥልቅና ሰፊ ሐሳቦችን ማንሸራሸር እንዲችሉ በማድረግ ሳይቆጠቡ ንጽጽራዊነትን በሚያንፀባርቅ መልኩ ስለተቋማዊ ዕውቀት ያላቸውን የውሳኔ አሰጣጥ አድማሳቸው እንዲሰፋ ማድረግ መልካም የጉዞ ጅምር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ሲሆን አመራሩ ውስብስብ አካሄዶችን በአንድ በተግባባ መንገድ የሚያስጉዙ እና የሚገዙ የሐሳብ አማራጮችን በማብዛት የዕውቀት ምንጮችን እያጐለበተ ውሳኔዎቹን ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይችላል፡፡ የውጤቶቹንም ፋይዳ በበርካታ ፈርጆች አጣቅሶ መተርጐም ያስችለዋል፡፡

በተጨማሪ የተቋሙ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና መካከለኛ አመራሩ የግንዛቤ ትኩረት መፍቻና የውሳኔ መተግበሪያ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ሕጐችን ሳይስቱ ሥራቸውን እንዲተገብሩ ያግዛቸዋል የሚል የጸና ሐሳብ አለ፡፡

ሌላው የሐሳብ ዘርፍ ደግሞ በልምድ ወይም ተሞክሮ የተገነባ ዕውቀት ባለቤቶቹ በጡረታ ወይም በሌላ አስገዳጅ ሁኔታ ተቋሙን ሲለቁ የሚባክነው ወይም ሊጠፋ የሚችለውን ልዕልና ያለውን ዕውቀት እንዴት ማስቀረትና ተቋማዊ ጠቀሜታውን ከፍ ለማድረግ የሚካሄድበት መንገድ ያልጠራ፤ አንዳንዴም የሌለ መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ይህን የዕውቀት ቀውስ መፍታት ተገቢ ነው፡፡ በጡረታ የሚገለሉ ወይም ተቋሙን ለቀው የሚሄዱ አንጋፋ ባለሙያዎችና አመራሮች ተተኪዎችን በማፍራት በበቂ ሁኔታ አብስለው መሄድ እንዳለባቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተቋማት የግብ ስኬታቸውን ያለምንም ማወላወል እና በሚፈልጉት አግባብ ሊያሳኩት እንደሚያስችላቸው ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

t.me/BooksandYou

# የዕውቀት ማኔጅመንት መሠረቶች

ለዕውቀት ማኔጅመንት አብቂ ወይም አስቻይ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ በርካታ ጉዳዮች በተለያዩ ምሁራን ይጠቀሳሉ፡፡ የእነዚህ አብቂ ጉዳዮች መገለጫቸው የሥርዓቱ ይዘትና ዓላማ ላይ የሚያተኩር ቢሆንም በዋናነት የሚከተሉት አዘወትረው ይጠቀሳሉ፡፡

- የአመራር ብቃት፤
- የዕውቀት ግንባር ቀደሞች፤
- ባህል፤
- ተደራሽነት፤

- ቴክኖሎጂ፤
- መማማር፤
- እና ሌሎችም .....

የዕውቀት ማኔጅመንት አዲስ ከሚባሉት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት ከአንድ የሙያ መስመር የወጣ ሳይሆን የባለብዙ ሙያዎች ውጤት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ስለሆነም ትርጉሙን በአንድ አቅጣጫ ወስኖ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ግን ብዙም ባልተራራቁ በበርካታ የታሪክ ወቅቶች ትርጉሞች ሲሰይሙት ይታያል፡፡

ይህም በዕውቀት ማኔጅመንት ዙሪያ የተለያዩ ሐሳቦች እና አቀራረቦች እንዲንሸራሸሩ በማድረጉ አዎንታዊነቱ የላቀ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ወጥነት የጎደለው ትርጉም ማጣቱ በሐሳቦችና አመለካከቶች ዙሪያ ያልጠራ መስመር እንዳለ ይጠቁማል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ከላይ የተጠቀሰው እንደሚንፀባረቅ አበክሬ ማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለዕውቀት ማኔጅመንት መሠረታዊ ትርጉም ወሰኑ እየሰፋና እየጠራ እንደመጣ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ ሰብዓዊና ቴክኖሎጂካዊ የዕውቀት ማኔጅመንት ልዩነቶችን አበጥሮ ለማቅረብ እንዲያስችል የሙያው ባለቤቶች እጅግ ሰፊ የሆነ ትንተና በማድረግ ወጥነት እንዲሰፍን ያደረጉት ጥረት በእጅጉ የሚደነቅ ነው፡፡ ይህም የዕውቀት ማኔጅመንት ሁሉ-አቀፍ ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርጐታል ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁሉ አቀፍ ግንዛቤዎች በአመዛኙ የዕውቀት ማኔጅመንት ሚዛን የሚያጋድለው በሰብዓዊ የዕውቀት ምንጨታ፣ ሂደትና አጠቃቀም ላይ መሆኑን ሲያስገነዝቡ፤ ቴክኖሎጂካዊ ግብዓቶትም ያልተገደበ ድጋፍ እንዳላቸው ይጠቁማሉ፡፡

የዕውቀት ማኔጀመንት አካሄድ ብዙም ውስብስብ ባይሆንም በተለያዩ ሂደቶች የሚታዩ መዘበራረቆች፣ የባለሙያዎች ልምድና ክህሎት፣ የተቋም አደረጃጀትና ሌሎች ጉዳዮች ፈታኝ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የዕውቀት ማኔጅመንት ሂደቶች እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡፡




ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የዕውቀት ማኔጅመንት ትርጉም በሐሳብ ደረጃ እና አጠቃቀም ዙሪያ የሚከተሉትን ትርጉሞች ያሳየናል፡፡

# የዕውቀት ዑደት እና የአተገባበር ሂደት

ይህሂደትየዕውቀት ማኔጅመንትን በዑደቱ፣ በተቋማዊ ውስብስብነት፣ ኃላፊነት እና አካሄድ ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ እነዚህን ጉዳዮችንም በንዑስ ኃላፊነቶች፣ አካሄዶችና ተግባራት ያያቸዋል፡፡ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት ግብ እነዚህ ንዑሳን

ጉዳዮችን በማሻሻል ተቋማዊ ሽግግርን ማምጣት ላይ ያተኩራል ለማለት ያስደፍራል፡፡

የዚህ ትርጉም መነሻዎቹ ዕውቀትን በማመንጨት፣ በመለየት፣ በማረጋገጥ፣ በመገምገም፣ በመለወጥ፣ አደረጃጀትና ጥምረትን በማያያዝ፣ ተዓማኒነትን በማስፈን፣ ማጣራትን፣ ማሰራጨትን፣ ማስረፅን፣ ማጋራትን፣ ማቅረብን፣ ጥቅም ላይ ማዋልንና የዕውቀት ሂደትን ማስቀጠልን እማኝ በማድረግ ለተቋማዊ ጉዳዮች ሥርዓት ያለው ሰብዓዊና ቴክኖሎጂካዊ አወንታዊ ጣልቃ ገብነትን የሚያቀጣጥል አካሄድና መሣሪያ ነው በማለት ይገለፃል፡፡

ታሪካዊ ሂደቶች እንደሚጠቁሙት ዕውቀት በፈላስፋዎች ዙሪያ ትርጉም ሲሰጠው እንደቆየ ነው፡፡ ለሁሉም በሚያሰኝ ሁኔታ ትርጉሙ ከፍልስፍና ጋር ለዘመናት ተቆራኝቶ መቆየቱን በሚከተሉት አገላለጾች ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡

# የግሪክ ፈላስፋዎች

ሂራክሊተስ፣ ሶቅራጥስ፣ ፕሌቶ እና አሪስቶትልስ የአውሮፓውያንን ብሎም የዓለምን አስተሳሰብ የቀየሩ

ፍልስፍናዎችን በማቅረብ ዕውቀትን እና በዝርዝር ዕውቀት መሻትን አብራርተዋል፡፡ በእነዚህ ፈላስፋዎችና አሁን ባለው አስተሳሰብ መካከል ያለው ልዩነት ቀደምት ፈላስፋዎች ዕውቀት የአንድ አካሄድ ውጤት ሳይሆን ተለያይተው ግን በኅብር በተቀመጡ የሚዳሰሱ፣ ሞራላዊ እና ፖለቲካዊ እሳቤዎች ሳቢያ የሚገኝ ነው ሲሉ፤ አሁን ካለው አስተሳሰብ ለየት ያደርጋቸዋል፡፡ የእነዚህ ፈላስፋዎች ሌላው መለያቸው ደግሞ በተጨባጭ ሁኔታዎች ወይም የገሃዱን ዓለም በተለያዩ ዘዴዎች በመመልከት፣ በመፈተሽ፣ በመተንተን እንዲታወቅ ማድረግ ይቻላል ማለታቸው ነው፡፡ ስለሆነም እውቀት የገሃድ ዓለሙ ነፀብራቅ ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች የዚያኛው ዘመናት ውጤቶች መሆናቸውን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

ሶቅራጥስ በዕውቀት ዙሪያ ካበረከታቸው አባባሎች ጥቂቶቹን እንጥቀስ፡-

- የእውነተኛ ዕውቀት ብቸኛው መገለጫ አለማወቅን ማወቅ ነው፤
- ያልተፈተሸ ሕይወት እንዳልተኖረበት ይቆጠራል፤

- ሁሉንም ነገር ማስተማር አልችልም፤ ሰዎችን ግን እንዲያስቡ ማድረግ እችላለሁ፤

- መገረም የዕውቀት መጀመሪያ ነው፤

- ጠንካራ ሰዎች ሐሳቦችን ይመረምራሉ፤ መካከለኛዎቹ ሁኔታዎችና ክሥተቶች ላይ ይወያያሉ፤ ዝቅተኛዎቹ ደግሞ ሰዎች ላይ ሲወያዩ ጊዜያቸውን ያባክናሉ፤

- ከሀብት በላይ ዕውቀትን ምረጥ የፊተኛው ቀሪ የኋለኛው ቀጣዩ ስለሆኑ፤

## አብዮታዊአስተሳሰብ

በ17ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ሲል የነበሩ የዕውቀትና የእምነት አቻነትን በመተቸት በዕውቀት ላይ ትኩረት የሚሰጡ ራሽናሊዝምና ኢምፕሪሲዝም የተባሉ አዲስ የፍልስፍና ዘውጎችን ጀባ ማለታቸው በታሪክ ተመዝግቧል፡፡ ይህም አስተሳሰብ የኢንዱስትሪ አብዮት እየተባለ በሚጠራው ዘመን እና የሶሻሊዝምና ኮሙኒዝም ፍልስፍናዎች ከማቆጥቆጥ ወደ ተቆጣጣሪነት በተሸጋገሩበት የታሪክ ዘመን ሚናቸው የጐላ እንደነበር የተለያዩየጽሑፍ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

# ባለብዙ ፈርጅ ዕይታ

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስፍናን ማዕከል ያደረጉ አስተሳሰቦችም ታይተዋል፡፡

*ለምሳሌ፡-* አወንታዊነት በሚለው ዘርፍ ዕውቀት ነገሮችንና ሁኔታዎችን በመመልከትና በመፈተሽ ይገኛል የሚል ሲሆን፣ ሁኔታዎችን በመመልከትና ምልከታ በተደረገበት ሁኔታ መካከል ያለውን ጥግነት፣ ርቀት ወይም መሳሳብ ላይ ያተኩራል፡፡

*ለምሳሌ፡-* በተቋምና በከባቢው መካከል ያለውን ልዩነት በማመንጨት ልዩነቱ የዕውቀት መስኰትነቱን ያሳያል ማለት ነው፡፡

## ግንባታዊ

ይህ የፍልስፍና ዘርፍ ሁሉም ዕውቀት በአዕምሯችን ውስጥ የተፀነሰ መሆኑን ያብራራል፡፡ የገሐዱ ዓለምን የዕውቀት መሠረትነትንም ይተቻል፡፡

## ዋቢ ፅንሰ ሐሳብ

ይህ አስተሳሰብ ነባራዊ ወይም ባህላዊ የዕውቀት ወሰንን የሚተች ሲሆን፤ መነሻውም ቀደም ያሉ አስተሳሰቦች የኅብረተሰቡን እና የሳይንስን መስተጋብር ከግምት ውስጥ ያስገቡ ባለመሆኑ እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል፡፡

## ተጨባጭነት

ይህ የዕውቀት አተናተን ንድፈ-ሐሳብ ዕውቀት ከተሞክሮ የሚመነጭ ሲሆን መሠረቶቹም የተፈጥሮ ሳይንስና የሒሳብ ትምህርት መሆናቸውን ያብራራል፡፡

## ማኅበራዊነት

የዚህ የአስተሳሰብ መንገድ አቀንቃኞች ደግሞ ዕውቀት በማኅበረሰቡ ተሳትፎ የሚፈጠር ነው ይላሉ፡፡ ዕውቀትን አስመልክቶ ከላይ በአጭሩ የቀረቡት ዕውቀትንና የዕውቀትን ማኔጅመንት ትርጉም እንዲኖራቸው በማድረግ እጅግ የላቀ አወንታዊ ተፅዕኖ እንዳላቸው መረዳት ይገባል፡፡ አስተሳሰቦቹ አሁን ላለውና ወደፊትም ሂደቱን ተከትሎ ለሚሰጠው የዕውቀት ትርጉም የመወዳደሪያ መድረክ ሆነው እንደሚያገለግሉ መገመት

ይቻላል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ዕውቀትንና የዕውቀት ማኔጅመንትን አስመልክቶ ሁሉን የሚያረካ ትርጉም ይኖራል የሚል አቋም ሊያመጣ ባይችልም አብዛኛውን ሰው ሊያግባባ የሚችል ጽንሰ ሐሳባዊና ተሞክሯዊ ትርጉም ግን እየተፈጠረ ለመሆኑየባለሙያዎች ትንተና ያስረዳል፡፡ ይህም በዘርፉ ሰፊና ጥልቅ ምርምር መካሄድ እንዳለበት ተስፋ ይሰጣል፡፡

የዕውቀት ማኔጅመንትን በተናጠል ማየትና መተንተን አግባብነት የለውም ይባላል፡፡ ምክንያቱም ማወቅ በተለያዩ ክሥተቶች ይገለፃል ተብሎ ስለሚታመን፡፡ ዋና ዋናዎቹ የማወቅ/የዕውቀት መከሠቻዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

- **መኖር፡-** ዕውቀት በቋንቋና በቴክኖሎጂዎች መስተጋብር ውስጥ በመተባበርና በመቆጣጠር ዙሪያ ሊከሰት ይችላል፤
- **መታዬት፡-** እውቀት በጊዜ፣ በቦታ እና በአጋጣሚ ሊከሰት ይችላል፤
- **ሲሳይ፡-** እውቀት ይገነባል በተቀጣይነትም ያድጋል፤
- **ተጨባጭ፡-** እውቀት ዓላማና ተጨባጭነትን ያማከለ ነው፤

- **መፎካከሪያ፡**- እውቀት ለዝና እና ለታዊቂነት መፎካከሪያ መድረክ ነው፤
- እና ሌሎች.....

ስለሆነም ስለዕውቀት ማኔጅመንት ሲወሳ ነገሮችን በተናጥል አይቶ ከመፍረድ ወይም ከመፈረጅ በፊት ዙሪያ-መለስ ምልከታዎችና ትንተናዎች በተገቢው ቅርፅና ይዘት ማካሄድ ተገቢ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## ሁሉ አቀፍ ዕውቀት

የዚህ የዕውቀት ዘርፍ መሠረታዊ ጭብጡ ግምገማን፣ ሐሳብን እና ትንበያን ማካተቱ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ሌሎች ዘርፎች በዋናነት መረጃ ላይ ብቻ ትኩረት መስጠታቸው ከዚህኛው ይለያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የዕውቀት ሥርዓት የተለያዩ ምንጮችን በአማኝነት ማካተት ይኖርበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ልዩ ልዩ ዶኩመንቶችን፣ መልዕክቶችንና የመሳሰሉትን ቢያካትት ጠቃሚ የዕውቀት ምንጮችን ሊያስጨብጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት ነባሩን የተቋም የመረጃ ሥርዓት ማዕከል አድርጎ ሊጐለብት ወይም ሊመሠረት ይችላል፡፡

# የዕውቀት ተቋማዊ ሚናዎች

ዕውቀት በአንድ ተቋም ላይ የሚኖረው በጐ ተፅዕኖ በስፋትና በጥልቀት ቢገለፅ የበለጠ ግንዛቤን ከማምጣት በተጨማሪ የተቋሙን ሕልውና ከመወሰን አንፃር የራሱ የሆነ ዐቢይ ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ እስቲ በዋናነት ይጠቀሳሉ የሚባሉትን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

- ዕውቀት ተቋማዊ ለውጥን ለማምጣት ወሳኝ ነው፤

- የአንድ ተቋም ሠራተኞች ባለሙያዎችን አመራር ለተቋሙ ስኬት የሚያቀርቧቸው ሐሳቦች እና ፈጠራዎች አዳጊ ብቻ ሳይሆኑ የተቋሙ የደም ሥር መሆናቸው ተቋሙ እምነት እንዲጥልባቸውና የለውጡ እንቅስቃሴነታቸውን አምኖ መቀበል ይገባዋል፡፡ በዚህ ሂደት የዕውቀት ምንጮችን በተገቢው መንገድ እንዲደራጁ ወጥና ቀጣይነት ያለው ሥርዓት መገንባት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም በመልካም አስተሳሰብ ሲቃኝ የተቋሙን የዕውቀት አባወራዎችን የዕውቀት እና የብቃት ማረጋገጫ ወይም መግለጫ እንዲያዘጋጅ የማያስገድዱ ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ በቅድሚያ እና በአርቆ አስተዋይነት የተቋሙ እሴት እንዲሆኑ ጥረት ይሻል፡፡

በሌላ መልኩ ሲታይ ዕውቀትን ማዕከል ያደረገ ተቋማዊ ለውጥ የሚያሳየው የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት በትኩረትና በጥራት ሲከናወን ውጤቱ የተሳካ እንደሚሆንና ጐታች የተቋም ባህል ለውጡን መሸከምና መጓዝ እንደሚያስችለው ያሳያል፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይ የዕውቀት ማኔጅመንት ከላይ ወደታች ሳይሆን ከሁሉም የተቋሙ አቅጣጫ ተግባራዊ እንደሚሆንና ውጤቱም የላቀ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ይህ የሚጠቁመው ሌላው ቁም ነገር የዕውቀት ግንባር ቀደሞች በብዛትና በጥራት እንዲገኙ የተቋም አመራረሮች ልዩ ትኩረት ሊሰጡበት እንደሚገባ ነው፡፡ ይህም ቀጣይነት ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሆኑ ታምኖበት በዕቅድ ተመርቶ አተገባበሩም ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ እየተደረገበት ወደፊት ሊባልበት ይገባል፡፡

ዕውቀትን በተለያዩ ፈርጆች ማስቀመጥ ለዕውቀት ማኔጅመንት ተጨማሪ ጉዳዮችን ከመሻት አንፃር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ይህም የተለያዩ ተቋማትን ባሕሪ አንጥሮ ለማውጣት ይጠቅማል፡፡ በዚሁ መሠረት ዕውቀት ተቋማት አደረጃጀታቸውንና አሠራራቸውን በመፈተሽ ለመሻሻል አማራጮችን ከማቅረብ አንፃር አስፈላጊ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ የማሻሻያ አማራጭ ምንጮችም ግለሰባዊ ወይም የወል ዕውቀት እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም፡፡

ዕውቀት ለተቋም እድገት ካለው ጠቀሜታ አንፃር ሲታይ ይዘቱ የሰዎችን አዕምሮ ከሚገምተው ጋር ተያይዞ ምልከታዎች ትርጉም ባለው መልኩ ተሰባስበውና ተደራጅተው ከተሞክሮ ጋር በመቀናጀት ግለሰቦችና የተቋም ባልደረቦች በቀላሉ ሊጠቀሙባቸው በሚያስችል ሁኔታ ለተቋም መሻሻል ድርጊቶችን የሚለዩበት፣ የአደረጃጀትና የሥራ ባሕሪያትን የሚቃኙበት ብሎም የማሻሻያ መርሐ-ግብሮችን በቀጣይነት እንዲካሄዱ ሆኖ ተደራሽ ሊሆን ይገባል የሚል ሰፊ ትንታኔና ትርጉም ይሰጠዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የዕውቀት ማኔጅመንት ትርጉሞች ሁሉም የሚዛመዱት ከተቋማዊ ትውስታዎች በመነሳት የአካሄድ መሻሻያ አማራጮችን ከማፍለቅ አንፃር እንደሆነ ሰፊ ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡

# የዕውቀት ኦዲት

የዕውቀት ኦዲት ማለት የአንድንተቋም የዕውቀት አቅም መገምገም ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ግምገማ ተቋሙ በይዞታው ያለውን የዕውቀት አቅም በመለየትና ለወደፊቱም የሚያስፈልገውን በማየት ክፍተቶችንና ሽንቁሮችን ለይቶ ለማስቀመጥ ባለውለታነቱ ይጠቀሳል፡፡ ስለሆነም ተቋማዊ የዕውቀት ኦዲት ከተቋሙ ስትራቴጂ መነሻነቱን ያጠነጥናል፡፡ ከስትራቴጂ ዕቅዶችም ነባራዊና ዘላቂ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን፣ ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚዎችንና ፈተናዎችን በቀላሉ ለመለየት እገዛው ከፍ ያለ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ ተቋሙ አሁን ያለበትን ደረጃ፣ ወደየት መቀጠል እንደሚኖርበት እና የሚደረስበትን ደረጃ በምን ዓይነት መንገድ መጓዝ እንደሚገባው ማጤንን ዋቢ ያደርጋል፡፡

የዕውቀት ኦዲትን ለመተግበር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

- ዕውቀት ጥልቅ ትንተና ይሻል፡፡ በተለይ ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚዎችን በመመሥረት የተቋም የዕውቀት ኃይል ሊሳልና ሊተነተን ይገባዋል፡፡ ይህም ተቋሙ ምን ዓይነት

የዕውቀት መሠረቶች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ አንድ እርምጃ ያስኬደዋል፤

- ዕውቀት የእሴት ትንተናን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የሰዎችን አዕምሯዊ ዕውቀትና ፊዚካላዊ የዕውቀት እሴቶችን በተለይ ዶክመንቶች፣ ዳታ፣ ድረ-ማዕከላትን፣ ወ.ዘ.ተ. ለይቶ መገንዘብና ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ሙያዊ ቀረቤታቸውና ልምዳቸው የዳበረ ሠራተኞችን፣ ባለሙያዎችንና አመራሮችን በልዩነት መርጦ መጠቀም አዋቂነት ይሆናል፤

- ዕውቀት የፍሰት ትንተናን ይፈልጋል፡፡ በአንድ ተቋም የዕውቀት መሠረቶች ፍሰት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህም የዕውቀት ተደራሽነትን በግልጽ ለማየትና እንደአስፈላጊነቱ የፍሰት እርምጃዎችን በማድረግ ተቋማዊ ዕውቀት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ተቋማዊ ዕውቀትንም በቀላሉ ለማሸጋገርና ለመጋራት ጐዳናውን ግልጽ ያደርጋል፡፡ ተቋማዊ ሽግግርንም ለማሳለጥ ይረዳል፡፡

ጠቅለል ብሎ ሲታይ የዕውቀት ኦዲት ዕውቀትን በስትራቴጂያዊ ዕይታ ውስጥ አካቶ በማየት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ በመሠረቱ የዕውቀት ስትራቴጂያዊ ግምገማ ተቋማዊ ዕውቀቶች መቼ፣ እንዴት፣ በማንና ለምን መጠቀም እንዳለብን ዋቢ ጠቋሚ እንደሆነ መረዳት ይገባል፡፡

ለዚህም ነው የዕውቀት ኦዲት መገለጫው የተቋምን የዕውቀት ጸጋ በግልጽ መረዳት ነው የሚባለው፡፡

ከዕውቀት ኦዲት ጋር በተያያዘ የዕውቀት ካርታ ወይም ማፐጽንሰ-ሐሳባዊና ተተግባሪ ገለፃዎችን በአጭሩ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

# የዕውቀት ካርታ/ማፕ

የዕውቀት ካርታ/ማፕ መሠረታዊ ጠቀሜታው በአንድ ተቋም የሚታዩ የዕውቀት ክፍተቶችን በመለየት ለቀጣይ አማራጮች ሰፊ በር መክፈት ነው፡፡ በመሆኑም የዕውቀት ካርታ ከፍተኛ ደረጃ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተቋማዊ የዕውቀት መሠረቶችን ማዕከል ያደርጋል፡፡ ከዚሁ በመነሳት ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ተቋማዊ የዕውቀት መሠረቶች እንደሚከተለው ባጭሩ ሊገለፁ ይችላሉ፡፡

***መሠረታዊዕውቀት***

ይህ ዓይነቱ ተቋማዊ ዕውቀት ባልደረቦች ሊይዙት የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

**የላቀዕውቀት**

ይህዕውቀት አንድን ተቋም ተወዳዳሪና ዘላቂ እንዲሆን የሚያስችል ኃይል እንዳለው ይታመናል፡፡

**ፈጠራዊዕውቀት**

ይህ ዕውቀት አንድን ተቋም ከተፎካካሪዎች በላይ ልቆ እና አይሎ እንዲገኝ ለማድረግ ያስችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ስለዚህ ተቋማት እነዚህን መሠረታዊ ዕውቀቶች ለይተውና ተገንዝበው ውስጣዊ ይዞታቸውንም በጥሞና አጢነውና ሁሉም የተቋሙ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሮች ሰፊና ጥልቅ ከግንዛቤ በመውሰድ የተቋሙን ስትራቴጂያዊ ግቦች በቀላሉ፣ በአጭር ጊዜ እና በበቂ ሁኔታ እንዲደረስባቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ስትራቴጂያዊዕውቀት ማኔጅመንት

ስትራቴጂ የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ መነሻ ቢኖረውም፣ የቃሉ አጠቃቀምም ከውትድርና አመራር ጋር የተያያዘ መሆኑ በበርካታ የመረጃ ምንጮች ተጠቁሟል፡፡ ቀስ በቀስም አጠቃቀሙ አሁን

ወደተለመደው እና በቀላሉ ሲገለጽ አንድን ዓላማ ለማሳካት የሚዘጋጅ ተግባራዊ ዕቅድ የሚለውን ይዟል፡፡

የዕውቀት ማኔጅመንትን በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ውስብስብ መሆኑ ይበልጥ እየጐላ መምጣቱን ነው፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንት ውስብስብነት ከማኅበራዊ ለውጦች፣ ከተቋማት አወቃቀርና ለውጥ እንዲሁም ከተለያዩ በሥርዓት ከሚገዙ ሁኔታዎችና አደረጃጀቶች በተለይ ደግሞ ከግለሰቦች በዕውቀት ዝግጁነት መለያየት ጋር የጠራ ግንኙነት እንዳለው ግንዛቤ መውሰድ ግድ ይላል፡፡ ስለሆነም ስትራቴጂያዊ የዕውቀት ማኔጅመንት በተወሰኑ መሠረታዊ መርሆች ዙሪያ እንደሚያጠነጥን በግልጽ ይታወቃል፡፡የዕውቀት ባሕል በተለይ በሰዎችና በተቋማት መካከል የሚኖር የዕውቀት መጋራት እና የአመራር እሴቶችን በውል ማጤንናለተግባር ዝግጁ መሆንን ያካትታል፡፡ ለበለጠ ግንዛቤ የሚከተሉትን መርሆዎች ለግንዛቤ እንመልከት፡፡

## ዕቅድ

በውል የታወቁ የዕውቀት ምንጮች ቀጣይነት ኖሯቸው ወደተግባር እንዲሸጋገሩና የተቋም ሽግግርን ለማምጣት እቅድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የዕውቀት ምንጮቹም ለውጥ

አብሣሪነታቸው ቀጣይነት እንዲኖረው ተለይተውና ተደራጅተው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም በተሟላ ዝግጁነት የተዘጋጀ ዕቅድ የአንድ ተቋም መለያው ሆኖ ሊታይ ይገባል፡፡

## ሂደቶች

በተለይ ስትራቴጂያዊ መርሆች፣ ሂደቶች፣ ትግበራና መልዕክቶች በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የዕውቀት ማኔጅመንትም ለሥራ አመቺ በሆነ መልኩ ሊደራጅና ሊቀጥል ይገባል፡፡ለዚህም በዕውቀት ማኔጅመንት የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሂደት አካላት የሆኑት ሁሉ በግልጽ ሊቀመጡ ይገባል፡፡

## ውጤቶች

የዕውቀት ምሰሶዎች ሁሉ ለስትራቴጂያዊ የዕውቀት ማኔጅመንት ተለይተው እንደአግባብነታቸው ለተቋም ለውጥ አጋዥ እንዲሆኑ ማገዝ ተገቢ ይሆናል፡፡ እነዚህ ምሰሶዎች በጥናትና በምርመራ የሚገኙ የግምገማ ውጤቶችንም የሚጨምሩ ናቸው፡፡

## አፈጻጸም

የተቋምን ውጤታማ አፈጻጸም ለማገዝ፣ የተሞክሮ ዕውቀቶችና ክህሎቶች ተወዳዳሪ ለውጥን እውን ለማድረግ ጠቀሜታቸው

የላቀ ነው፡፡ ስለሆነም አግባብነቱ በተጠበቀ መንገድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## ሰዎች

የተቋም ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሮች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች፣ የዕውቀት ደረጃዎችና ዝግጁነት አንፃር እና የአመራር እሴትን ከማጐልበት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ዋልታዎች ናቸው፡፡ በተለይ ዕውቀትን ስትራቴጂያዊ በሆነ መልኩ ለማሳለጥ እጅግ ወሳኞች ናቸው፡፡ ስለሆነም ዕውቀትን በስልታዊ መንገድ ለመምራትና አሳልጦ ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር ሰዎች በተቻለ መጠን ግንዛቤያቸው እንዲጐለብት ማድረግ አማራጭ የሌለው ስትራቴጂያዊ ጉዳይ ነው፡፡

ተጠቃሎ ሲታይ ስትራቴጂያዊ የዕውቀት ማኔጅመንት ከፍ ብለው ከተጠቀሱት መሠረታዊ ሐሳቦችና ትግበራዎች ጋር ተጣጥሞ መዳዝ ያለበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በአካሄድ ደረጃ በተቋማት መካከል ልዩነቶች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የዕውቀት ምንጮቹ የሚታለምላቸው የትግበራ አቅጣጫና አፈጻጸም ከሚጠበቀው የግብ ስኬት አኳያ ልዩነት ሊያመጣ ስለሚችል ነው፡፡ ለዚህም ነው የተለያዩ ተቋማት የራሳቸውን

የዕውቀት አጠቃቀም እና አያያዝሥርዓት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል የሚባለው፡፡

# የዕውቀት ሽግግርና መጋራት

የዕውቀት ሽግግር የመልካም ሐሳቦች፣ የምርምር ውጤቶች እና ክህሎቶች ከተለያዩ ተቋማት ወደ ኅብረተሰቡ በማድረስ የፈጠራ ሥራን፣ አዳዲስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ማስቻል" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ለማጠቃለል ተሞክሯል፡፡

ለዕውቀት ሽግግር የዕውቀት ክምችት፣ አደረጃጀት፣ ተደራሽነትና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የተለያዩ አካሄዶች መኖራቸው በስፋት ይጠቀሳል፡፡ እነዚህንም አካሄዶች ነባራዊና ዘመናዊ ብሎ መለየት ይቻላል፡፡

**ነባራዊ አካሄዶች እንደሚከተለው ይገለጻሉ፡-**

- ከጽሑፍ ምንጮችና ከምስሎች ማግኘት፤

- ከመጻሕፍት ማውጫዎችና ቅንስናሾች (አህጽሮተጽሑፎች)፤

- ከሰዎች አዕምሮ፤

- ከላይ የተጠቀሱትን በቅንጅት መጠቀም፤

- እና ሌሎችም.....

## ዘመናዊ አካሄዶች ደግሞ

- ከዘመናዊ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ማዕከላት፣ ገጾችና ኔትወርኮች፤

- በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ያለን ዕውቀት በዘመናዊ መሣሪያዎች መጠቀም፤

- የዕውቀት ምንጮች በርካታና ውስብስብ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ጥቅሙንም እጅግ በጣም ውጤታማ ማድረግ በሚያስችል ዘመናዊ አካሄድን መጠቀም ተገቢነቱን አጉልቶ ያሳያል፡፡

ዕውቀትን በማንኛውም ጊዜ፣ ሁኔታና መጠን ማሸጋገር ይቻላል፡፡ ሆኖም የሚሸጋገረው ዕውቀት በግለሰቦች መካከል በተለያዩ

ሁኔታና መጠን ቅበላን ሊያገኝ ይችላል፡፡ ለዚህም ይመስላል በርካታ ምሁራን **“ሰዎች የሚያቁውትን ብቻ ናቸው”** የሚሉት፡፡ ለዚህም ነው የተሸጋገረ ዕውቀት አተገባበሩ ለየቅል በመሆኑ ይህን ለማላቅ በርካታና ተከታታይ ማስገንዘቢያ መድረኮችን ማዘጋጀት በተወሰነ መልኩ ተገቢ ነው የሚባለው፡፡ በተጨማሪም በተሞክሮ አካሄድ ዕውቀትን ለማሸጋገር ልዩ ልዩ የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ ተመራጭ እየሆነ የመጣው፡፡

ከላይ በቀረበው ዙሪያ የሚከተሉትንመግለጫዎች እንመልከት፡-

- ሰዎች ሥራ እንዲሠሩ ከማዘዝ በፊት ሥራውን አጥብቀው ማወቃቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፤

- የሚሸጋገረውን ዕውቀት ግልጽና ተዓማኒ መሆኑን መገንዘብ የዘወትር ጉዳይ አድርጎ ማየት ይገባል፤

- ሁሌም በዕውቀት ውስጥ አንቂ፣ አቀጣጣይ፣ አስፈፃሚ፣ አያያዥ፣ አስቻይ የኃይል ጸጋ እንዳለ መረዳት ጥሩ ተሞክሮ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ባለፉት በርካታ ዓመታት በዕውቀት ሽግግርና መጋራት ዙሪያ በተለያዩ የሙያ መስኮች በርካታ ጽሑፎች መታተማቸው

ይታወቃል፡፡ እነዚህ ጽሑፎች የተለያዩ ዝርዝርና ጠቅለል ያሉ ጉዳዮችን ይዘው ታዳሚያንን ሲያከራክሩ፣ ሲያወያዩና የዕውቀት ምንጭነታቸውን ሲያስመሰክሩ ቆይተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ፅሑፎች ለዕውቀት ማኔጅመንት፣ ሽግግርና መጋራትን ለማቀላጠፍ ጠቃሚ ናቸው ያሏቸውን አማራጮች አቅርበዋል፡፡ እነዚህ አማራጮች እንደ አግባብነታቸው ተገቢውን የትግበራ መስመር እንደያዙ ብዙም ጥርጣሬ የለኝም፡፡ በተለይ ለዕውቀት ይዘቶች ግልጽና ተዓማኒ መሆን እየተሰጠ ያለው ምክር ከፍተኛውን ሥፍራ ይዟል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ለዚህም በርካታ መሠረታዊ ጽንሰ-ሐሳቦች መካተታቸው የዕውቀት ማኔጅመንትን ተገቢነት በጉልህ ያወጣዋል፡፡

በርካታ የሙያው ባለጸጐች እንደሚሉት የዕውቀት ሽግግርና መጋራት ቢያንስ በጽንሰ-ሐሳብ ደረጃ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ትርጉም እየተሰጣቸው በበርካታ ሪፖርቶችና ትንተናዎች እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡ በሌላ መስመር ደግሞ ልዩነታቸውን ለማስገንዘብ ጥረት ሲደረግ ይታያል፡፡ እስቲ በልዩነታቸው ላይ ስላለው አስተሳሰብ ጠቅለል ተደርጐ የቀረበውን እንመልከት፡፡

በግለሰቦች፣ በቡድኖች እና በተቋማት መካከል የዕውቀት መጋራት የዘወትር ተግባር ነው፡፡ የዕውቀት መጋራቱ ግልጽ የሆነ

ወይም ግልጽነት የሚጐድለው ሊሆን ይችላል፡፡ ቀደም ብሎ የተቀመጠለት ዓላማም ላይኖረው ይችላል በማለት ስለ ዕውቀት መጋራት ከበርካታ ጽሑፎች አዳቅዬ ያወጣሁት ከላይ እንደተገለጸው ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል በርካታ ጽሑፎች እንደሚሉት የዕውቀት ሽግግር በሁለት ወገኖች መካከል ሲካሄድ አንደኛው ወገን ዕውቀት አቀባይ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ዕውቀት ተቀባይ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ተቀባዩ ለራሱ በሚያመች ወይም በገባው መጠን ተርጐሞ ሊጠቀምበት ይችላል ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ይቻላል፡፡

ከላይ የቀረበውን መሠረት በማድረግ የዕውቀት ሽግግርን አስመልክቶ ያለው ልዩነት ግልጽ የሚሆንባቸውሲመረመር፤ የዕውቀት ሽግግር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በግለሰቦች፣ በቡድኖችና በተቋማት መካከል ግብቡነትን ለመፍጠር ጥረት የሚደረግበት መስመር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ መነፅር ሲታይ የዕውቀት ሽግግር ባለአንድ መስመር (ግልብ መስመር) ግንኙነት ላይ ማተኮሩ ሌላውመገለጫው ነው፡፡ ስለሆነም ተቀባዩ አዕምሯዊ ግንዛቤ ያለው እና ዕውቀትን ተግባራዊ ማድረግ የሚችል ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

በዕውቀት ሽግግርና መጋራት ላይ ያሉ ልዩነቶችን ደግሞ በተለያዩ አይታዎችና ደረጃዎች ያስቀምጧቸዋል፡፡ የዕውቀት ሽግግር እና መጋራት በግለሰቦች ላይ ብቻ ያተኰረ መሆኑ ወይም ተቋማትን ያማከለወይም ያላማከለ፣ ግልጽነት የጐደለው፣ አንዳንዱም ግልጽ ሊሆን የሚችል፣ ዕውቀትን መጋራት አለመቻሉና ስለመቻሉ እንዲሁም አካሄዱ ቀጥታዊ ወይም ግልብ መስመራዊ በመሆኑና ባለመሆኑ ተብለው ሲከፈሉ ይታያሉ፡፡

ከፍ ሲል የተገለጹትን ከግምት ውስጥ በማስገባትና ውዥንብርን ከማስወገድ አንፃር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተቻለ መጠን የዕውቀት ሽግግርንና መጋራትን በተመሳሳይነት በመውሰድ፣ አንዳንዴም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለየት በማድረግ ጥቅም ላይ ለማዋል እንደተሞከረ አንባብያን ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ምናልባት በግለሰቦች መካከል ሲሆን የዕውቀት መጋራት፣ በቡድኖች እና ተቋማት ሲሆን ደግሞ የዕውቀት ሽግግር የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ቀለል ያለውን የዕውቀት ሽግግር ትርጉም እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

በመሠረቱ ከላይ የቀረበው የዕውቀት ሽግግር ቀለል ያለ ትርጉም ምንጩ “**የመረጃ ልውውጥ**” ከሚለው ሰፊና ግልፅ ጽንሰ-ሐሳብ

መሆኑን ግንዛቤ ይወሰድበት፡፡ ሰዎች መረጃን ወደ ጠቃሚ እሴት ሲቀይሩትና ሲጠቀሙበት ዕውቀት መሆኑን ደግሞ በይበልጥ መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለሆነም አንዳንዱ ዕውቀት የራሱ ጠቀሜታ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ቀደምት ወላጆቻችን እንደሚሉት **"ዕውቀት በእጅና በደጅ"** ይገኛል፡፡ እኛ ደግሞ ይህን ዕውቀት በወጉ ይዘን መጠቀም ይገባናል ብንለውስ? በሌላ አባባል በዕውቀት ሽግግር ጊዜ ድንበሮቹ ከሞላ ጐደል ደመቅ ብለው ይታያሉ፡፡

የተቋም አደረጃጀት እና ሥራ በሚፈቅደው መሠረት ዕውቀት በሥራ ዘርፎች ተደራጅቶ ይቀመጣል፡፡ ይህ ዕውቀትን በመጠኑም ቢሆን በድንበር የተካለለ ያስመስለዋል፡፡ ሆኖም ተቋማት የሥራ ዘርፎቻቸውን የዕውቀት ማኅደር (የሰው ሀብቱን ጨምሮ) አቀናጅተውና አጣጥመው ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ ይህም በተቋም ደረጃ ዕውቀትን ለመጋራት ሁነኛ አካሄድ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህ ሁነኛ ጉዳይም የተጠናከረ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት ወሳኝነቱን በድጋሚ ቢገለጽ የበለጠ ግንዛቤ ያስጨብጣል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ምክንያቱም የተቋም ግብ-ተኮር ውጤታማነት መነሻው የዕውቀት ምንጮችን በሚገባ ለይቶ መጠቀምን ማዕከል ማድረግ ስለሚገባው ነው፡፡

የተለያዩ አገራት የዕውቀት ሽግግር በኢኮኖሚ ልማታቸው ውስጥ የራሱን ሚና እንዲጫወት በሰፊው ትኩረት ይሰጡታል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም ልማቱ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ የዕውቀት ሽግግርን በዋና አገራዊ ተልዕኮነት እያራመደ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ብዙዎች እንደሚስማሙበት የእውቀት ድንበር የለውም፡፡ ምናልባት ድንበሩ በአቀባዩና በተቀባዩ መካከል ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብም ይቻላል፡፡ በእውቀት ሽግግር ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ለሽግግሩ ውጤታማነት ተግተው መሥራት እንዳለባቸው ቆም በማለት ሊያጤኑት ይገባል፡፡ በዚሁ መሠረት ሽግግሩ የተሳካ እንዲሆን

- ዕውቀት አቀባዮችንና ተቀባዮችን መለየት መቻል አለባቸው፤
- የትብብር መስካቸውን ማስፋት ይጠበቅባቸዋል፤
- በሽግግሩ ሳቢያ ሊታዩ የሚችሉ ፋይዳዎችን አስቀድመው ማጤን ይኖርባቸዋል፤
- ዕውቀትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀበል ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፤

- እና ሌሎችም ....

እንደሚታወቀው አንድ መርሐ-ግብር ወይም ፕሮጀክት ሲጠነሰስ የሚጠበቀውን ውጤት አስቀድሞ መተንበይ ይቻላል፡፡ ጥንስሱ ሲተገበር የተለያዩ አደናቃፊ ሁኔታዎች ሊከሡቱ እንደሚችሉ አስቀድሞ መገንዘብም ይገባል፡፡ በዚሁ ምክንያት በመላምትነት የቀረበው ተጠባቂ ውጤት ሙሉ በሙሉ ላይሳካ ይችላል፡፡ በዕውቀት ሽግግር እንቅስቃሴም የተሸጋገረው ዕውቀት ምርታማነቱ ወይም ውጤታማነቱ እንደተጠበቀው ላይሆን ይችላል፡፡ ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ወይም መንሥኤዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ይይዛሉ፡፡

- የሚሸጋገረውን ዕውቀት በውል ለይቶ አለመገንዘብና የዕውቀት አቀባዮችን እንዲሁም የሽግግሩን ዘይቤ በጥንቃቄ አለመገንዘብ፤

- የተሸጋገረውን ዕውቀት ፋይዳ እና ዓላማውን ለመመዘን የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ሥርዓት አለመኖር ወይም ግልጽነት የጐደለው መሆን፤

- የዕውቀት ሽግግሩ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ካሉት ተቋማዊ አደረጃጀቶች ጋር ለማጣጣም ትኩረት አለመስጠት፤

- እና ሌሎችም .... ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የዕውቀት ሽግግር ተዋንያን በተለይ ዕውቀት አቀባይ፣ ዕውቀት ተቀባይና ተሳታፊዎች የራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ስለሆነም ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተለይ በዕውቀት ሽግግር ጊዜ ለሽግግሩ ተሳታፊዎችን መለየት ተገቢ ይሆናል፡፡ አስፈላጊነታቸውም በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ መቼ እንደሚያስፈልጉም ማጤን የግድ ይላል፡፡ ለተሳትፏቸውም ስልታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በሚሸጋገረው ዕውቀት የመሸጋገሪያው መንገድ ላይ ሊያሳድሩት የሚችሉትን በጐ ተፅዕኖ መገንዘብ ብልህነት ነው፡፡ ለመሳተፍ ያነሳሳቸው ጉዳይ እና የሚሸጋገረው ዕውቀት ከእነሱ የዕውቀት ፍላጐት ጋር ያለው ትስስርም ቢታወቅ ጥሩ ነው፡፡

የዕውቀት ሽግግር በበርካታ ምክንያቶች ሊደናቀፍ ወይም ሊገታ ይችላል፡፡ ለሽግግሩ አደናቃፊ ምክንያቶችን ለይቶ ማወቅ በሌላ አንፃር ሽግግርን ማሳለጥ እንደሆነ ሊታሰብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የዕውቀት ሽግግርን ሊያደናቅፉ ወይም ሊገቱ ስለሚችሉ ልዩ ትኩረት ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

- አዕምሯዊ ዕውቀትን በሚገባ መለየትና መረዳት አለመቻል፤
- በአዕምሯዊ ወይም ተሞክሯዊ ዕውቀት ላይ የተለያዩ አመለካከቶች መኖር፤
- የቦታ መራራቅ፤
- የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውስንነት፤
- ያልተጋሩት ማኅበራዊ ማንነት፤
- ቋንቋ፤
- የሙያ ቀረቤታ፤
- የሙያ/የውስጥ ግጭቶች፤
- የትውልድ መራራቅ፤
- ማትጊያ አለመኖር፤
- በጋራ እምነቶች፣ ተሳቢዎች እና ባሕላዊ አስተሳሰቦች ላይ የሚታዩ ችግሮች፤

- ዕውቀትን በስዕላዊ መንገድ መግለጽአለመቻል፤
- የልምድ ማነስ፤
- በትክክል አለመረዳት፤
- የተዛባ መረጃ፤
- የማይመጥን ተቋማዊ ባሕል፣
- የመነቃቃት ጉዳይ፤
- እምነት ማጣት፤
- አቅም፤
- እና ሌሎችም......

የዕውቀት ሽግግር አማራጭ ስያሜዎች በርካታ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ የስያሜዎች መበራከት ዕውቀት ማኔጅመንት የአንድ ወይም የተወሰነ አካል ባለቤትነትን የማያንፀባርቅ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ባለሙያዎች ወይም

ግለሰቦች እንዲሁም ተቋማት እንደአግባቡ ስያሜዎችን ይሰጣሉ፡፡ ስያሜዎቹም በተለዋጭነት ጥቅም ላይ እየዋሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የስያሜ አማራጮች እጅግ በርካታ ከሆኑ የዕውቀት ምንጮች ተሰብስበው ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተተርጐሙ ናቸው፡፡ የስያሜዎቹ አተረጓጐምም ቃል-በቃል ሳይሆን አስረጅ በሆነ መልኩ እንደሆነ አንባቢያን እንዲገነዘቡት አሳስባለሁ፡፡

- ተግባራዊ ምርምር፤
- መረጃን ማሰራጨትና መጠቀም፤
- የመረጃ አሰረጫጨትና አጠቃቀም፤
- ተቋማዊ ግኝት/ፈጠራ፤
- በጋራ ወይም በተቋም ዕውቀት የተገኘ ግኝት፤
- ተግባራዊ ስርጸት፤
- አዲስ ግኝት ወይም ዕውቀት መጠቀምና በተግባር ማዋል፤
- አሳታፊ ተግባራዊ ምርምር፤
- ተግባራዊ የጤና ምርምራ፤
- የፈጠራ ትግበራ፤
- አሳታፊ ጥናትና ምርምር፤
- አቅም ግንባታ፤
- የተቀናጀ ዕውቀት ሽግግር፤

- የበሽተኛ ደኅንነት ጥንቃቄ፤
- የለውጥ አፈጻጸም፤
- የዕውቀት እጥረት/ክፍተት፤
- ምርምርን ተዋቂ ማድረግ፤
- የዕውቀት ትግበራ፤
- የብቃት ማረጋገጫ፤
- ትብብር፤
- ዕውቀትን መደለል፤
- የጥራት መሻሻል፤
- ትብብር/ውሕደት፤
- የዕውቀት ተግባቦት፤
- የምርምር አቅም ብቃት፤
- የጋራ ዕድገት፤
- የዕውቀት ጊዜ /ዘመን/ የዕውቀት ዑደት፤
- ምርምር አተገባበር፤
- አወዛጋቢ ገላጋይነት /አስቸጋሪ፣ ውስብስብ ገላገጋይነት/፤
- ዕውቀት ማኅልበትና ትግበራ፤
- ሳይንስ ተግባቦት፤
- የሳይንስ ውስብስብነት፤
- የዕውቀት ስርጭት፤

- የቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ሽግግር፤
- ቀጣይ ትምህርት /ዕውቀት የማስፈለግ ሂደት/፤
- ዕውቀትን ማዳረስ፤
- መናኘት፣ ማሰራጨት፣ መንዛት፤
- ዕውቀትን ቅብብሎች /መለዋወጥ/፤
- አጠቃላይ የጥራት አመራር፤
- ግኝት ማስፋፋት፣ ማሠራጨት፤
- ዕውቀት አስተዳደር፤
- ሥርጭት/ክፍፍል፤
- ዕውቀት ማነቃቃት/ማነሳሳት፤
- ትርጉማዊ ምርምር፤
- ስኬታማ ስርፀት፤
- የምርምር ዉጤታማነት፤
- የዕውቀት ሽግግር፤
- ዕውቀት ማስፋፋት/ማሰራጨት፤
- ግምገማዊ ምርምር፤
- የዕውቀት ማጎልበት/ማደግ/መበልጸግ፤
- ግብረ መልስ፤
- የዕውቀት ትርጉም፤
- አጠቃቀም አያያዝ፤

- የእጥረት ትንተና፤
- መመሪያ አፈጻጸም፤
- ዕውቀት አጠቃቀም፤
- ተጽዕኖ፤
- ዕውቀት በተግባር፤
- አፈጻጸም፤
- ትሥሥርና ልውውጥ፤
- እና ሌሎችም...

በዕውቀት ሽግግር እና መጋራት ላይ የቀረቡት ሐሳቦች እንዳሉ ሆኖ በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ሰዎች እና ተቋማት ዕውቀትን በመጋራት በኩል የራሳቸው የሆኑ በርካታ ውስንነቶች ወይም የፍላጐት መገለጫዎች አሏቸው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን የዕውቀት ሽግግር ወይም መጋራት አጋዥ ሁኔታዎችን እንመልከት፡፡

- ዕውቀት የኃይል መገለጫ ነው በሚል የተዛባ እምነት፤
- ዕውቀትን ለመጋራት የጊዜ እጥረት አለብን ከሚል ያልተፍታታ አመለካከት፤

- ዕውቀትን ከማሸጋገር ወይም ከመጋራት የላቀ መደበኛ ወይም አጣዳፊ እና በርካታ ሥራዎችና ኃላፊነዎች አሉብኝ ማለት፤

- ይህ እኔን የሚመለከት ሥራ አይደለም በሚል ጨለምተኛ አስተሳሰብ፤

- የሌሎችን ሐሳብ በመቀመር ወደ ጠቃሚ እሴት መለወጡ ለሐሳቡ ወይም ለዕውቀቱ አመንጪዎች የሚገባቸውን ዕውቅና አይሰጥም በማለት፤

- ተግባራትን ለእኔ በሚያመቸኝ መንገድ ወይም አዝማሚያ ማካሄድ አለብኝ ከሚል ጠባብ አስተሳሰብ፤

- የዕውቀት ሽግግር ያለምንም ትኩረት በራሱ አካሄድ የሚከናወን ስለሆነ ምንም አዲስ እና የተሻለ ነገር የለም ከሚል ሰንካላ ምክንያት፤

- ከፍተኛ የመረጃ ሸክም ስላለብኝ ተሰላችቻለሁ ከሚል ሰበብ ያጐለበተው እይታ፤

- ሌሎች እኔ የማውቀውን ሁሉ ያውቃሉ በሚል የቸልተኝነት አስተሳሰብ፤

- ማንኛውንም ሐሳብ ወይም ዕውቀት ባካፍል ተቋማዊ ፋይዳው እርባና ቢስ ነው ከሚል ሰንካላ አስተሳሰብ፤

- ለማሸጋግረው ዕውቀት ለእኔስ ምን ጠቃሚ ምላሽ ወይም ስጦታ ወይም ልዩ ትኩረት ሊጠኝ ይችላል፤

- እና ሌሎችም…

ከላይ የተጠቀሱት የዕውቀት ሽግግር አዘጋጆችን ጠርጥሮና ለይቶ እርምጃ መውሰድ አለመቻል መልካም አስተሳሰቦች እየሚሸሹ አላስፈላጊ ወይም ገዳዳ ፋይዳዎችን ይተፋሉ፡፡ ይህ ልዩ ጥንቃቄው ዝግጁነትን እና ቁርጠኝነትን ይሻል፡፡ ምክንያቱም በዕውቀት ላይ ያልተመረኮዘ ውሳኔ በቀጣይ ማስተካከያዎች የሚስተጋባ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመጨረሻም የዕውቀት ሽግግር ውጤታማነት መመዘኛው አቀባዩ ግልጽና ተዓማኒ ሆኖ ሲገኝ፣ ተቀባዩ ደግሞ ዝግጁ ሆኖ ሲቀበልና ተግባራዊ ሲያደርግ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

# ዕውቀትን መተርጎም እና መጠቀም

በማንኛውም ጊዜ ምርምርና ማስረጃዎች በፖሊሲ አፈጻጸሞች ላይ የራሳቸው የሆነ አወንታዊ ፋይዳ እንዳላቸው በግልጽ ይታወቃል፡፡ የምርምር ውጤቶችና ማስረጃዎች ተግባራዊ እንዲደረጉና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ዕውቀትን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የምርምር ውጤቶች እና ተጨማሪ ማስረጃዎች በትክክል ተተርጉመው እንዲተገበሩ ካልተደረጉ ውጤታማነታቸው እምብዛም እንደሚሆን መገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ በትክክል የተተረጎመ ዕውቀት (የምርምር ውጤቶች) ከፍተኛ ወጭ ተደርጎባቸው የተገኙ በመሆናቸው ቢያንስ ወጫቸውን የመሸፈን አቅም እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ተመራማሪዎች የምርምር ውጤቶቻቸውንና ማስረጃዎችን በወቅቱና በተገቢው መጠን ማቅረብ ካልቻሉ ተቀባዩ ወይም ተርጓሚው ችግር ውስጥ እንደሚገባ መረዳት ውስብስብ ትንተና የሚያስፈልገው ጉዳይነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተመራማሪዎች ውጤቶቻቸውን ወይም የዕውቀት ትሩፋቶችን በውል ተተርጉመው ተግባር ላይ እንዲውሉ የማስፈጸሚያ ጥቆማዎችን ማድረግ የኃላፊነት ግዴታቸው መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየን ዕውቀት በአግባቡ ተተርጉሞ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ የዕውቀት ባለይዞታዎችና ዕውቀትን ተርጉመው ተደራሽ የሚያደርጉ ሁሉ ግዴታ መሆኑን ነው፡፡

በተለይ በሕክምና፣ በሥነ-ምግብ እና ሌሎች ቴክኒካዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የሚፈልቁ ዕውቀቶች በተጠቃሚው ወገን በቂ ግንዛቤ ካልተወሰደባቸው አስጊና አደገኛ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ከአንድ የሕክምና ባለሙያ የታዘዘ መድኃኒት ወይም ከአንድ የግብርና ባለሙያ የተሰጠ የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም በተጠቃሚው ወገን በትክክል ግንዛቤ ተወስዶበት ተግባር ላይ እንዲውል ካልተደረገ ሊከተል የሚችለውን አደጋ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ይህ የሚያሳየን ዕውቀትን በትክክል ተርጉሞ ተግባራዊ አለማድረግ ማስረጃዎችንና ዕውቀትን

ከማባከን ባሻገር ሊከሠቱ የሚችሉ አሉታዊ ሁኔታዎችን ማባባስ ጭምር መሆኑን ነው፡፡ የምርምር ውጤቶችን በሚገባ ተርጉሞ አለመጠቀም በሚታወቀው እና በሚተገበረው ዕውቀት መካከል የሰፋ ክፍተት መኖሩን ነው፡፡ ስለሆነም በተገቢውና አጥጋቢ በሆነ መንገድ የተተረጐመ ዕውቀት የሰዎችን ኑሮ እንደሚያሻሽል መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ከላይ የተገለጻውን ጠቅለል አድርገን ሥናይ በምርምር እና በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ሊታይ የሚገባ ትስስር ጠንካራ ሊሆን እንደሚገባው ነው፡፡ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለፀው አንዱ የዕውቀት ማኔጅመንት ጥቅም መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋፋት ነው፡፡ በመሠረቱ መልካም ተሞክሮዎች ከአንድ ወይም ከተለያዩ ምንጮች ፈልቀው ወይም ተሻሽለው ወይም ዳብረውና ጐልብተው ውጤታማነታቸው ተመስክሮላቸው በሌላ ሥነ-ምሕዳር ወይም ሥርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ ቢውሉ በተመሳሳይ ወይም በተሻለ ሁኔታ ምርታማነታቸውንና ትርፋማነታቸውን ሊያሳዩ የሚችሉ፣ የሚታዩና የሚዳሰሱ ወይም የማይዳሰሱ የምርምር ወይም የተሞክሮ ተምሳሌያዊ ውጤቶች መሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

በተለያዩ ሙያዎችና ይዘቶች ሥር ያለ ዕውቀትንተርጐሞ ከመጠቀም አንፃር በርካታ ተዛማጅ ትርጉሞች ወይም አባባሎች በተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተካተው ይገኛሉ፡፡ በሰፊው ጥቅም ላይ የዋሉ ተዛማጅ ትርጉሞች እና አባባሎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- ማስረፅ፤
- መጠቀም፤
- መተርጐም፤
- ማሰራጨት፤
- ማስፋፋት፤
- መቀበል፤
- ክፍተትን መሙላት ወይም ማጥበብ፤
- የምርምር ውጤትን መጠቀም፤
- መተግበር፤
- ሠርቶ ማሳየት፤
- ማስገንዘብ፤
- ማስተዋወቅ፤
- ተግባራዊ ምርምር፤
- ተቋማዊ ለውጥ ወይም ሽግግር፤
- ሥልጠና፤

- ማኀበራዊ ትስስሮች፤
- ማነቃቂያ መድረኮች፤
- ሐሳብ ማካፈል፤

በተቋም አደረጃጀት ሲታይ ደግሞ ዕውቀት በአግባቡ ካልተተረጐመ መሠረታዊ ለውጦችን በማምጣት ተቋማዊ ሽግግርን እውን ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ነው በተቋማዊ ለውጦች እንደግብዓት የምንጠቀምባቸው ዕውቀቶች ግልጽነት በጐደለው መልኩ ሲተገበሩ በርካታ ሁኔታዎች የሚከሠቱት፡፡ የዚህ ሥረ-መሠረቱ በርካታ ቢሆንም የተዛባ አመለካከት ሳይጣራና መስመር ሳይዝ ወደ ተግባር መገባቱ በሠራተኛው፣ በባለሙያውና በአመራሩ መካከል አለመተማመንን መፍጠሩ እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ እጅግ የሰፉና የረቀቁ ግላዊና ማኀበራዊ ሐሳቦች በውል ባልተንሸራሸሩበትና የጋራ መግባቢያ ባልተደረሰበት ሁኔታ በለውጥ ማስፈጸሚያ ሂደት በርካታ ውጣ ውረዶችና ሁካታዎች የሚታዩትና የሚሰሙት እነዚህ ያልተፍታቱ ሐሳቦችን በትክክል ለመተርጐም ባለመቻል በርካታ ሽንቁሮችና ክፍተቶች የመፈጠራቸው አጋጣሚ ወይም እድል ከፍተኛ በመሆኑ ይታወቃል፡፡

ዕውቀትን በአግባቡ ካለመተርጐምና ለተቋማዊ ለውጥ ዝግጁ አድርጐ አለመጠቀም ሐሳብንና ክህሎትን ለውጥን ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረጉ ሂደቶች በተለይ ለውጥን በእቅድ ከመምራት አኳያ፣ ለውጥን ተግባራዊ ለማድረግና ለውጡን በቀጣይነት ከማስኬድ አንጻር ልዩና ከፍተኛ ጥንቃቄን ተገን አድርጐ በላቀ እንቅስቃሴ መዳዝን መምረጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ለማንኛውም ተቋም ተመራጭ እንደሆነም ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

አንድን የዕውቀት መስመር የሚጋፉ የማኅበረሰብ አካላት ለዕውቀቱ የሚኖራቸው ግንዛቤ የተለያዩ ስለሚሆን በጋራ ሊያግባባቸው የሚያስችል ትርጉም ይዘው መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህም የጋራ የሆነ ችግራቸውን ለመፍታት አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው ነው፡፡ በሌላ መልኩ ማኅበረሰቦች ዕውቀትን ሲጋሩ ተግባራዊነቱንም መጋራታቸው ወይም ለትግበራው መተጋገዛቸው አይቀሬ ነው፡፡ በሂደቱም የበለጠ ዕውቀት በማግኘት ውጤታማነታቸውን እያጐለበቱ በስኬት ጐዳና ሽር-ጉድ ማለታቸው አያጠራጥርም፡፡

በመሆኑም የዚህ እሴት መነሻው የማኅበረሰቡ ተነሳሽነት እና የዕውቀት ተርጓሚዎች ችግር ፈቺ ጽናት ለመሆኑ ማስረጃ ፍለጋ

መሄድን አይጋብዝም፡፡ በዚህ መልኩ የሚንቀሳቀስ ማኅበረሰብ ለጋራ ፍላጐታቸው የጋራ መፍትሔ ለመሻት ቆርጠውና ተስማምተው ለትግበራ ዝግጁ መሆናቸውን መረዳት አካሄድን ወደ ሌሎች የማኅበረሰብ አካላት ለማጋራት እንደሚረዳ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል የሚል የጸና እምነት አለኝ፡፡

አንዳንዴ በጋራ ወይም በግብቡነት ተተርጐሞ ተግባራዊ የሚደረግ ዕውቀት የራሱን ወሰን ወይም ጥግ መያዙ አይቀርም፡፡ የዚህ መገለጫም የጋራ የተደረገው ሐሳብ መሆኑን በግልጽ መረዳትን ይጠይቃል፡፡ የጋራ የተደረገውና የሚተገበረው ሐሳብ ዙሪያ መለሱ የማኅበረሰቡ በመሆኑ የሌሎችን ግላዊ ሐሳቦች የማግለል ባሕሪ ይኖረዋል፡፡ ይህ የሐሳብ ክልል አልፎ አልፎ የፍላጐት ግጭቶችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተያያዘ መልኩም የሐሳብ ግጭቶች ወደ አላስፈላጊ ፉክክሮች ሊያስገቡ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም ማኅበረሰባዊ ክልሎች በጋራ ዕውቀቶች ምክንያት በሚያስከትሉት ፉክክር-አከል አለመግባባቶች በተሞክሮ እና በጥረት ሊስተካከሉ እንዲችሉ ልዩ ልዩ የማህበረሰቡ አካላት የጋራ የመማሪያ መድረኮችን በመፍጠር ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡ ይህም የማኅበረሰቡን የዕውቀት አተረጓጐምና የትግበራ አድማስን ያሰፋል፣ የግብ ስኬት ሂደትን በማፋፋም ማኅበራዊ ትርፋማነትን

ያመጣል፡፡ ስለሆነም ዕውቀትን በአግባቡ በመተርጎም ማኅበረሰባዊ ጥቅምን ከማምጣትና የፍላጐት ድምጽን ጐላ አድርጐ ለማሰማት እንዲቻል ማኅበራዊ ሥነ-ምግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የጋራ መግባቢያ ውሎችን ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ መረዳት ይገባል፡፡ የማያስፈልጉ ጥርጣሬዎችን ለማስወገድና ማኅበራዊ እድገትን ከመሻት አኳያ በጋራ በመማማር ወይም በመመካከር የዕውቀት ትርጉምን እና ግንዛቤን ማስፋት ጠቃሚነቱ የተለየ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተቋም ደረጃ ሲታይ ደግሞ የተቋሙንአደረጃጀት ከግምት ውስጥ ማስገባት ልዩ ልዩ የሥራ ድርሻዎች በየዘርፉ ውስጥ እንዳሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ የሥራ ክፍፍል በዕውቀት ትርጉም ላይ የራሱ ተፅዕኖ ሊያመጣ ይችላል፡፡ በሥራ ክፍፍሎች ውስጥም የሙያ ስብጥሩ የተፈረጀ በመሆኑ በዚህ መልኩም የዕውቀት ትርጉምና ቀጣይ ትግበራ የተለየ መልክና አቅጣጫ ሊይዝ ይችላል፡፡ ስለሆነም የዕውቀት አተረጓጐም ስልታዊና ፈርጃዊ ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ የሚቻል ይመስለኛል፡፡

ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተመለከተው በአንድ ተቋም በተለያዩ ደረጃዎችና ሙያዎች ሥር ሆነው የዕውቀት ምንጮች ተብለው የተለዩ ግለሰቦችም የዕውቀት ሐብታቸው፣

ችሎታቸውና ሰብዓዊ አስተሳሰባቸው እንዳይባክን ማድረግ ልዩ ትኩረት ይሻል፡፡ ከፍላጐት አንፃር በተለይ ተቋማዊ ለውጥን በቀጣይነት ለማስኬድ ይህ የዕውቀት ምንጭ ምሰሶነቱ ልዩ ግንዛቤ እንዲሰጠው ያስፈልጋል፡፡ በተቀጣይም የዕውቀት ግብዓትነቱን ለይቶ እና አንጥሮ መተግበር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን መቀበል ተገቢ ነው፡፡ የዕውቀት ምንጮቹንም ያለምንም መሸማቀቅ ከተለመደው አካሄድ በላቀ ሁኔታ ተገቢውን ግብዓት እንዲሰጡ ማበረታታት እና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የዘወትር ተቋማዊ ሥርዓት ሆኖ ሊቀጥል ይገባል፡፡ በተቃራኒ ገፅታው ምንጮቹ ማሚሚቂያ እንጂ የውሳኔ መስጫ ሊሆኑ ያዳግታቸዋል፡፡ የውጤት መገለጫቸውም ያለ ተጋጣሚ በእስታዲዬም ኳስ መጫወት ሊሆን ይችላል፡፡

በግለሰብ ደረጃ ሲታይ ደግሞ ሰዎች ከእነሱ በላይ ከሆኑት ከልምዳቸው፣ ከብስለታቸው፣ ከዕድሜ ጸጋቸው ይቋደሳሉ፡፡ ከእነዚህ ሰብዓዊ የዕውቀት ምንጮች ሲያጠፉ ለመገሰጽ፣ ቢሳሳቱ ትክክለኛውን መንገድ ለማሳየት፣ ክፍተቶችና ጉድለቶች ቢያጋጥማቸው ለማጥበብና ለመሙላት ሁነኛነታቸው የላቀ ነው፡፡ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ዕውቀትን በሚገባ መጠቀም በግለሰብ ደረጃ የተሟላ ስብዕናን፣ በተቋም ደረጃ ደግሞ በግብ-ተኮር እንቅስቃሴ ለለውጥ ዝግጁ መሆንን በማስፈን

እንደሚጠቀም ግንዛቤ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በዕውቀት ያለመታገዝ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ተግባራትና አካሄዶች የእነሱም ብሥራት ከሆኑት ሁሉ **ሊያርቅ እንደሚችል ማስተዋል ይገባል** የሚል ሐሳብ ማቅረብ ይቻላል፡፡

በመሠረቱ ዝርዝሮቹ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮችና እኔ ራሴ ከሰዎች አንደበት የሰበሰብኳቸው ሲሆኑ በአጠቃቀም ደረጃ ልዩነታቸው ጐልቶ እንደሚታይ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የፊት ለፊት ትርጉማቸውን በሚመለከት ብዙዎቹ ከልዩነታቸው ይልቅ ተመሳሳይነታቸው ያይላል፡፡ ስለሆነም አንባቢያን አገልግሎቱን በራሳቸው ግንዛቤ ወይም ሊጠቀሙባቸው በፈለጉት አግባብ እንዲወስዱት አበክሬ ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ድግግሞሽ እንዳልሆኑም በተቻለ መጠን ጥንቃቄ እንዲያዝበት እጠይቃለሁ፡፡

ታሪካዊ፣ ነባራዊና ዘመን ተሻጋሪ ይሆናሉ በሚል ከፖለቲካ፣ ከኢኰኖሚ፣ ከባሕላዊና ከእምነት አኳያ መገለጫዎቹን በሙሉ ለመዘርዘር አስቸጋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደማይቻልም መግለጽ ተገቢ ይሆናል፡፡ ሆኖም በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በስፋት የሚጠቀሱትን ለማቅረብ እንደተሞከረ ግንዛቤ ይወሰድበት፡፡

- ከትዕዛዝ መቀበል፤
- ከሂደት መቆጣጠር፤
- ከተሳትፎ፤
- ከመልእክት ማስተላለፍ፤
- ከአብሮነት፤
- መመሪያ ከመቀበል፤
- ኪሳራን ወይም ጉዳትን መቀነስ፤
- ከእምነት፤
- አምኖ ከመቀበል፤
- ራስን ከመቀየር፤
- ከግንዛቤ፤
- ከፈተና ማለፍ፤
- ከውሳኔ፤
- ቅደመ-ሁኔታዎችን ከማስቀመጥ፤
- ከምክንያታዊነት፤
- ሰምቶ ከመተግበር፤
- ከመገመት፤
- ከወጭ ቆጣቢነት፤
- ከመልመድ/ከመላመድ፤
- ከግዴታና ውዴታ፤
- ተግባብቶ ከመሥራት፤

- ከምስክርነት፤
- ከመለያየት፤
- ከትንተና፤
- ከተለጠጡዕቅዶች ውጤቶችን ከመጠበቅ፤
- ድጋፍ ከማድረግ፤
- በራስ ከመተማመን፤
- ከትግል፤
- ከተዓማኒነት፤
- ከአማራጮች፤
- ከድርድር፤
- መድረክ ከመምራት፤
- ትክክለኛ የሥራ አጋጣሚን ከመቀበል፤
- ከመጋራት፤
- ወድቆከመነሳት፤
- ከፍታን/ዝቅታን ከመወሰን፤
- ክፍተትን ከመለየት፤
- አድማሳዊ እይታ ካለማድረግ /ከትኩረት/፤
- አድማሳዊ ግምገማ ካለማድረግ /ከትኩረት/፤
- መፍትሔ ከመሻት፤
- ሥጋቶችን ከመለየትና ከማስወገድ፤
- ከመልሶ ማጥቃት፤
- የትምሕክትን የጠባብነት አመለካከት ከመዋጋት፤

- ከመቻቻል፤
- ብዝኀነትን ከማወቅና ከማክበር፤
- ሰቆቃን ከመቋቋም፤
- ዜጐች በአደጋ እንዳይዳረጉ ከማድረግ፤
- ግብረ-መልስ ከመስጠት፤
- መርሕን ካለመሳት፤
- ይቅርታ ከማድረግ፤
- አፍራሽ አቅጣጫን ከመለየት፤
- ከማመስገን፤
- ልማትን ከማፋጠን፤
- ለሰላም ቅድሚያ ከመስጠት፤
- ቁጭትን ካለማባባስ፤
- ጥላቻን ካለማባባስ፤
- ከአስነዋሪ ተግባር ከመላቀቅ፤
- ተፈጥሮን ከመግራት፤
- አዝማሚያዎችን ከመለየት፤
- ከቅድመ-ዝግጁነት፤
- የተሟላ ግልጽነት፣ አመኔታ እና የመፈፀም ተነሳሽነትን ከማስፈን፤
- ከሰጥቶ መቀበል፤
- የግብር ግዴታን ከመወጣት፤
- ሐሳብን ከመግለጽ፤

- ሥልጣንን የግል ጥቅም ማስጠበቂያ ካለማድረግ፤
- ውክልናን ከመስጠትና ከመቀበል፤
- ሚሥጢርን ከመጠበቅ፤
- ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከማክበር፤
- መስዋዕትነትን ከመክፈል፤
- የሕዝብ አገልጋይ ከመሆን፤
- ሥነ-ምግባርን ከመጠበቅ፤
- ከአስተዋይነት፤
- ከነውር ከመጠበቅ፤
- አሉታዊ ተጽእኖን ከማስቀረት/ከመቀነስ፤
- ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅም/ጉዳቶችን ከመለየት፤
- በሠራተኛና በአመራር ጠንካራ መተማመንና መደጋገፍ ካለማስፈን፤
- ሕዝብን ከማንቀሳቀስ፤
- ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ከማምጣት፤
- ተቋማዊ እሴቶችን ከመቀበልና ከመተግበር፤
- ችግሮችን አሳንሶ ካለማየት፤
- ተፈጥሮን ከማድነቅ፤
- ተጠቃሚነትን /የጋራ ወይም የግል/ ከማስከበር፤
- ተፈላጊ ውጤት ከማምጣት፤
- የውጤት ተቋዳሽ ወይም አቋዳሽ ከመሆን፤
- ስኬትን ከማስቀጠል፤

- የሐሳብን ትግበራ ከመወሰን፤
- ማኅበራዊ ግንኙነትና ትስስሮች ውስጥ ከመሳተፍ፤
- ቅራኔዎችን በገላጋይነት መልክ ከማስያዝ፤
- መር-ግብሮችን ከመተርጐም፤
- መሠረተ-ልማትን ከማሟላት፤
- መልካም አስተዳደርን ከማስፈን፤
- ፖለቲካዊ አመራርን ከማጐልበትና ከማራመድ፤
- ስኬታማ አመራሮችን ከማቅረብ፤
- ግልጽ ከመሆን፤
- የሥራ መሣሪያዎችን በአግባቡ ከመጠቀም፤
- ደንቦችን በአግባቡ ከማስተናገድ፤
- በጋራ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ከመምከርና ከመወሰን፤
- ምቹ የሥራ ቦታን ከመፍጠር፤
- ለለውጥ ቅርብ ከመሆን፤
- ተደራጅቶ ከመተግበር፤
- ሥሪቶችን ከማስመዝገብ፤
- የተቋም ተልዕኮን በሚፈለገው ፍጥነት፣ ጥራትና መጠን ለማሳካት በተደራጀ አግባብ ከመንቀሳቀስ፤
- በብቃት ከመፈፀም ሐሳብና ተግባር፤
- የጐደለውን ከመሙላት፤
- ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ከመስጠት

- ምክርን ተቀብሎ ከመተግበር፤
- የተንጋደደ አተገባበርን አቃንቶ ከማስኬድ፤
- የጋራ ፕሮጀክቶችን ከመቅረፅና ከተመግበር፤
- ተወዳዳሪ/ተፎካካሪ ከመሆን፤
- ሐሳብ ከመለኰስ፤
- ፍትሕን ከማግኘት፤
- የክህሎት ግንባታን በአግባቡ ከመተርጐም፤
- ከማሳመንና ከማጤን፤
- ምኞትን ከማሳካት፤
- የፍትሐዊነትን፣ የግልጽነትንና ተጠያቂነት መርሆናዎችን አጉልቶ ከማውጣት፤
- በሕግ፣ ደንብና መመሪያ ከመመራት፤
- ሂስን በቅንነት ወስዶ ማስተካከያ ከማድረግ፤
- ጠበኝነትን ከማብረድ፤
- የሥራ አፈጻጸምን ከማቀላጠፍና ከሪፖርት፤
- የክህሎት፣ የሙያ ብቃትና የለውጥ መሣሪያዎችን ከመጠቀም፤
- የሕዝብ/የተገልጋይ እርካታን ከመፍጠር፤
- የሕዝብ መብትና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፤
- የተቋም አደረጃጀትና አሠራርን ከማጣጣም፤
- የሥራ ፍሰትን ከማስተካከል፤
- ለጋራ ግብ መሳካት ተሳስሮና ተናቦ ከመረባረብ፤
- ባሕልና ታሪክን ከመገንዘብ፤

- ገናና እና ድብቅ ታሪክን ከመረዳትና ተደራሽ ከማድረግ፤
- የታሪካዊ ቅርሶች ተደራሽነትን ከማጉላት፤

ገዳፉ ተግባራትንና አመለካከቶችን በመታገስ፣ በመቻል፣ በመሸከም፤ እንደራስ ጉዳይ በማየት የተደናበረ የዕውቀት ምልክቶችን አይቶ የሚያልፍ ሰብዓዊ ዕውቀትን ያመለክታል ማለት ይቻላል፡፡

ምንም እንኳን መላላት አጥብቆ ለመጓዝ ብቃት፣ ትጋትና ፍላጐትን በምሰሶነት መያዝ ቢገባም ማወቅ፣ ማመዛዘን፣ መለወጥ፣ መሻሻል፣ መገመት፣ መመዘን፣ ካለፈው መማር፣ ነገን ማሰብ፣ ከአካባቢ፣ ከዘር፣ ከሃይማኖት፣ ከቆዳ ቀለም ወጣ አድርጐ ማሰብን፣ የማኅበረሰባዊነት ልማትን ማጐልበት፣ የራስ የላቀ ቦታ መስጠትና አዕምሮን ማሳለጥ፣ ስህተትን መቀበልና ማረም፣ አዲስ ነገርን ወይም ሁኔታን ለመረዳትና ተቀብሎ ለመጓዝ፣ ለመሠልጠን፣ ለመማር፣ ለፈጠራና ትጋት፣ ለፍቅር፣ ለርኅራሄ፣ ለመቻቻል፣ ለሥርዓት፣ ሕግ ተገዥነት፣ በአቅም ለመዝለቅ፣ በመርሕ ለመጠቀም ዕውቀት የተጠበቀ ቋጠሮ ነው፡፡

# የሳይንስዕውቀት

ሳይንሳዊ ክንዋኔን አምዳዊና አግድማዊ ተደራሽነቱን ከማጕልበት አኳያ የሳይንስ የዕውቀት ዘርፍ ጉልህ ሚና አለው፡፡ የሳይንስ አጠናን ዘዴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ ተጨባጭና የማይጨበጡ ክስተቶችን ለማጥናትና ዘርፋዊ ወይም ሁሉ-አቀፍእውነትን ከማመንጨት አንፃር በርካታ ክፍለ-ዘመናት መቆጠራቸው እሙን ነው፡፡ አንድ አጠናን ሳይንሳዊ የሚያሰኘው የአጠናኑ ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰቡ፣ የመረጃ አተናተኑና ትርጉም ያለው የዕውቀት ምንጭ ከመፍጠርና አኳያ ያሉ ገሃዳዊ አንዳንዴምሚሥጢራዊ ሂደቶች ዓይነትና ይዘት እንዲሁም በቀጣይነት ሊተገበሩ መቻላቸው ሁሉም ከግምት ውስጥ ገብተው ሲመዘኑ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ በመሆኑም ሳይንሳዊ የአጠናን ወይም ነገሮችን እና ክስተቶችን የመረዳት ዘዴ በቅድሚያ ስለሚጠናው የጠለቀ ዕውቀት መያዝን፣ ጥናቱን

ለማካሄድ የተመረጠ አካሄድን፣ በጥናቱ ሂደት የተሰበሰቡ አሃዛዊ ወይም ቃላዊ መረጃዎችን የማደራጀት እና የመተንተን ብሎም የትንታኔዎችን ወደ ትርጉም ያለው መረጃ ማዳረስን አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ መመንደግና የዕውቀት ፍላጐት እያየለ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ትውፊቱ እየሰፋና እየጠለቀ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡

በዘመናት ሂደትና በሰው ልጅ የማሰብና የመተንተን ብቃት ማደግ የተነሳ ሳይንሳዊ ዕውቀትም የፍልስፍና ዘርፍ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ዘርፎችም የጥናት እና የትምህርት ዘርፍ እየሆነ የአዕምሮ ቀራጭ እንዲሆን በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ መገኘቱ የዓለማችን የወቅቱ ክስተት እየሆነ መገኘቱ አያስገርምም፡፡

ሰብዓዊና ሥነ-ሕይወታዊ ፋይዳዎችና ሥርዓቶችን ለይቶ እና ጥቅም ሊሰጡ በሚችሉበት አግባብ ማስቀመጥና የግንዛቤ ወይም የዕውቀት ምንጭ ማድረግ የሳይንሳዊ ዕውቀት ማኔጅመንት ትኩረት ነው፡፡ በዚሁ አግባብ አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ቀጣይ ፋይዳዎቻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ምክረ-ሐሳቦችንና የተጠቃለሉ ዕውቀቶችን ማቅረብ የዘወትር እንቅስቃሴው አካል መሆኑን ሳይንቲስቶች ለሚያወጡት ዕውቀት ዋቢነታቸውን

ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም ነው ለዕውቀት ምንጮቻቸው የተቀናጀ ትንተና በመስጠት ልዩ ትኩረት ለሚቸራቸው ምክሮቻቸው ቅድሚያ ሰጥተው እና ከተለመደው አካሄድ ወጣ ብለው አንፃራዊ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ደፋ ቀና ሲሉ የሚታዩት፡፡ ምክንያቱም ጥቃቅን ስህተቶች የማይሽሩ ጠባሳዎችን ይዘው ስለሚቀሩ ነው፡፡

ሳይንስ ሁኔታዎችን ወይም ክስተቶችን አንጥሮ ለመረዳት ሰዎች በተሟላ የሐሳብ ወሰን ወስጥ ሆነው በመረጃዎች ላይ በመመርኮዝ አብሮ መቆየት የሚችሉ የውሳኔ መዳረሻዎችን ወይም የግንዛቤ አድማስን ለማስፋትና ለማጐልበት የሚረዳ አካሄድ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡
በሳይንሳዊ ሂደት የነገሮችን ምንነት ወይም የእንቅስቃሴዎችን አካሄድ ወይም በሳይንስ ሊገለጹ የሚችሉትን ሁሉ ለመገንዘብ ሁለት ዓይነት አካሄድ እንዳለ መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ አንደኛው መንገድ ዙሪያ-ገብ አካሄድ ሲሆን ሁኔታዎችን ከውጭ ወደ ውስጥ በማየት ቅኝት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስን በመርሕነት የሚይዘው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከውስጥ በመሆን የመስተጋብሩ አካል ሆኖ ግንዛቤን በተለያዩ ዘዴዎች የመመርመርን አካሄድ መከተልን አጥብቆ ይይዛል፡፡ በመሠረቱ እነዚህ ስልቶች በሳይንሳዊ ምርምር የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ

እንዳላቸው የሚገመት ሲሆን፤ ተመራማሪዎች ምርጫቸውን በፍላጐታቸውና ምርምሩ በሚጠይቀው የጥናት አካሄድ ወይም ስልት ይመሰረታሉ፡፡

በሳይንስና ዕውቀት ዙሪያ የወሳኝነትና የአሳማኝነት ባሕሪ ያላቸው በርካታ አመለካከቶች በዓለማችን ጐልተው ይታያሉ፡፡ በሰፊው የሚወሱትን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

- ሳይንስ የዕውቀት መዋቅር ነው፤
- ዕውቀት ደግሞ በመረጃና ማስረጃ ላይ ያማከለ ነው፤
- መረጃ ደግሞ የዳታ መዋቅርን አጥብቆ የሚሻ ጉዳይ ነው፤
- ያልተተነተነ ዳታ ደግሞ መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ያልተሟላ እና በዘፈቀደ የተቀመጠ የመረጃ ሥረ መሠረት እንደሆነ እና አወቃቀሩም ትርጉም ሊሰጥ የማይችል መሆኑ ይታመናል፡፡

ስለሆነም ሳይንስ በዕውቀት፣ ዕውቀት ደግሞ በመረጃና ማስረጃዎች፣ መረጃና ማስረጃ ደግሞ በዳታ ላይ መመሥረቱ ለተጨባጩ ዓለም መገለጫ መሆኑን ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ ዕውቀት እየተተገበረ ያለ ወይም የተተገበረ

መረጃ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሳይንቲስት፣ መረጃና ዕውቀት የጠበቀ ወዳጅነታቸው ዘልቆ የሚሄድ ዘላለማዊ ነው፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ሳይንሳዊ ዕውቀትን ለማመንጨት ምርምር ሊያተኩርባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን ልብ ማለት ይገባል፡፡ በሳይንሳዊ ምርምር የሚመነጩና የሚጐለብቱ ዕውቀቶች በምርምሩ ሂደት፣ ምርምሩ በሚካሄድበት ጊዜ በሚያጋጥሙ ውስንነቶች እንዲሁም ምርምሩ በራሱ አጠቃላይ ባሕሪያት የሚወሰኑ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የምርምር ሂደቱን በሚመለከት በተለይ ለጥናቱ ወይም ለምርምሩ የተመረጠው ችግርን ከመለየት አንጻር፣ ለጥናቱ ይመጥናሉ ተብለው ከሚመረጡት የማጣቃሻ የመረጃ ምንጮች፣ ከምርምሩ የሚጠበቀውን ውጤት አስቀድሞ ከመገመት አንጻር፣ በጥናቱ ወይም በምርምር ሂደት ከሚሰበሰቡ መረጃዎች (ዳታ)፣ ዳታውን ከመተንተን፣ የተተነተነውን ዳታ ትርጉም በሚሰጥ ደረጃ ከመጻፍ እና የምርምሩን ውጤቶች እንዲሁም ከምርምሩ ዓላማ ጋር በማነፃፀር መደምደሚያ ወይም ምክረ-ሐሳብ ከማዘጋጀትና ከማቅረብ አንፃር የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

ምርምሩ በሚካሄድበት ወቅት የሚታዩ ውስንነቶች ደግሞ ምርምሩን ለማካሄድ የሚያስችል የሰው ኃይልና ሌሎች መሠረታዊ ድጋፎች፣ የተቋሙ አደረጃጀትና አሠራር፣ የምርምሩ ወይም የጥናቱ ውስብስብነት እንዲሁም የምርምሩ ስልት ወይም አካሄድ በዋናነት የሳይንስ ዕውቀት ምንጮችን እንደሚወስኑ ግንዛቤ መውሰድ ይገባል፡፡

የምርምሩ ባሕሪያት ደግሞ የምርምሩ መረጃ ተጨባጭነትን፣ የምርምር ውጤቱ ተጠቃሚዎች ማረጋገጫ፣ የምርምሩ ዓላማ፣ የምርምሩ ምክንያታዊነት እና የውሳኔ እርግጠኝነት የሳይንሳዊ ዕውቀት ምንጮችን ሊገቱ ወይም በተቃራኒው ሊያፋጥኑ የሚችሉ ጉዳዮች መሆናቸው በሰፊው ይታወቃል፡፡

ሌላው ነጥብ ደግሞ ከሳይንስ የሚመነጩ እውቀቶች በምርምር ዓይነቶች ሊመካኙ ይችላሉ የሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የምርምር ዓይነቶች መሠረታዊና ተተግባሪ ተብለው በሰፊው ይታወቃሉ፡፡ አንዳንድ አዋቂዎች ደግሞ አንድን ጉዳይ ወይም ልዩነት መገምገምን እንደ ሳይንሳዊ ምርምር አካል ወይም ዓይነት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ እነዚህ የምርምር ዓይነቶች የሳይንሳዊ ዕውቀት ምንጮችን በተለያዩ መንገዶች በምክንያትነት

ከሚያስጠብቅላቸው ውስጥ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## መሠረታዊ ምርምር

የመሠረታዊ ምርምር ትኩረት ተፈጥሯዊና ማኅበራዊ ክስተቶችን መረዳት፣ መግለጽና መተንበይ ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ይህ የሳይንስ ምርምር ዘርፍ በጽንሰ-ሐሳቦች፣ በመርሖችና በተጠቃለሉ ጉዳዮች ላይ መነሻውን ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይ ጽንሰ ሐሳቦችን ለመፈተሽ ሳይንሳዊ አካሄዶችን በዋቢነት ጥቅም ላይ ያውላል፡፡ አካሄዱም በበርካታ ተግዳሮቶች ሊወሰን ስለሚችል፤ ጥንቃቄ የተሞላበት የምርምር ስልትን ይጠይቃል፡፡

## ተተግባሪ ምርምር

ተተግባሪ ሳይንሳዊ ምርምር ደግሞ በአመዛኙ ከቤተ-ሙከራዎች ውጭ በሆነ መልኩ በማሳ ወይም በተወሠኑ ሥነ-ምሕዳራት ላይ ጥናቱን ያተኩራል፡፡ ትኩረቱም ችግር-ፈቺ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሆኖለተከሠቱ ወይም ለነበሩ ወይም ወደፊት ሊከሠቱ በሚችሉ ችግሮች ምክረ-ሐሳብ እና ተጨባጭ መፍትሔዎችን በማፍለቅ

ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ የሳይንሳዊ ምርምር ዘውግትኩረት ባነሰው የተጠቃለለ ሐሳብ በማቅረብ ላይ አይወሰንም፡፡ እንዲያውም ቀደም ብለው በውል በተለዩና የምርምር አጀንዳ ሆነው በተመረጡና ትኩረት በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ሙሉ ትኩረት ያደርጋል፡፡

## ግምገማዊ ጥናት

ግምገማዊ ጥናት ደግሞ የትኩረት መስኩ አንድን መርሐ-ግብር ወይም ነባራዊ ተግባርን ውጤታማነት ከተለያዩ መነሻዎችና ጠቋሚዎች ላይ በመመሥረት የጥናት ውጤት ማቅረብ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚመነጩ የዕውቀት ምንጮችም ከግምገማዊ ጥናት ባሕሪ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡የተለያዩ ምሁራን ደግሞ የሳይንስ ዕውቀት ምንጮች ውጤቶችን በአሃዛዊና በቃላት /ትረካ/ በመከፋፈል ሲለዩዋቸው ይታያል፡፡ እነዚህ የውጤት መገለጫዎች የሚለያዩባቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም በተለይ ትኩረት የሚሰጡት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሚወስዷቸው ታሳቢዎች፤
- በምርምሩ ዓላማ፤

- በምርምሩ የአካሄድ ሥልት፤
- የተመራማሪው ሚና ወይም ፍላጐት፤
- ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች፤
- የውጤቶች አገላለጽ ወይም አቀራረብ፤
- የውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ፍላጐት ከሞላ-ጐደል በስፋት የሚጠቀሱ ሲሆኑ የዕውቀት ምንጮቹም ይዘት በዚሁ ቅኝት ውስጥ እንዳሉ ይገለጻል፡፡

ጠቅለል ብሎ ሲታይ ሳይንሳዊ ምርምር እንደ ዕውቀት ማመንጫ ወይም ማጐልበቻ ምሰሶነቱ የራሱ አካሄዶች ከመነሻቸው ችግሮችን ወይም ክሥተቶችን መለየት፣ የምርምር አካሄድን ስልት ከመንደፍ፣ ጥናቱን ማካሄድ፣ መረጃ መሰብሰብና መተንተን፣ ጥናቱን ቀደም ካሉ ጥናቶች ጋር ማመሳከር፣ የጥናቱን ውጤቶች ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግና ከአተገባበሩ የሚወጡ ግብረ-መልሶችን በመንተራስ ዕውቀትን በደረጃ እና ፈርጅ ማየት እንደሚቻል መጠቆም ይቻላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ተገን በማድረግ ሳይንሳዊ ዕውቀት ተለያይነት በፍጥነትና በውስብስብነቱ እያየለ በሚታይበት የዘመናችን ሁኔታ እንኳ ቢሆን ዘላቂነቱ እሙን እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ከሳይንሳዊ ምርምር የሚገኙ ዕውቀቶች በተናጠልም ሆነ በጥምረት ለሁሉም ችግሮች መፍቻ ቁልፎች ናቸው ብሎ መውሰድ ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም ሳይንሳዊ ሐሳቦች ሁሌም በለውጥ ማዕበል ውስጥ መሆናቸውን በእርግጠኝነት መውሰድ ይቻላል፡፡ የሳይንሳዊ ዕውቀት መንገድም ጽናትን፣ ትሕትናን፣ ታማኝነትንና ተዓማኒነትን አጥብቆ የሚሻ ጉዳይ መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፡፡

የሳይንሳዊ ዕውቀት የራሱ ሥርዓት፣ ባህል፣ ዘዴና አቀራረብ የመተንተኛ፣ የማቅረቢያ፣ የመገምገሚያና የማስተላለፊያ ሥርዓቱም ጠንካራ ነው ሊባል ይቻላል፡፡ የሳይንሳዊ ዕውቀት ውጤትን ወይም ተሞክሮን ለተለያዩ ምክንያቶች ከማዋል ባሻገር ሕብረተሰቡን የሠመረ ለመለወጥና መዋቅራዊ ሽግግርን ለማምጣት መሣሪያነቱን በተግባር ለማሳየት መትጋት ተተኪ የለውም፡፡ ለዚህም ሳይንቲስቶች፣ ተመራማሪዎች እና የአካዳሚ ምሁራን የሳይንስ ዕውቀት ምንጮች፣ ሥርጭትና መጋራት ባህሉን፣ አካሄዱንና ስልቱን ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ለማኅበረሰብ ግልጋሎትና አወንታዊ ውጤት ሁነኛ አጋር

እንዲሆን አድርጐ ማቅረብ የሙያና የዜግነት ግዴታ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ጠቅለል ብሎ ሲታይ የሳይንስ ዕውቀት ባለቤቶች ከማኅበረሰቡ ርቀውና በሥራና በሙያቸው አጥር ውስጥ ተከልለው ከማኅበረሰቡ እይታ ውጭ ሊሆኑ አይገባም፡፡ የማኅበረሰቡ አካል ነን በሚል እሳቤም ማኅበረሰቡን አጮልቀው በማየት ደካማ የዕውቀት ነፀብራቅን ብቻ እንደ አቅም አውራሽነት በመተንፈሱ ሊቀላቀሉት አይገባም፡፡ ለክብርና ለንዋይ ፍጆታ ብቻ ዕውቀታቸውን ሊያባክኑም ሆነ ሊያስቡት አይገባም ቢባል የቆየና የታወቀን ጉዳይ በድጋሚ እንደመግለፅ ይታሰባል፡፡ ሳይንሳዊ ዕወቀት የልማት አጋርነቱን ዕውን ሲያደርግ ብቻ ነው ትርፋማና ውጤታማ የሚሆነው፡፡

# ዕውቀት የልማት ውል

ዕውቀት ለተለያዩ ጥቅሞች ያለው ፋይዳ በተለያዩ ገፅታዎችና ግዝፈቶች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ዕውቀት እና ልማት የሚዋዋሉባቸው አግባቦች ደግሞ እንዴት እንደሚመስል ለማዬት እንሞክራለን፡፡ዕውቀት ልማትን በተለያዩ ሁኔታዎች ተፅእኖውን እንዴትና ለምንስ ያሳድራል? ብሎ መጠየቅ ምናልባት ለሚሰጠው ትንተና መነሻ ሊሆን ይችላል ወደሚያሰኝ መደምደሚያ መድረስ እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡

ዕውቀት ለልማት ምሰሶ እንደሆነ ቢታወቅም መተማመን፣ መከባበር፣ ለግልና ለጋራ ፈጠራዎች ትኩረት መስጠት፣ መማማር፣ ገንዘብ፣ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽንስ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ሌሎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ጉዳዮች ሲታከሉበት

ተጠባቂ ውጤቶች አመርቂ እንደሚሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

በመሠረቱ ዕውቀት ማኅበረሰባዊና ኢኰኖሚያዊ ተፅዕኖው ፀሐይ የሞቀው ምሥጢር እንደሆነ ቀደም ባሉት የዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች ተጠቅሷል፡፡ ይህም የዕውቀትን ሁለንተናዊ እሴት በሚገባ ማጤን አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይሆንም ብሎ ሙግት ማንሳት የተሰለቸ አስተሳሰብ መሆኑንም ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ሆኖም ዕውቀት ከዘመን ወደ ዘመን መሸጋገሪያነቱ እንዳለ ሆኖ በጊዜ ሂደት ልማትንና ኅብረተሰብን መፍጠርን በግንባር ቀደምትነት ያስቀመጠ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ዕውቀትና ግለሰቦች፣ ማኅበረሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ተቋማት፣ መንግሥትና ባጠቃላይ ሕዝቦች ሊነጣጠሉ የማይችሉ ስብስቦች መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ስለሆነም ዕውቀት እና ልማትን ነጥሎ ማየት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን የማይቻል ነው፡፡

ዕውቀት ከሰፊውና ከጥልቁ እውነታ ተቀድቶ የአካባቢ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ልማትን እንዲያግዝ ተደርጐ መቃኘት ይኖርበታል፡፡

ከላይ የተቀመጠውን በዋቢነት በመያዝ ዕውቀት የልማትና የሂደቶች አቀጣጣይ መሆኑን ነው፡፡ የዕውቀትና የልማት መተሳሰር ዕውቀት የወደፊት አቅጣጫን እውን ለማድረግ ዋቢ መሣሪያነቱ ምጡቅ መሆኑን ያለ ማንገራገር መውሰድ ይቻላል፡፡ ለዚህ ስኬትም ሰዎችወሳኝነታቸውን በተደጋጋሚ መግለጽ ይገባል፡፡

ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ውጤታማነታቸው የሚለካው እነሱን ለማስፈን ፈሰስ በሚደረገው ዕውቀት ላይ መሆኑን ያለመዘናጋት መቀበል ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ሥልታዊ አጠቃቀሙ የተቀናጀ አካሄድ ነው፡፡ ይህም የዕውቀት ማኔጅመንት መሣሪያዎች በሚገባ ተግባራዊ መደረጋቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ከፍ ብሎ እንደጠቆመው እነዚህ መሣሪያዎች የዕውቀት ተደራሽነት፣ መማማር፣ መጋራት፣ በጋራ ፈጠራ፣ ማሻሻል፣ መተግበር፣ መጠቀም፣ ማንጸባረቅ እና መጠበቅ በሚሉ መሠረቶች ላይ መዋሉን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

እነዚህን መሣሪያዎች መጠቀም የሚሻለው ማኅበረሰባዊ ትስስርን ጠበቅ በማድረግ የዕውቀት ባሕል ስብጥርን በማክበር እንዲሁም እይታዎችንና ፍላጐቶችን በውል በመለየት መሆኑ በቅድሚያ ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ማድረግ ዕውቀት ለልማት የሚኖረውን መልካም ተጽእኖ እውን የሚያደርጉ መሪ መርሖችን፣ በዕውቀት ዙሪያ የሚካሄዱ ውይይቶችን ማሳለጥ እና ውጤታቸውን መጠቀም፣ የዕውቀት ሥነ-ምኅዳርን ማስፋትና ማጥለቅ በቀጣዩም የልማት እቅዶችን የላቀ አፈጻጸም እና የሕዝብ ተጠቃሚነትን አስቀድሞ መጨበጥ እንደሚቻል የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ዕውቀት አዕምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ እና ወሳኝ ኩነቶችን ያቀፈ መሆኑን ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡ ይህም በዕውቀት የሚመራ ማኅበረሰብ ለዕውቀት ትኩረት በመስጠት ደስተኛ ኑሮን በዘለቄታ መምራት የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ዕውቀት ለልማት ያለው ጸጋ ሲመዘን በተግባራዊ ሂደቱ ሰብዓዊ መብቶችን በማስጠበቅ መብቱም የግለሰቦች አዕምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ወሳኝ ጉዳዮች መሆኑን በቅድሚያ ግንዛቤ ወስዶ መንቀሳቀስ ላይ መመሥረቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ በሰብዓዊ ጉዳዮች

ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎችን ዘርዘር አድርጐ ማየትም ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የግለቦችን ዓመኔታ፣ ኃላፊነት፣ ተወዳዳሪነት፣ የወደፊቱን አስቀድመው መለየት የሚችሉ መሆናቸውን እና ሌሎች ጸጋዎችን ተጠቅመው ከሁለንተናዊ የዕውቀት ምንጭ ተጠቃሚነታቸውንና ለዕውቀት ምንጮችም ዋቢ ተሳታፊነታቸውን ማረጋገጥ አግባብነት አለው፡፡

የዕውቀትና ልማት ትስስር ከግለሰቦች፣ ከቤተሰብ፣ ከማኀበረሰብ፣ ከተቋም እና ከአምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የፖለቲካና የልማት አመራሮች ድረስ በልዩ ልዩ ደረጃና ጥራት በሚላኩ እንቅስቃሴዎች የተገነባ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም እነዚህ አካላት ተያይዘው ሲንቀሳቀሱ የዕውቀትና ልማት ውሎችን ያጠናክራሉ፡፡

የዕውቀትና ልማት ትስስርሐሳብን እንደሚከተለው አጠር አድርጐ ማየት ይቻላል፤

- ዕውቀትን ለልማት አጋዥነት ያለውን ሚና አጉልቶ ለማየት የዕውቀት ሥነ-ምኅዳሮችን አካታች፣ ያላፈነገጠ፣ ተዓማኒ፣ ነፃ፣ ኃላፊነት የተሞላበት፣ ተጠያቂ እና ግልጽ መሆኑን ማረጋገጥ፤

- የዕውቀት ሥነ-ምኅዳር ሰዎችን፣ ተቋማትንና ድርጅቶችን እንደ ዕውቀት ጸጋዎቻቸው በሚገባ የተሳሰረ እንዲሆን ማድረግ፤

- በተለይ በወጣቶች፣ በሴቶች እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ዙሪያ የሚታዩ የተጋላጭነትና ሌሎች ክፍተቶችን ለመሙላት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፤

- ዕውቀትን ማዕከል አድርጎ የሚንቀሳቀስ ማኅበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ተባብሮ የመሥራት ባሕልን በማጐልበት የፖለቲካ መቀስቀሻ ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ኑሮ በአወታዊ መልኩ ከመቀየር ጋር አስተሳስሮ ማየት፤

- ዕውቀት የሴት፣ የወንድ፣ የዚህኛው ሃይማኖት፣ የዚያኛው ብሔር ወዘተ.. ብሎ ለውጥ በማይታይበት ሁኔታ የግለሰቦችን ሕይወት ማለትም ኑሮ፣ ጤንነት፣ ትምህርት፣ እምነቶች፣ መብት ኃላፊነትንና ግዴታንከነባራዊና ተጠባቂ ሁኔታዎች ጋር መላመድንና መቋቋምን እንዲወሠራ ተገቢው ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርለት ይገባል፤

- የተፈጥሮ ሀብትን በሚገባ በመንከባከብ መጠቀም፤

- ጥራት ያለው የትምህርትና ስልጠና አቅርቦትን እውን በማድረግ ማኅበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

- ዓለማቀፍ የመረጃና የዕውቀት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

- የብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ሥብጥርና የቋንቋ አጠቃቀምን ማክበር፣

- አገራዊ ሉዓላዊነትን በማስቀደም አገር-በቀል የዕውቀት ምንጮች በሥርጐ-ገብ አላስፈላጊ የዕውቀት ምንጮች እንዳይዋጡ ጥንቃቄ በማድረግ ጠቃሚውን ብቻ በመውሰድ ከአገርኛ የዕውቀት ምንጮች ጋር አቀናጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ለአገር-በቀል የዕውቀት ምንጮች መጐልበት ምቹ አደረጃጀትና ፖሊሲዎችን ለመተግበር ሙሉ ዝግጁነትን ማረጋገጥና ለተግባሩም በሚገባ መንቀሳቀስ ተገቢነቱ አያጠያይቅም፤

- የዕውቀት ምንጮች ከገጠር እስከ ከተማ ተያይዘው ልማት አጋዥ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

- የልማት የዕውቀት ሥነ-ምኅዳራት በጠንካራ ግንኙነትና ትብብር ራዕይንና ግብን በመጋራት የሚጐለብቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይህ በውድድር ላይ የተመረኮዘ መሆኑንም ማጤን ተገቢ ነው፡፡

እነዚህ የውድድር ሂደቶችም ማኀበረሰብ ችግሮችን ወይም ፈተናዎችን በመጋፈጥ፣ መልካም አጋጣሚዎችን በመቀመር ጠቀሜታቸውን ማጉላት እንጂ በቀላሉ አገላለጽምሑራዊ ትንተና መስጠትና ከግንዛቤ ውጭ ፋይዳቸው አናሳ የሆኑ አስተሳሰቦችን ለሕዝብ ማቅረብ ተገቢ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በሌላ መልኩም ሕዝብን በሰፊው የማይጠቅም ለጥቂቶቹ ብቻ እርካታን የሚሰጥ መሆንና አለመሆኑን በመለየት እንደአግባቡ መጠቀም ይገባል፤

- የዕውቀት ሥነ-ምኅዳር በሙያ ስብጥር ያልተገደቡ ውይይቶችን ያበረታታል፡፡ የወል ጥቅም ያላቸውን ዕውቀቶችን ለመጋራት የሚተጋ ተሳታፊ ማኀበረሰብን ከመገንባት አንጻር የጐላ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ያለጥርጣሬ መውሰድ ይቻላል፤

- ዕውቀት የሚጐለብተው ከነባራዊ ሁኔታዎች እና ከነባር የዕውቀት ምንጮች መሆኑን መረዳት በራሱ ዕውቀት ነው፡፡ የዕውቀት ለልማት አጋዥነቱም ቅኝት መነሻው ከዚሁ መሆኑን ልብ ይሏል፣ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ የዕውቀት ምንጮችም ይህን ጉዳይ አጉልተው ያዩታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአካባቢ መሪዎች በዕውቀት ምንጭነታቸው ይጠቀሳሉ፤

- ልማትን በዕውቀት ለመቃኘት የግለሰብ፣ የተቋምና የድርጅት ተስፋን ከማለምለም ባሻገር የግብ ስኬትን በሚያጓጓ መልኩ እንደሚያቀርብ ይታወቃል፤

- የሰዎችን ዕውቀትና ክህሎት የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም በጋራ መርሖች እና ራዕይ ላይ ተመርኩዞ የትብብር መንፈስን በመፍጠር ተቻችሎ ከአንድ ሁለት ይሻላል በሚል ብሂል መጓዝ ወሳኝነቱ አያጠያይቅም፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ዕውቀትን መጋራት፣ መማማር፣ የጋራ ፈጠራ፣ የጋራ ትግበራ፣ የጋራ ጥበቃን እና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፤

- ዕውቀትን ለልማት አጋርነቱ የበለጠ ተሳትፎን ለማምጣት የግል፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት ድርጅቶች ተቀናጅተው ቢሠሩ ውጤቱ የላቀ እንደሚሆን መረዳት ቀላል ነው፡፡ ሆኖም በእነዚህ የተቋማትና ድርጅቶች ይዞታ ሥር ያሉ የዕውቀት ምንጮች ተደራሽነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊወሰን ይችላል፡፡ ለተፎካካሪነት የሚጠበቁ የዕውቀት ምንጮች ምንጊዜም ሲሆን ተደራሽነታቸው ከባድ ወይም ምስጢራዊ እንደሚሆን መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም የጋራ ዓላማና ግብ ይዘው ሲንቀሳቀሱ ግን የትብብር ውጤቱም ሆነ ግዴታው በሚያዘው መሠረት ዕውቀትን በደርጅቶች መካከል በግልጽና በጋራ መጠቀም ለጋራ የግብ ስኬት እምብርት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተለያዩ ድርጅቶች እና ተቋማት የሚገኝን የዕውቀት ጸጋ ለጋራ ዓላማና ግብ መጠቀም እንዲቻል የዕውቀት ማኔጅመንት ሁኔታው በውል ታስቦበት፣ ታቅዶ እና ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፤

- ከግለሰብ ወይም ከአዕምሮ ውስጥ ከታጨቀ ያልተፈረጀ ዕውቀት ውጭ የተደራጀ ዕውቀት ምንጮቹ ቤተመዛግብት፣ ቤተመጻሕፍት፣ ቤተመዘክር እና ሌሎች ተቋማት በሥርዓት ተደራጅተው በአግባቡ ተደራሽ ሆነው መገኘታቸው ለወቅታዊ የዕውቀት ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ትውልዶች ጠቃሚነታቸው ምንም ማጣጣያ ሊያድርባቸው አይገባም፡፡ በተጨማሪም ዕውቀትን ማዕከል አድርጐ የሚንቀሳቀስ ማኅበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ሚናቸው የላቀ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ተቋማት ተደራሽነታቸው በተቻለ መጠን ሁሉንም ዕውቀት ፈላጊ አሳታፊ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ተቋማዊ እይታ ወሳኝ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ሂደቱ የዕውቀት ዲሞክራሲያዊነትን ከማሳለጥ አንፃር የሚጫወቱት ሚና ግልፅና የላቀ በመሆኑ ነው፤

- ዕውቀት የልማት አጋዥነቱ የማያጠራጥር ቢሆንም በይዞታነት የተቀመጠ ዕውቀት ሁሉ በአግባቡ ተለይቶ አግባብ ላለው ልማት አጋዥ እንዲሆን ማድረግ ብስልን ከጥሬ ለይቶ መጠቀም መሆኑን ለአፍታም ችላ የማይባልበት ጉዳይ ነው፡፡ ጥርጣሬን የሚጭሩ

ወይም አግባብነት የሌላቸው ክምችቶችን ለይቶ ማስቀረትግለሰብንም ሆነ ማኅበረሰብን ከመንከባከብና ከማብቃት አንፃር መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን የዕውቀት መምረጥ ጥረትን ለማጐልበት ተጠቃሚዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ ርዕሰ-ጉዳዮችን ከትምህርት ተቋማትና ማሠልጠኛ ማዕከላት ጋር ትስስር በመፍጠር የተሻለ ክህሎት ማግኘት እንዲችሉ ተቋማትና ድርጅቶች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከውጭ ከተገኙ የዕውቀት ምንጮች በላቀ ሁኔታ አገራዊ ምንጮችን መጠቀም በውጤታማነቱ የሚፎካከሩት ጥቂቶች መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር ቢቻልም፣ የላቀ ዕውቀትን ከመሻት አኳያ የውጭ ምንጮችና መጠቀም የግድ ይላል፡፡ ይህም አማራጭ ችግር ፈቺ መፍትሔዎችን ከማቅረብ አንፃር የላቀ ሚና ይኖረዋል ብሎ መቀበል ይቻላል፤

- ወቅታዊና ነባራዊ የልማት ማነቆዎችን ከመፍታት በተጨማሪ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ በሰዎች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ እንዲሁም የሚያመጡትን ክፍተት ከመለየትና አግባብ ያለው ምላሽ ለመስጠት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥግ የያዙ ዕውቀቶች ከመሠረታዊ ጥንካሪያቸው በተጨማሪ አጋዥነታቸው ያየለ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ ስለሆነም በአግባቡ ሊገኝ በሚችል ሁኔታና የጠቀሜታ ፈርጅ ተደራጅቶ መገኘት እንዳለበት በሰፊው የተመሰከረለት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዕውቀት ጠቀሜታን ለማጐልበት በቅድመ ሁኔታነትም ይጠቅሳል፣

- የዕውቀትና ልማትን መስተጋብር ከማጠናከር አንፃር የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማንኛውም ጊዜ፣ ሁኔታና ቦታ ወሳኝነታቸውን በድጋሚ ማብሠር አሰልቺ እንደማይሆን እምኛለሁ፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ ቴክኖሎጂዎች መነጠል የዕውቀት ለልማት አጋዥነትን ያሳጣል ቢባል ስህተት እንደማይሆን ይታመናል፡፡ ሆኖም ሌሎች የዕውቀት ምንጮችና ማሳለጫዎች ለምሳሌ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ እና የሰዎች የፊት ለፊት የሐሳብ መጋራት አስፈላጊነታቸው የሚቀጥል እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ የዕውቀትና ልማት ጥምረትን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ደረጃውን የጠበቀ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት መዘርጋት፣ የዲጂታል የዕውቀት ምንጮችን አቅርቦት ማሳደግ፣ የዕውቀት ማኔጅመንት አገልግሎት አቅራቢዎችን የባለሙያነት አቅም ማሳደግ፣ የዕውቀት አገልግሎት ስብጥርን ማሳደግ፣ ተቋማት የዕውቀት ማኔጅመንት እንደ ተቋም አደረጃጀትና ተግባር መውሰድ እንደሚገባቸው ማድረግ፣ የዕውቀት ተደራሽነትን መከታተል፣ መገምገምና ግብረ-መልስ እየቀረበ በየጊዜው የሚሻሻልበትን መንገድ መሻት ተፈላጊ ጉዳዮች መሆናቸውን ተቀብሎ መተግበር ሊተኮርባቸው ይገባል፡፡

t.me/BooksandYou

# ፈጠራን በዕውቀት መታደግ

እንደሚታወቀው በአሁኑ ጊዜ ማንኛውም ልማት በውድድር ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግልጽ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ ገበያን ወይም ትርፍን ማዕከል ያደረገ ልማት ወይም ንግድ የሙሉ ጊዜ እንቅስቃሴው የውድድር መድረክ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚና በእጅጉ እያደገ እንደመጣ በርካቶች ይስማሙበታል፡፡ በተጨማሪም የልማቱ ወይም የንግድ እንቅስቃሴው ተጠቃሚዎች ፍላጐት መጨመር፣ የግንኙነት አውታሮች መመንደግ፣ ዓለምአቀፋዊ የገበያ ሁኔታዎች መወሳሰብና የመሳሰሉትየዘመናችንን የልማትና የንግድ እንቅስቃሴ ባሕሪያት ወሳኞች እንደሆኑ በርካታ የመረጃ ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን የልማትና ንግድ ባሕሪያት ወሳኞችን በመቋቋም ትርፍንና የማኅበረሰቡ ተጠቃሚነትማሳደግ

የግድ ይላል፡፡ ይህ የማምረትንና የአገልግሎት አሰጣጥን ከማሳለጥ በተጓዳኝ የዕውቀት አቅርቦትን ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ተጠቃሚነትን እና አትራፊነትን ማንሰራፋት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የማምረትንና የአገልግሎት አሰጣጥን ትርጉም ባለው መልኩ ለማሳለጥ  በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የምርትና የአገልግሎት አሰጣጥ ማኔጅመንትን ወደላቀ ደረጃ ማሳደግ ቸል የማይባልበት የዘመኑ ጉዳይ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ፈጠራን በዋቢነት ተገን አድርገው ለመንቀሳቀስ ያለሙ ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉየልማትና የንግድ ተቋማት ካላቸው እንቅስቃሴ አንፃር ውስጣዊ የዕውቀት ጸጋቸውና ተተግባሪነቱ የማያዋጣ ሆኖ ሲያገኙት በዕውቀት ማኔጅመንት የተካኑ አመራሮችን በቅጥር ወይም በሌላ አመቺ ሁኔታ በማሳተፍ አስፈላጊ ሲሆንም የሥራ አመራሩን ለሌሎች ተቋማት አሳልፈው እንደሚሰጡ የሚታወቅ ጉዳይ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ለምሳሌ በ2000 ዓ.ም. አካባቢ የኢቲዮቴሌኮም ማኔጅመንቱን ለአንድ የፈረንሳይ ኩባንያ ለተወሰኑ ዓመታት ሰጥቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የዚህ ዓይነቱ አካሄድ ውድድሩን ከማሳለጥና ተቋማዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ከማጐልበት አንፃር ተገቢ አካሄድ ቢሆንም በጥልቅ ጥናት ወይም ዕውቀትን ከተለያዩ

አቅጣጫዎች በመጠቀም ሊተገበር እንደሚገባ መገንዘብ ራሱ አዋቂነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ውጤታቸው ውድቀትን ያመቻቸ እንደነበር በርካታ ተሞክሮዎች ይጠቁማሉ፡፡

ኢኮኖሚያቸው በእጅጉ ባደጉ አገሮች እንደሚታየው ለፈጠራ ሥራዎች የላቀ ትኩረት እንደሚሠጡት ነው፡፡ በተጓዳኝም የፈጠራ ሥራዎች በአግባቡ እንዲመሩና የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያበሥሩ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ እንቅስቃሴም የዕውቀት ዋቢነት ከምንጊዜወም በላይ ጐልቶ እየወጣ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ዕውቀት የተቋማትንና የድርጅቶችን እሴቶች ከመፍጠርና የፈጠራ አመራርን በጥንካሬ ለማስኬድ ወሳኝነቱን ለማረጋገጥ መሠረታዊ እንቅስቃሴዎች እያየሉ የመጡበት ወሳኝ ዘመን ውስጥ ያልገባ ጉዳይ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በመሠረታዊነት የፈጠራ አመራርን አስፍኖ የሚበጠቅ ውጤትን ለማምጣት በሚያስችል መልኩ ፈጠራ የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ መስጠቱ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም ለዚህ ምዕራፍ ቅርብ የሆነ ትርጉም በሚል መልኩ ሲተነተን **"የፈጠራ ማኔጅመንት ወይም አገልግሎት የአዲስ ፈጠራ፣ የሂደቶች፣ እና የውጤቶች**

**መስተጋብር ሆኖ አዲስ ምርት፣ አዲስ አገልግሎት እና አዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ማቅርብ”** ብሎ ማየት ይቻላል፡፡

የፈጠራ ማኔጅመንትንና ራሱን ፈጠራን ውጤታማ ለማድረግ ለሚከተሉት መርሖዎች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

- ሃሳቦችን ማፍለቅ፤
- ሐሳቦችን መተንተን/መፈተሽ፤
- ሐሳቦችን ወደተግባር ማሸጋገር፤
- ትግበራውን መገምገም፤
- እና ሌሎችም .....

ሐሳብ ማፍለቅ የሚለው መርሕ ትኩረቱ በፈጠራ ሂደቶች ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ አፈጻጸም በጋራ ውይይት ላይ የተመሠረተ የፈጠራ ጸጋዎችን ለመለየት የተሳትፎ መድረክ ነው፡፡ ከቀረቡት ሐሳቦች ውጤታማ ወይም ጸጋ ያላቸውን መለየት ትኩረት ይደረግበታል፡፡

ሐሳብ መትንተን ወይም መፈተሽ የሚለው ደግሞ የተመረጡትን ባለጸጋ ሐሳቦች ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የፍተሻ ሥራ የሚሠራበት ነው፡፡ የተመረጡና የተፈተሹት ሐሳቦች ወደተግባር ገብተው ሂደታቸው በሚገባ ነጥሮ የሚጠበቀው ውጤት (ምርት ወይም አገልግሎት) ትርፋማ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ በተያያዘ መልኩም ለውጤቱ ዕውቅና ወይም ማረጋገጫ መሻት፣ ማስተዋወቅና በገበያ ውስጥ የላቀ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ አጥብቆ ይሻል፡፡

በጨረሻም ከሐሳብ ምንጮች እስከ ምርት ማቅረብ ወይም አገልግሎት መስጠት ድረስ ያለውን ሂደት በመገምገም ለቀጣይ የፈጠራ ሐሳቦች ዝግጁ ሆኖ መገኘትን አጥብቆ ማቀድና መተግበር ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ለአፍታም ቸል የማይባልበት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የፈጠራ አመራር እና ሂደቶች ቀልጣፋና ውጤታማነታቸውን በቅኝት ውስጥ ለማቆየት አሁንም የዕውቀት ማኔጅመንት ሁነኛ አጋር እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡
የፈጠራ እና የዕውቀት ማኔጅመንት ትብብርን ዘመኑ ከሚጠይቀው የአመራር አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ሲታይ

ከለውጡና ከተቋማዊ ሽግግር አንጻር ሊታይ ይገባል፡፡ ትስስሩም የላቀ ድርጅታዊ አገልግሎት ወይም ምርት ከማቅረብ አንጻር እንዲሁም ከአደረጃጀት ጋር ተቀናጅቶ መታየቱ አግባብነቱ የላቀ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ በፈጠራ ላይ ያተኮረ ውጤት የዕውቀት ማኔጅመንት የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል ቢባል ማጋነን እንዳልሆነ ቀደም ሲል የቀረበው ሐሳብ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡ የሁለቱ ትሥሥርም በዚሁ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡

በማንኛውም መለኪያ ሲታይ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ፈጠራ ውጤቱ በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚታይ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የሁለቱ ቅንጅት የማያገኘውን ውጤት ተዓማኒና በቀጣይነት ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ የሠራተኞችና የአመራር ልባዊ ቁርጠኝነት ይሻሉ፡፡

በመጨረሻም ተቋማትና ድርጅቶች እሴቶቻቸውን መሠረት አድርገው ለፈጠራ ሥራዎቻቸው ውጤታማነት ሳይታክቱ አዳዲስ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓትን መገንባትና በቀጣይነት ማጐልበት እንደሚገባቸው መጤን ይኖርበታል፡፡ በተለይ ለዕውቀት ማኔጅመንት ባለሙያዎቻቸው ትኩረት በመስጠት ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ማድረግ እንደሚገባቸው ሊያጤኑትና በዕቅድ ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡ ይህን እና ሌሎች አስፈላጊ

ጉዳዮችን ከዕቅድ በዘለለ መልኩ ሲተገበር ግስጋሴው ውጤታማና ትርፋማ የሆነ ተቋም ወይም ድርጅትን መምራት እንደሚቻል ማመን ይቻላል፡፡

ግለሰቦች፣ የተቋም ሠራተኞችም ይሁኑ አመራሩ ለፈጠራ ትኩረት ሰጥተው የመጨረሻ ውጤቱ አመርቂ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ለውጤቱ አመርቂ መሆን ከልብ መትጋታቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡

# ትረካና ዕውቀት ማኔጅመንት

ትረካ በሰው ልጅ የአዝጋሚ ለውጥ ሂደቶችንና ታሪካዊ ክሥተቶችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ተሞክሮዎችን ተገን አድርጎ እያደገ የመጣ ክሥተት ነው፡፡ የትውልድ ሽግግር ሳይበግረው ይዘቱንና አካሄዱን ጠብቆ የዘለቀ ዋቢ ቅርስ ቢኖር ትረካ ወይም ተረክ ለመሆኑ ጥርጣሬን የማይጭር ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያት ደግሞ ተረክ ግንኙነትን ለመፍጠርና መልእክትን በቀላሉ ለማስተላለፍ ቀላልና አመቺ መሆኑ በስፋት ይገለፃል፡፡

የተረክ እሴቶች ዋነኛ መገለጫዎች ደግሞ የተወሳሰቡና ድርብርብ ሐሳቦችን በቀላሉ ማስተላለፍ ማስቻሉ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ በመሠረቱ ትረካ እና ማነቃቃት መልእክት በቀላሉ እንዲተላለፍ በማድረግ የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ በተጨማሪም ግጭቶችን ወይም አለመግባባቶችን

በማርገብ ሚናቸው የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ለመማማርና ተግባብቶ ለመዝለቅ የራሳቸው አስተዋጽኦ እንዳላቸው መጠቆም ይቻላል፡፡

በተቋም ደረጃ ሲታይ ተረክ የሚተረከው በተለያየ መንገድ ሲሆን ዋና ግቡም የተቋሙን እሴቶች፣ ደንቦች፣ ለውጦች እና ሌሎች ተቋማዊ ጉዳዮችን ማስረፅ ነው፡፡

ዕውቀትን መሠረት አድርገው ለሚንቀሳቀሱ ተቋማትና ድርጅቶች ተረክ አንዱ የዕውቀት ማሸጋገሪያና ማጋሪያ መሣሪያ መሆኑን በውል ይገነዛባሉ ወይም ሊገነዘቡትና ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ ስለሆነም ዓለምአቀፋዊ ሂደቶችን ዋቢ በማድረግ ዘመኑ ትረካን ለአንድ ተቋም ወይም ድርጅት በውጤት ለመዝለቅ እንደ አንድ አስተማማኝ መሣሪያ መጠቀም አስተዋይነት ነው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

በመሠረቱ ተረክ ቀደም ያሉ ሁነቶችን እና አጋጣሚዎችን በመጠቃቀስ ወይም በርዕሰ-ጉዳይነት በማንሳት የሚቀርብ መረጃ እንደሆነ ጠቅለል አድርጐ መግለጽ ይቻላል፡፡ ተረክ እንደሁኔታው ወይም እንደመረጃው ተዓማኒነት ሊቀርብ የሚችል ሲሆን አንዳንዴ በመረጃው መራቅ፣ ግልጽ ያለመሆንና ተደጋግሞ

ሲነገር በሚደርሱ መፍሰሶች ምክንያት ሊዘበራረቅ እንደሚችል ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በሌላ ጐኑ ሲታይ ተረክ ለችግር መፍቻ የሚሆኑ ተሞክሮዎችን እንዲይዝ አድርጐ ማቅረብ የተራኪውን የዕውቀት ምሉዕነት ያሳያል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በተቋም ወይም በድርጅት ስም የሚቀርቡ ተረኮች እንደሁኔታው ጽንሰ-ሐሳባዊና በተግባር የተፈተሹ መረጃዎችን ያቀርባሉ፡፡ ከተጻፉና በሐሳብ ደረጃ ከሚገኙ ምንጮችም ሊቀዱ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተረኮች የዕውቀት ምንጭነታቸው ብቻ ሳይሆን በቀላሉ ሊጋሯቸው የሚችሉት እና የተቋም ባልደረቦችን በማነቃቃትና በማትጋት ሚናቸውን የላቀ እንደሆነ ይታመናል፡፡

የትረካ መንገዶች በአብዛኛው በቃል የሚተላለፉ በመሆናቸው ተረኩ በግልጽ እንዲተላለፍ ተራኪው ጥንቃቄ ሊወስድበት ይገባል፡፡ ሆኖም በጽሑፍ ተረኮች ሲተላለፉ በቃል እንደሚተላለፉት ሁሉ ተራኪው የተረክ አጻጻፍ ክህሎት እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡ የጻፈውንም በአግባቡ ሊተርከው ይገባል፡፡ ለዚህም ልምድ ማዳበር ወሳኝ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተረክ የሁነቶች ተከታታይነት መሠረት አድርጐ የሚቀርብ መሆኑን ተረድተናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ትረካ ደግሞ እነዚህን ሁነቶች በዓይነትና በይዘታቸው መሠረት ለታዳሚው ማቅረብን ያካትታል፡፡ ሁነቶችን በሙሉ ወይም እንዳሉ ማቅረብ አስቸጋሪ እንደሚሆን ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ ስለሆነም እንደጥንካሪያቸው ወይም እንደ ተዓማኒነታቸው አንዳንድ ሁነቶች ወይም ክሥተቶች ሊዘለሉ ወይም ተቆርጠው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ይህም የተራኪውን ክህሎት ይሻል፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ ትረካ ተረክን ያሳልጣል ብሎም ተዓማኒ ወይም ተሰሚነት ያላቸውን ሐሳቦች ለማሸጋገር ዋቢ መሣሪያ መሆኑን በድጋሚ መግለጽ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

በአንድ ተቋም ወይም ድርጅት ውስጥ ተረኮች እጅግ አስፈላጊ መሆናቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ በእለት ውሎዎች ውስጥ ትርጉም ያለው ሚናቸው የላቀ ነው፡፡ እነዚህ ተረኮች በተፈጥሯቸው ተደራጅተው የተቀመጡ ምንጮች አይደሉም፡፡ ይልቁንስ ከክሥተቶች ወይም ሁነቶች፣ ከስኬቶች፣ ከውድቀቶችና ከሌሎች ልዩ ሁኔታዎች ጋር ተዛምደው ሊቀርቡ የሚችሉ መሆናቸውን በእርግጠኝነት ማስገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተቋማትና ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው ተረኮችምንጮቹም የተቋማቱ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሮች፤ በሥራ ላይ ያሉና የሌሉትን ያካትታል፡፡ ይህ የሚጠቁመው ተቋማትና ድርጅቶች በተራኪዎች ሲጣሉ፣ ሲነሱ፣

ሲንኳሰሱና ሲሞገሱ እንደሚውሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየን ተረኮች የሚተረኩት የተቋማትን እሴቶች፣ ግቦችና ባጠቃላይ ባሕሎችን መሠረት አድርጐ የግብ ስኬትን ማምጣት ላይ ትኩረት በመስጠት ነው፡፡ የተቋም ሠራተኞችን፣ ባለሙያዎችንና አመራሩን፣ አመለካከት እና ባሕሪን ለማቅረብና በተቋም እሴቶች ላይ እንዲታሰሩ ለማድረግ ብቃት ያላቸው መሣሪያዎች ናቸው፡፡

በተቋም ደረጃ ሲታይ ተረክ በዕውቀት ምንጭነቱ ተግባራዊ እንደሚደረግ ይታወቃል፡፡ በዘመናዊ ተቋማትና ድርጅቶች ተረኮች በደንብ እንዲቀርቡ ከተደረጉ ለግብ ስኬት ዋቢ መሣሪያነታቸው አያጠያይቅም፡፡ ሰብዓዊ ግንኙነቶችንም ለማጠናከር አመቺ ናቸው፡፡ ተቋማትን ከደንበኞቻቸው ጋር የጠበቀ ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ይጠቀሳሉ፡፡ ስለሆነም ተረክ ነባር የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ለዘመናዊ ተቋማት ዘላቂነት እየጐላ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ በዓላማ ላይ የተመረኮዘ ተረክ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ወይም ሰፋ ያሉ የማኅበረሰብ አካላትን ማዳረስ የሚያስችል ብቃት እንዳለው መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ተረክ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽንስ ቴክኖሎጂዎችን በዋናነት አይፈልግም፡፡ የሰዎችን አንደበት ግን በውል ይሻል፡፡ በዚህ እና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ሳቢያ እንዲሁም

በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ አወንታዊ ምላሽ የሚገኝበት መድረክ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ማንም ሰው ተራኪ መሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ነውሁሌም ተረክ ማቅረብ መቻላችን፡፡ ይህ ሲሆን ግን በእርግጠኝነት ግንዛቤ ወስደንበት አለመሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም፡፡ ተራኪነታችንን ግን በውል ብንገነዘበው በሂደት የተዋጣለት ተራኪ መሆን መቻላችንን መመስከር የምንችል ይመስለኛል፡፡ ተራኪ ብቻ ሳይሆን ለተቋማችን ስኬት አስተዋጽኦ ለማድረግ ብቃት እንዳለን መገንዘብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አዕምሯዊ ዕውቀትን ለመተግባር የሚያስችል ቁመና እንዳለንም ልብ ልንለው ይገባል፡፡ ለዚህም ነው ተረክ የዕውቀት ማኔጅመንት ጠንካራ አጋዥ መሆኑን መመስከር እና መገንዘብ የሚገባን ምክንያቱም ተረኮች ትርጉም ይሰጣሉ፣ አዕምሯዊ ዕውቀት ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ያግዛሉ፡፡ በተጨማሪም ለዕውቀት ሽግግር ተፈጥሯዊ ባሕሪያቸው የላቀ ነው፡፡ ዕውቀትን የሚሹ ለተረኮች ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ውስብስብ ሐሳቦችን ቀለል አድርጐ ለማቅረብ ተረኮች ግንባር ቀደምት ናቸው፡፡ በባሕል፣ በአስተሳሰብና በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች የተሰባጠሩ

የማህኀበረሰብ አካላትን ለሚቀራረብ የተረኮችን ተፈላጊነት የጐላ ያደርገዋል፡፡

ተረኮች በራሳቸው በቀላሉ የሚዳረሱ ናቸው፡፡ ለዕውቀት በቀላሉ መዳረስ መቻል ልዩ መገለጫው ነው፡፡ ውጤታማ እና ተዓማኒ ተረክ እንደሰደድ እሳት በቀላሉ የሚዳረስ ነው፡፡ የሕትመት ባለቤትነት የማይመለከተው የዕውቀት ማሸጋገሪያና መጋሪያ መሣሪያ በመሆኑ በቀላሉ ለመዳረስ መቻሉ አንዱ ምክንያት እንደሆነ መግለጽ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተራኪዎች በራሳቸው ስልት ተረክ ማቅረባቸው ለፈጣን ተደራሽነቱ ሌላው መገለጫ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ለተረኮች ባለውለታነት በርካታ ተጨማሪ መገለጫዎች እንዳሉ ልብ የሚሉት ጉዳይ ነው፡፡ ተረኮች ለአዕምሯዊ እና ለተግባራዊ ዕውቀት ድልድዮች መሆናቸው ሌላው መገለጫ ነው፡፡ቀደምት ጀግኖችን እያወደሱ ለአዲሱ ትውልድ ማቅረቡ የእነዚህ ጀግኖች ተምሳሌነት ለዚህኛው ትውልድ የላቀ ትርጉም እንዳለው ለመመስከር ያስችላል፡፡

ተረኮች ቀደምት ክሥተቶችን ማወደስ ብቻ ሳይሆን የተራኪውን ስብዕናም ለመመዘን ማስቻላቸው ነው፡፡ ተራኪው የመረጣቸው

ተረኮችን በራሱ ጭብጥ ሳይስት አገላለጽ ማቅረቡና አድማጩን ማሳመን መቻሉ የብቃቱ መገለጫ እንደሆነ ማመን ይቻላል፡፡

የተረክ አድማጮች መልዕክት ሰሚዎች ብቻ አለመሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ አድማጮች ተረኩን ሊቀበሉትም ሆነ ላይቀበሉት ይችላሉ፡፡ አንዳንዴም ለራሳቸው ፍላጐት እርካታ ተረኩን ተርጐመው ወይም አሻሽለው ሊቀበሉት ይችላሉ ብሎ ማሰብም መልካም ነው፡፡

ዕውቀትን ለማሸጋገርና ለመጋራት በሚል ዓላማ የሚቀርቡ ተረኮች በተቻለ መጠን በሚታመንና እርግጠኝነቱ በታወቀ ምንጭ ለመፍለቃቸው በቅድሚያ ሊተኰርበት የሚገባ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ይህም መማማርን በሰፊው ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል፡፡

ጠቅለል ብሎ ሲታይ ተረክና ተቋማት የሚተሳሰሩበት ገመድ መገለጫዎች እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፡፡

- ተረኮች የተቋም እሴቶችንና ደንቦችን ለመጋራት ዋቢ ናቸው፤

- በተቋም ውስጥ የሥራ ተነሳሽነትንና መተማመንን ይፈጥራሉ፤

- አዕምሯዊ ዕውቀትን ለመጋራት ምቹ ናቸው፤
- ለስሜታዊ ትስስሮች ምንጮች ናቸው፤
- እና ሌሎችም .....

ስለሆነም ተረክና ትረካ የተቋማትና ድርጅቶች ግብ-ስኬት ትርጉም ያለው ዕውቀትን በማስራጩት ይታመናሉ፡፡ በተቋማት መካከል መደጋገፍንና መተባበርን ያጠናክራሉ፣ ለተቋማት ተፈጥሯዊ የግንኙነት መሣሪያዎች ናቸው፣ የማኅበረሰብን ባሕልና ታሪክ በማስገንዘብ የላቀ አስተዋጽኦ አላቸው፣ ማኅበራዊ መማማርን ያጐለብታሉ፣ የምሁራንን የዕውቀት ጸጋ ለማካፈል ያመቻሉ፣ ባሕላዊ ለውጥን ያበስራሉ፣ እንዲሁም ውስብስብ ሐሳብን በቀላሉ ተደራሽ ያደርጋሉ፡፡

ዕውቀት ሲተረክ ማኅበረሰቡ እንዲወስደውና እንዲጠቀምበት መደረግ አለበት፡፡ ካልሆነ መነቃነቅ የተሳነው የኩሬ ውሃ መሆኑ አይቀርም፡፡ የመረጃ እና ዕውቀት መከዘኛ ሥርዓቶችን ማድመቂያ ከመሆንም አያመልጥም፡፡ ይህን ተያያዥነት ለማጥለቅ ተተግባሪና ለዋጭ ዕውቀቶች ለማኅበረሰብ ጥቅም እንዲሰጡ ሆነው ሊተረኩ ይገባል፡፡

# ዕውቀት ማኔጅመንትና ፖለቲካዊ አንደምታው

የ21ኛው ክፍለ ዘመን አንዱ መገለጫው የዓለም ኢኮኖሚ በዕውቀት ላይ ያተኮረ መሆኑ በግልጽ እና በስፋት የሚወሳ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት ከፖለቲካዊ አካሄድ ተነጥሎ ሊታይ የማይችልበት አካሄድ እንዳለ ማጤን ግድ ይላል፡፡ በተለይ ይህ ጉዳይ ጐልቶ የሚታየው ዕውቀትን ለይቶ ጥቅም ላይ ለማዋል በሚደረግ ጥረት በሰዎችና በድርጅቶች መካከል በሚከሠት ተግባቦት የፍላጐት መጣረስ የሚያስከትላቸው ግጭቶች በመልክም ሆነ በይዘት የተወሳሰቡ መሆናቸው በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይ የዕውቀት ምንጮችን ለመመዝበር የሳይበር ቴክኖሎጂን

በመጠቀም የሚደረገው እሽቅድድም ከምንጊዜውም በላይ እያየለ መምጣቱ ነው፡፡ ስለሆነም በተለይ ኢኮኖሚያቸው በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ በመሄድ ላይ ያሉና ልማታቸውንም በከፍተኛ የለውጥ ጉዳና ውስጥ ያስገቡ አገሮች የዕውቀት እሴትን ከምንም በላይ ከፍ ያለ ቦታ የሰጡት በመሆኑ በየዕለቱ የሚታዩት ልማታቸውንና ኢኮኖሚያቸውን ዳር ለማድረስ የሚያስፈልጋቸውን የዕውቀት ጸጋ መቼ፣ እንዴትና ማን ያሸጋግርላቸው ዘንድ ሳይታክቱ ጥረታቸውን መጠቀላቸው ገሀድ ትግል ግለት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከረረ መምጣቱም ይታወቃል፡፡ ቀጣይ ለመሆኑም ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ አይመስልም፡፡ ለዚህም ነው ሰዎች፣ ተቋማት፣ ድርጅቶችና አገራት ዘመኑ ያቀረባቸውን የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽንስ ቴክኖሎጂዎችን ከሰዎች ዕውቀትና ማኔጅመንት ሥርዓታቸውን በመገንባት እና በማጠናከር ተግባራዊ ለማድረግ እየጣሩ የሚገኙት፡፡ ይህም አካሄድ በማንኛውም መገለጫው ጫፍ የያዘ የተቋም አደረጃጀትና አሠራርን ትርጉም ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ አስገዳጅነቱ በግልጽ ይታያል ማለት ያስችላል፡፡

እንደሚታወቀው የሳይበር ቴክኖሎጂ ለዕውቀት ማኔጅመንት የማይተካ ድጋፍ ማድረጉ ተደጋግሞ የተገለጸ ነው፡፡ በተለይ ዕውቀትን በማመንጨት፣ በማከማቸት፣ በማሰራጨት፣

በማቅረብና ለትግበራ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር የላቀ አስተዋፅኦ እንዳለው በእርግጠኝነት ይጠቀሳል፡፡ ለዚህም ነው ዋስትናው የተረጋገጠ የዕውቀት ማኔጅመንት ሥርዓት የተቋማት እንዲሁም የአገራት ልዩ ትኩረት እየሆነ በመምጣት ላይ ያለው፡፡ የዘመኑ መገለጫ የሆነው የሳይበር ቴክኖሎጂ በዋናነት በዕውቀት ድብብቆሽና ተደራሽነት ላይ የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ ጫና እያሳደረ መምጣቱ ግር የሚያሰኝ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ ቀደም ካሉት ዘመናት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ ይለያል፡፡ በተለይ የዕውቀት ተደራሽነትና ድብብቆሽ በአጭር ጊዜ በሴኮንዶች ወስጥ ሊለያይና ኃያልነቱም በግልጽ ሊታይ በሚችልበት አካሄድ ውስጥ መሆኑ ዋነኛ የሁኔታዎች መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንም ከግምት ውስጥ በማስገባት የዕውቀት እሴቶች ፋይዳ በእጅጉ እየረቀቁና ብዝኀነታቸውም እየታዬ መምጣቱን ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡ ለዕውቀት አቅርቦት ቀረቤታ ያላቸው ሰዎች፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ማኅበራዊ መስተጋብሮች በተቻለ መጠን ከዕይታ ውጭ ሆነው ዕውቀትን ለመደበቅ እና እንደአስፈላጊነቱ ለመጋራት በውድድር ላይ የተመራጭነት አካሄድን እየመረጡ የሚገኙት፡፡ ይህም የውስጥና የውጭ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች እጃቸውን እንዲያስገቡ የሚያበረታታ ሁኔታን መፍጠሩ አይቀሬነቱን ያሳያል፡፡ ተግባራዊ

እንቅስቃሴውም በዚሁ ሳብ-ረገብ በሚል ቅኝት ውስጥ የሚሽሎከለከው፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው የዕውቀት ኃያልነትን ብቻ ሳይሆን ተቋማት፣ ድርጅቶችና አገራት የፖለቲካ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ሳይገታ እንዲቀጥል በተግባር እየተጠቀሙበት መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ይህን ጸጋ ለመጠበቅና ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መኖር በራሱ የኃይል መገለጫ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ተደጋግሞ እንተገለጸው ዕውቀት ሁኔታዎችን ድርጊቶችንና እንቅስቃሴዎችን በውል መረዳትን ያገናዘበ መሆኑን መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ዕውቀት አብዛኛውን ጊዜ በአጠራጣሪ ጉዳዮች ላይ ተመሥርቶ ሊከሥት እና ሊወሰድ ይችላል፡፡ እነዚህ አጠራጣሪ ወይም አደናጋሪ ሁኔታዎችን ለይቶና አንጥሮ በማውጣት እሴት የሚጨምረውን ብቻ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ውሳኔን እና ምርጫን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማስቀመጥና ውጤቱም ተዓማኒ እንዲሆን ያደራጋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ድርጅቶች ተፎካካሪዎቻቸውን ለማጣጣል አጠራጣሪና አደናጋሪ መረጃዎችን ያቀርባሉ፡፡ ይህም በውድድር መድረኮች የላቀ ድርሻቸው ሳይቆራረጥ እንዲፈለግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ዕውቀትን ተቀብሎ ከመተርጐም

አንፃር በፈለቀው ዕውቀት ዙሪያ-ገብ የሆኑ አማራጮችን መሻት ግድ ይላል፡፡

ዕውቀትና ኃያልነትን በተመለከተ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተገለጸ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዕውቀት አሉታዊና አወንታዊ ተፅዕኖያሳድራል፣ የአፈጻጸም ደረጃን ይወስናል፣ ለአገራዊና አህጉራዊ ጦርነቶችና እሰጥ አገባዎች ይዳርጋል፡፡ ሆኖም እነዚህና ሌሎች የዕውቀት ተፅዕኖዎች በተፍታታ መልኩ ለሕዝብ ሲደርሱ አይታዩም፡፡ ወጥነት የሚጐድላቸው መረጃዎች በስፋት ሲዳረስ ሲታዩም በመረጃ ምንጭነታቸው እርካታን የሚለግሱ እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም በማኅበራዊና ግለሰባዊ መስተጋብሮች ላይ መተዛዘቦችንና ጥርጣሬዎችን መጫሩ አይቀሬ ነው፡፡ የዚህ ፋይዳውም ፖለቲካዊ መናቆርን ያስከትላል፡፡ በተግባርም እየተከሰተ ለመሆኑ በግልጽእየታዬ ይገኛል፡፡ ለዚህም ነው ዕውቀት ማኔጅመንት ስትራቴጂያዊ ዕይታን ይፈልጋል የሚባለው፡፡ በያዝ-ለቀቅ ተጠቃሚነትን ማምጣት ውጤታማም ትርፋማም አያደርግም ማለት የሚቻለው፡፡ ይህን ግልፅ የሆነ ጉዳይ መቀበልና የዕውቀት ኃያልነትን በተግባር ማስመስከር ልዩ ትኩረት የሚሻ ነው የሚባለው፡፡ የዕውቀት ኃያልነት መገለጫዎችም የሚመነጩት ዕውቀትን ከማመንጨት፣ ተደራሽ ከማድረግና ከማሰራጨት ብሎም ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር

ማየት ይቻላል፡፡ በተያያዘ መልኩ መስተጋብሩ ከዕውቀት ይዘቱ እና ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ሲቃኝ የዕውቀት ተዓማኒነትንና ኃያልነትን ያስመሰክራል፡፡ የውስጣዊ ወይም ድርጅታዊ ጥንካሬንና ተወዳዳሪነትንም በዋቢነት ያሳያል፡፡ በአመራሩም የፈጠራ ሂደቶችን በእጅጉ ያበረታታል፡፡ በተለይ በሳይበር ቴክኖሎጂ እሴቶች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ መንገድ ይከፍታል፡፡

ቀደም ባሉት የዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች እንደተገለጸው የዕውቀት ይዘቶች ሚናቸው ከፍ ያለ መሆኑን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ዙሪያ የሚያተኩሩ ምሁራን ለዕውቀት ይዘት የተለያዩ ትርጉሞችን ይሰጣሉ፡፡ የሰው ሀብት እና ምሁራዊ ካፒታል የሚሉት በተለዋጭ ትርጉምነት ሲያገለግሉ ይታያል፡፡ ይህ የሚጠቁመው ዕውቀት ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች በሰዎች ዋቢነት ወሳኝነቱን ነው፡፡ በተጨማሪም የዕውቀት ይዘት በባሕሪው እንዲሁም በከፍታና ዝቅታው የተለያይነት አዝማሚያው የላቀ ነው፡፡ በተጨማሪም ዕውቀት ከግለሰቦች ተነስቶ የሕዝብ ሃብት መሆን የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት በግለሰብ ደረጃ የፈለቀ ዕውቀት ካለምንምና ማንም ተጽዕኖ ሌሎች ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

ሆኖም ፖለቲካዊ በሆነ አግባብ የዕውቀት ይዘት ሕጋዊ አካሄዶችን ሊከተል ይገባል የሚሉ ወገኖች ጥቂት አይደሉም፡፡ የዕውቀትና ፖለቲካ ግንኙነት ምልከታዊ እንጂ በመቆጣጠር ላይ ያተኮረ ሊሆን እንደማይችል መገመት ይቻላል፡፡ በተለያዩ ደረጃዎች እና የአስተሳሰብ አድማስ ላይ ያሉ ፖለቲከኞች ለዕውቀት እና ለፖለቲካዊ መልእክቶች ፖለቲካዊ ትርጉም ይዘው ተደራሽ ቢሆኑ የሚል መልእክት ሲያስተላልፉ ይታያሉ፡፡ በሌላው አድማስ የሚገኙት ደግሞ የዕውቀት ተደራሽነት ካለምንም ተለጣፊ ወይም አስገዳጅ ሁኔታ መሆን አለበት ብለው ይከራከራሉ፡፡ እነዚህን ሁለት አመለካከቶች በሚያስታርቅ መልኩም ዕውቀት ሕጋዊ መደላድል ኖሮት በተቻለ መጠን ተጠቃሚዎችን በሚያገል መልኩ ተደራሽ ሊሆን ይገባል የሚሉ አስተሳሰቦች ሲንጸባረቁ ይታያሉ፡፡

ሳይበር ፖለቲካን በተለይ ለማየት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ካላቸው በጐ ተጽዕኖ ባሻገር ፖለቲካ በግጭቶች፣ በድርድሮች እና በመግባባት የተሞላ መሆኑን ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡

በሳይበር ቴክኖሎጂ አማካኝነት የዕውቀት ክምችትን ለመምራት በተለይ መሠረታዊ እሴቶችን ትርጉም ባለው መልኩ ለመጠቀም ፖለቲካዊ አመራር ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙን እያጐለበተ

በመምጣት ላይ ነው፡፡ በተለይ ፖለቲካዊ አመራሩ በአገር ደረጃ ጐልቶ ይገኛል፡፡ ለዚህ አገራዊ፣ ፖለቲካዊ አመራርም ተቋማትና ድርጅቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በተለይ የዕውቀት ሽግግርን ማን ሊጠቀምበት ይገባል፣ ለማን ምን ዓይነት ዕውቀት ሊሸጋገርበት ይገባል፣ የዕውቀት ሽግግሩ መቼና እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል የሚሉ ጉዳዮች የበለጠ የፖለቲካ ስበቶች ተጋላጭ በመሆን ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም ዕውቀት ወደ ተግባር የሚሸጋገርበትን አግባብ መልክ ከማስያዝ ጋር ያለው ቁርኝት በመልካም ጐኑ ሊታይ ይችላል፡፡ ሆኖም የፖለቲካ አካሄዱ ዕውቀትን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የአግላይነት ተጽዕኖው የጐላ መሆን የለበትም የሚል እምነት አለኝ፡፡

የተለያዩ አገራት የዕውቀት ክምችቶቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ የሳይበር ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን ይሰጣሉ፡፡ ይህም የዕውቀት ማኔጅመንት እንቅስቃሴና አመራሩን ሕጋዊ እይታ ኖሮት የዕውቀት ልማትና ስርጸት በዚሁ ምህዋር ዓለምአቀፋዊ ግንኙነት ውስጥ እንዲሳተፍ ለማድረግ የሚጥሩት የዚህ ሂደት የውጤት መጠቆሚያዎች በሙሉ በሕዝባቸው ተጠቃሚነት ዙሪያ እንደሚያጠነጥን መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ የዕውቀት ፖለቲካዊ ሥነ-ምኅዳር ዲሞክራሲያዊ ተጠቃሚነት ሁሌም ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ የዕውቀት ምንጮች ተጠቃሚነት ከሰብዓዊ-መብቶች አንጻር ሲታይ ተደራሽነታቸው ግልጽና ቀጥተኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ ድርጅቶች፣ ተቋማትና አገራት ለሉዓላዊነታቸው መገለጫ ዕውቀትን ኢዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሲደብቁ እና አሳሳች መልእክቶችን በመጠቀም ሲያደናግሩ ይታያሉ፡፡ ስለሆነም የዕውቀት ማኔጅመንት ተፈጥሯዊ ሂደቱ በየጊዜው ሲቀያየርና ሲወሳሰብ ማየት የተለመደ ክሥተት እየሆነ መጥቷል፡፡

ሳይበር ቴክኖሎጂ በፈጣን አማራጭነቱ ለዕውቀት ሽግግር ሚናው የላቀ ነው፡፡ ፋይዳውም በግልጽ እየታየ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሆኖም በሳይበር ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ዕውቀቶች ምን ያህል አስተማማኝና ትክክለኛ ለመሆናቸው ጥያቄ የሚያመጣ እንደሆነ በርካታ አሉታዊና ወቅታዊ ሁኔታዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም የሳይበር ዕውቀት ምንጮች አቅርቦትን ዲሞክራሲያዊነት ያጠያይቃል፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደሚጠቁሙት የሳይበር ውጤት የሆነው ለምሳሌ፡- ዊኪፒዲያ በይዘት ደረጃ ሲታይ የሕትመት ውጤት ከሆኑ የዕውቀት ምንጮች ጋር ሲነጻጸር

አስተማማኝነቱ በእጅጉ አጠያያቂ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በእጅጉ አሳሳቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

# የዕውቀት ኃያልነት ሲጠነጠን

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ለመጥቀስ እንደተሞከረው ለግብ ስኬት ተግቶ ከመሥራት አኳያ ግለሰቦችም ሆኑ ተቋማት የዕውቀት ኃያልነትን አጥብቀው ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ጠለቅ ብሎ ሲታይ የአሠራርና የአመራር ጥበብን ማዕከል አድርጐ ለመንቀሳቀስ የሥራ አጋርነትን መሠረት አድርጐ ለመምራት ብሎም ተከታይ አጋርን ለማግኘት፣ ለውጡንም በአዋጭነት ለመምራትና በቂ የትግበራ ጊዜ መስጠት ተገቢ ጉዳይ መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡

እንደሚታወቀው ሐሳብ የትምቦታ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ይፈልቃል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሳይሆን ሐሳቡን በሚገባ ማስረፅና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ዝግጁ ሆኖ

መገኘት ትልቅ ቅድመ-ሁኔታ ነው፡፡ ሐሳቦች ቀድሞ የነበረውን በማስቀጠል የሚገቱ አለመሆናቸውን ለይቶ በመጠቀ ዕውቀት ላይ የተመረኰዘ የለውጥ መንገድን መከተል ችላ የሚሉት ጉዳይ አይደለም፡፡ ሁሌም በአዲስ ሐሳብና ዕውቀት ለትግበራ ዝግጁ መሆን ያዋጣል፡፡ ይህም ያለምንም ቆምታ ቢቻል ደግሞ ፈተናዎችን በፅናት ከመወጣት አንጻር ሊቃኝ የሚገባው ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በግልና በተቋማዊ የግንኙት እና ተግባቦትመርሕ በተቻለ መጠን ዕውቀትን በጋራ እያለሙ በስፋትና በቀጣይነት ለመዝለቅ የተራራቁ ፍላጎቶችን በማቀራረብና ቢቻልም በማዋሐድ ወደላቀ የእድገት ምሕዋር ውስጥ ዘልቆ መግባት እንደሚቻል ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በዕውቀት የሚሠሩ ግላዊና ማኀበራዊ ጉዳዮች የእድሜልክ ተግባራት በሆኑት በዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ይታገዛሉ ወይም ሊታገዙ ይገባል፡፡ ይህም በውል አልሞ በመሠራት ላይ በተመሠረተ እና በማያቋርጥ የዕውቀትና ክህሎት አቅም ግንባታ የሚታገዝ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ ጥራትን እና ብቃትን ጠብቆ ወደ ውድድር ለመዝለቅ ሂደቱ የራሱ የሆነ የዕውቀት ሽግግርና ትግበራ ይጠይቃል፡፡ ይህም የሚበጀውን ወይም የሚያዋጣውን ነቅሶ በመያዝና በቀጣይም እየገመገሙ

የሚያስተካክሉበት አዕምሯዊና ተግባራዊ ዕውቀት በእጅጉ ይፈለጋሉ፡፡ ለዚህ ትኩረት መሥጠት ግድ ይላል፡፡ የተወሰደን ለማግኘት፣ የተወሳሰበን ለመፍታት የዕውቀት ባለቤቶችና አቅም አጐልባቾች ሚናቸው ከምንጊዜውም በላይ ይጠበቃል፡፡ በተለይ በማኅበራዊ ዕውቀት ቅኝት ውስጥ ሲታለፍ ጠያቂ፣ መርማሪ፣ ተከራካሪ፣ ሞጋች፣ ተቺ እና መስካሪ በስፋት ይከሠታል የሚል የላቀ ግምት አለ፡፡ ይህን የዕውቀት አምባ ከመናፈቅ ባሻገር ይዘውት እና ልምላሜውን ጠብቀው ሊያቆዩት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ዕውቀት ተቀባዩም የረጅም ጊዜ ተጠቃሚነትን ዓላማ አድርጐ በመናፈቅ በጉጉት ሊዋደቅበት ይገባል፡፡ ተሳትፏዊ ሁኔታን በማሟሟቅ ምክክራዊ እንቅስቃሴን ተገን አድርጐ መጓዝ ተገቢ ይሆናል፡፡ የምርትና የአገልግሎት አቅርቦቱና ተነፃፃሪ ትርፋማነቱም የዚህ ቅኝት ማጠንጠኛ ናቸው ሊባል ይችላል፡፡

ስለዚህ በተለያዩ ይዞታዎች ያሉ ዕውቀቶችን በመተሳሰብ መርሕ መቀመርና ተጠቃሚ መሆን የዕውቀት ኃያልነት ወቅታዊ የፊት ለፊት መገለጫዎች እንደሆኑ በራስ ምልከታ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

አነቃቂነት ያላቸው ሐሳቦችንና ተሞክሮዎችን መጋራት ተገቢ ነው፡፡ መማማሪያዎች የዕውቀት ኃያልነት መልክ መድረኮች ናቸው፡፡በማንኛውም ተቋማዊ፣ ሕዝባዊና ግላዊ ተልዕኮዎች ለመሰማራትና በአስተማማኝ የስኬት ማማ ላይ ለመድረስ በኃይል አሰላለፍ ረድፍ ውስጥ ዕውቀት ግንባር ቀደም መሆኑን አቻም እንደሌለው ሁሌም መረዳት ተገቢ ነው፡፡

እውነታንና ሐሳብን አምኖ ለመቀበል፣ ሰምቶና አዳምሮ ለመተግበር፣ ተግባብቶ ለመሥራት የዕውቀት ኃያልነትን ብቻ ሳይሆን ከተስፋ የላቀ የዕውቀት ዘመን መገለጫ ነው ብሎ መድፈር ይቻላል፡፡ ይህም መገለጫ ለሥርዓት ግንባታ፣ ለሕግና ደንብ ጽናት፣ ለአገር ልማት፣ ለፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መዋቅራዊ ሽግግር የሚጠበቅ የጽናት ዘመንን አብሣሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ መልኩ የዕውቀት ኃያልነት ማኅበራዊ መገለጫው ደግሞ ማኅበረሰቡ በግሉ ተነሳሽነት ወይም በጋራ አመለካከት ኖሮት የማኅበረሰቡ አባልና አካል ተግባብቶና ተስማምቶ መገኘት ነው፡፡

የዕውቀት ኃይል የትንተና ዱካን፣ የዛሬ ተግባርን እና የነገውን ራዕይ አጣምሮ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ስለሆነም ዕውቀት የትይይዝ መድረክና ሂደት መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ ሲደመደምም የዕውቀት ኃይል የራሱን ባርኔጣ አድርጎ እንዲጓዝ ማድረግ ጽናትን የግድ ይሻል፡፡

t.me/BooksandYou

ISBN 978-99944-66-45-0
9 789994 466450 >